TABLE OF CONTENTS

PART ONE GENERAL PROVISIONS 2
1.Short Title 2
2.Definitions 2
PART TWO CAPITAL MARKET AUTHORITY 21
3. Establishment of the Capital Market Authority 21
4. Head Office 22
5. Objective of the Authority 22
6. Powers and Duties of the Authority 22
7. Organisational Structure of the Authority 29
8. Composition and Appointment of Board of Directors 29
9. Conflicts of Interest 30
10. Tenure of Board Members 31
11. Removal or Resignation of Board Members 31
12. Powers and Duties of the Board 32
13. Meeting Procedures of the Board 33
14. Appointment, Powers, and Duties of Director General 34
15. Deputy Director General 36
16. Delegation of Power and Duties 36
17. Furnishing of Information to the uthority 37
18. Funds of the Authority 39
19. Accounts of the Authority 40
20. External Audit of the Authority's Accounts 40
21. Financial Year of the Authority 40
PART THREE RECOGNITION OF A SELF-REGULATORY ORGANIZATION 41
22. Application for Recognition 41
23. Conditions for Delegation of Power and Duties to a Self-Regulatory Organization 42
24. Rules of a Self-Regulatory Organization 43
25. Restrictions on Decision 44
26. Disciplinary Action 45
27. Appointment and Change of Senior Personnel 47
28. Removal of a Senior Personnel 47
29.Annual Report 48
PART FOUR SECURITIES EXCHANGE 49

30. Prohibition of Unlawful Securities Exchange 49
31. Establishment of the Ethiopian Securities Exchange 49
32. Other Securities Exchanges and Trading Platforms 50
33. Administrative Measures against a Securities Exchange and Trading Platforms 51
34. Management of a Securities Exchange 54
35. Rules of a Securities Exchange 56
36. Responsibilities of a Securities Exchange 56
37. Information Sharing, Reporting, and Assistance to the Authority 59
38. Amendment to Rules of a Securities Exchange 60
PART FIVE SECURITIES DEPOSITORY AND CLEARING COMPANY 61
39. Licensing 61
40. Obligations of Security Depository and Clearing Company 62
41. Rules and Regulations 63
42. Securities Registration 64
43. Custody and Record keeping 65
44. Clearing and Settlement 66
45. Finality of Securities Ownership Transfer 67
46. Winding Up or Placement in Bankruptcy Proceeding of a Securities Depository and Clearing Company Member 68
47. Arrangements and Rules Binding Liquidators 68
48. Collateral for Securities Transfer and Settlement Obligation 69
49. Prohibition in Dealings in Book-Entry Securities 70
50. Reporting on Counterparties 70
51. Business Continuity and Disaster Recovery 71
52. Administrative Measures Against a Security Depository and Clearing Company 71
53. Government Securities 73
54. Special Authorization 74
PART SIX LICENCING OF CAPITAL MARKET SERVICE PROVIDERS 75
55. Regulated Capital Market Activities and Services 75
56. Fit and Proper Persons 78
57. Applications for License 80
58. Refusal to Grant or Renew a License 80
59. Suspension of a License 81
60. Revocation of a License 82
61. Membership to a Self-regulatory Organization 84
62. Review of Accounts and Internal Control procedures 84

https://ethiodata.et/

63. Appointment of External Auditors 86
PART SEVEN CAPITAL MARKET TRIBUNAL 86
64. Establishment of the Capital Market Administrative Tribunal 86
65. The Jurisdiction of the Administrative Tribunal 87
66. Appointment of Members of the Administrative Tribunal 87
67. Disqualification of Members of the Administrative Tribunal 88
68. Administration of the Administrative Tribunal 88
69. Budget and Accounts of the Administrative Tribunal 88
70.Annual Report of the AdministrativeTribunal 89
71.Filing of an Appeal 89
72.Proceedingsof the Administrative Tribunal 90
73.Decision of the Administrative Tribunal 90
74. Appeal to the Federal High Court 92
PART EIGHT PUBLIC OFFERING AND TRADING OF SECURITIES 92
75. Registration of Securities 92
76. Prospectus for Securities Issued by Companies 93
77. Ongoing Information Disclosure Obligations 94
78. Offer of Asset-Backed Securities 96
PART NINE DISCLOSURE OF INTERESTS 97
79. Definition 97
80. Submitted Information 97
81. Notification of Changes 98
82. Register of Disclosure 98
PART TEN ACQUISITION AND PROTECTION OF MINORITY INTERESTS 99
83. Definition 99
84. Acquisition Offer 99
PART ELEVEN COLLECTIVE INVESTMENT SCHEMES 102
85. Legal Form 102
86. Registration of Collective Investment Schemes 103
87. Collective Investment Scheme Operator 104
88. Rights of Collective Investment Scheme Investors 106
89. Investment Advisor of a Collective Investment Scheme 106
90. Custodian of Collective Investment Scheme 107
91. Restrictions on Collective Investment Schemes 108
PART TWELVE PROHIBITED TRADING PRACTICES 109
92. Information Made Public 109
93. Inside Information 110

94. Insiders 110
95. Insider Trading 111
96. Market Manipulation 111
97. False Trading 112
98. Fraudulent Transactions 113
99.Use of Manipulative Means 114
100.False or Misleading Statements 114
101.Front–Running and Other TradingPractices 115
102.Restrictions on Trading of Securities 115
PART THIRTEEN COMPENSATION FUND 116
103.Establishment of a CompensationFund 116
104. Disbursements from the Fund 118
105. Assets and Liability of the Fund 118
PART FOURTEEN MISCLLANEOUS PROVISIONS 118
106. Criminal Liability 118
107.Administrative Measures 125
108.Power to Issue Regulations andDirectives 125
109. License Renewal 126
110. Administration of Employees 126
111. Settlement of Disputes 126
112.Inapplicable Laws 126
113.Effective Date 127

https://ethiodata.et/

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ ሀምሌ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፫

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No.33
ADDIS ABABA, 23rd July, 2021

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፰/፪ሺ፲፫

የካፒታል ገበያ አዋጅ…………………..ገጽ ፲፫ሺ፫፻፴፭

Content

Proclamation No.1248 /2021

Capital Market Proclamation …..........Page 13335

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፰/ ፪ሺ፲፫

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የካፒታል ገበያ አዋጅ

ካፒታል በማሰባሰብ፣ የገንዘብ ስርዓቱን በአዳዲስ ፈጠራዎች በመደገፍ እና የኢንቨስትመንት ስጋቶችን የመጋራት አሰራርን በማስፋፋት የአገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት የሚደግፍ የካፒታል ገበያ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

ኢንቨስተሮችን ለመጠበቅ እና ገበያው ፍትሃዊ፣ ተአማኒ እና ቀልጣፋ እንዲሆን የሚያስችል የቁጥጥር እና በበላይነት የመከታተል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፣

ከሕዝብ ካፒታል ለመሰብሰብ የሚፈልጉ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጭዎች የሚገዙበትን ወጥ የሆኑ መስፈርቶች በህግ መደንገግ በማስፈለጉ፣

በሀገሪቱ የፋይናንስ ስርዓት ላይ የሚፈጠሩ መዋቅራዊ ስጋቶችን ለመለየት፣ ለመከላከል፣ እና ለመቀነስ በካፒታል ገበያ ላይ ጠንካራ የቅርብ ክትትል እና የቅኝት ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፣

PROCLAMATION NO. 1248 /2021

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA CAPITAL MARKET PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to establish a capital market to support the development of the national economy through mobilising capital, promoting financial innovation, and sharing investment risks;

WHEREAS, it is necessary to adopt a legal framework for the regulation and supervision of the capital market to ensure the fairness, integrity, and efficiency of the market and protect investors;

WHEREAS, it is necessary to legislate uniform requirements for the regulation of issuers who desire to raise capital from public investors;

WHEREAS, it is necessary to adopt a legal framework for effective monitoring and surveillance of the capital market to detect, mitigate, and prevent systemic risk to the country's financial system;

https://ethiodata.et/

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው አዋጅ ታውጇል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፰/፪ሺ፲፫›› ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ ‹‹**ማስታወቂያ**›› ማለት፡-

ሀ) በጽሁፍ፣ ማስታወቂያ በመለጠፍ፣ ወይም በሰርኩላር ወይም በሌሎች ሰነዶች፤

ለ) በፎቶግራፎች፣ በሲኒማቶግራፊ ፊልሞች ወይም ቪዲዮ አውዲ-ርዕይ፤

ሐ) በድምጽ ስርጭት፣ በቴሌቪዥን፣ ወይም ቀረጻዎችን በማሰራጨት፤ ወይም

መ) እንደ ድረ-ገጽ እና ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን ባሉ ሌሎች ኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ብዙሃን መድረኮች፤

የሚተላለፉ ማስታወቂያዎችን ያካትታል፤

፪/ ‹‹**ተሿሚ እንደራሴ**›› ማለት በባለስልጣኑ የንግድ ፈቃድ የተሰጠውን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ በመወከል ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት የሚያከናውን ሰው ነው፤

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Capital Market Proclamation No.1248/2021."

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ **"Advertisement"** includes every form of advertising, whether:

a) in a publication, by the display of notices or by means of circulars, or other documents;

b) by the exhibition of photographs, cinematograph films or videos;

c) by way of sound broadcast, television, or by the distribution of recordings; or

d) other electronic media platforms such as websites and social media;

2/ **"An Appointed Representative"** means a person who conducts regulated activities and acts as an agent for a capital market service provider licensed by the Authority;

፫/ ‹‹**በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች**›› ማለት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሆነው የሚያስገኙት የገንዘብ ፍሰት በዋናነት ተለይተው በሚታወቁ የተሰበሳቢ ወይም ሌሎች የገንዘብ ሰነዶች፣ ቋሚ ወይም ተዘዋዋሪ የሆኑ፣ በውል በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ገንዘብ የሚለወጡ፣ በተጨማሪም እነዚህን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለያዛቸው ሰው የሚከፈለው ገንዘብ በወቅቱ እንዲፈፀም ለማረጋገጥ ዋስትና የተደረጉ ማንኛውም መብቶች ወይም ሌሎች ሃብቶች፣

ለ) አክሲዮኖችን ወይም ከጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች የሚገኙ መብቶችን ሳይጨምር ነገር ግን የተስፋ ወረቀቶችን ጨምሮ ማንኛውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣

ሐ) ሊሸጡ እና ሊለወጡ የማይችሉ ሰነዶችን ሰብስቦ እንዲሸጡ እንዲለወጡ ወይም በራሳቸው ለግብይት የማይውሉ ሰነዶች የግብይት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መፍጠር ሂደትን ተከትሎ በተቋቋመ ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋም ሃብት ላይ ከሚጠራቀም ዋና ብድር ወይም ወለድ፣ ገቢ፣ የካፒታል ክፍፍል ወይም ክፍያዎች ወይም በእነዚህ ተቋማት ላይ ድርሻ የያዙ ባለሃብቶች ማንኛውም መብት ወይም ጥቅም፣ የዕዳ ሰነድ ወይም ህጋዊ የአላባ ተጠቃሚነት ወይም በድርሻ ላይ የጥቅም መብቶችን የሚያረጋግጡ የምስክር ወረቀቶች፣ ወይም

መ) ሌላ ማንኛውም በሀብት የተደገፈ ሰነደ ሙዓለ ነዋይ አይነት መብት፣ ጥቅም ወይም ሰነድ፤

፬/ ‹‹**ባንክ**›› ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክ ስራ እንዲሰራ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም በመንግስት ባለቤትነት ስር ያለ ባንክ ማለት ነው፤

3/ **“Asset-Backed Securities (ABS)”** means:

a) securities that are primarily serviced by the cash flows of a discrete pool of receivables or other financial assets, either fixed or revolving, that by their terms convert into cash within a finite period of time, plus any rights or other assets designed to assure the servicing or timely distributions of proceeds to the security holders;

b) any securities including promissory notes but do not include shares or entitlements under a collective investment scheme;

c) any rights or interests, debentures or certificates evidencing the legal, equitable or beneficial interest or entitlement of its holder to a share of the assets of a special purpose vehicle or to entitlement to payment from such assets where payments or distributions of capital, income, principal or interest to investors accrue principally from the assets of the special purpose vehicle as a consequence of the establishment or operation of a securitization transaction; or

d) any other right, interest, instrument of security or class of securities prescribed to be asset-backed securities;

4/ **“Bank”** means a company licensed by the National Bank of Ethiopia to undertake banking business or a bank owned by the government;

፭/ **‹‹የካፒታል ገበያ››** ማለት እንደ አክሲዮን፣ ቦንድ፣ ተዛማጅ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም እነዚህን የመሰሉ የተለያዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የሚደረግበት ገበያ ነው፤

፮/ **‹‹የካፒታል ገበያ ተዋናዮች››** ማለት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች፣ ኢንቨስተሮች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ ተገቢነት ያላቸዉን ዉሎች ያደረጉ ብቁ የሆኑ ተጓዳኝ ወገኖች እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያዎች ናቸው፤

፯/ **‹‹የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ››** ማለት ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ስራዎች ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

፰/ **‹‹ማዕከላዊ የክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ወገን››** ማለት፡-

ሀ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይቶች ላይ ድህረ ግብይት የማጣራት እና ክፍያ የመፈጸም ስራን፣ እና

ለ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተገበያዮች መካከል የተቃራኒ ወገን ስጋትን የመውሰድ ስራን የሚመለከት ነው፤

፱/ **‹‹ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት››** ማለት፡-

ሀ) ከተማከለ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አያያዝ ጋር በተገናኘ፡-

(፩) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወጥነት ባለው መንገድ የሚከማቹበት፣ ወይም ወደ ኤሌክትሮኒክ ይዘት ተቀይረው የሚቀመጡበት፣ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በአውጪው ኩባንያ ወይም በአውጪው ኩባንያ ስም ሆኖ በሚሰራ ሌላ ኩባንያ ስም የሚመዘገቡበት ሆኖ እነዚህ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን

5/ **"Capital Market"** means a market where securities such as shares or equities, bonds, derivatives, or other related securities are bought and sold;

6/ "Capital Market Participants" means capital market service providers, issuers of securities, investors, securities exchanges, eligible counter parties to eligible contracts, and securities depository and clearing companies;

7/ **"Capital Market Service Provider"** means any person engaged in regulated capital market activities and services under this Proclamation;

8/ **"Central Clearing Counterparty"** refers to the act of:

a) providing post-trade clearing and settlement services for transactions in securities; and

b) taking on counterparty credit risks between parties to such a transaction;

9/ **"Central Securities Depository"** refers to a system:

a) for central handling of securities;

(1) where securities are immobilized or dematerialised and held in custody by, or registered in the name of the company or its nominee company for depositors and dealings in respect of these securities are effected by means of entries in securities accounts without the physical delivery of

በተመለከተ የሚደረግ ግብይት ሰነዶቹን በአካል ማረካከብ ሳያስፈልግ የሰነዶቹ መተሳሰቢያ መዝገብ ላይ ብቻ በሚደረግ ወጪና ገቢ ለማስተላለፍ የሚያስችል ስርዓት፣ ወይም

(፪) በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ሂደት ወቅት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ምዝገባ፣ ክፍያና እና ርክክብ ያለ አካላዊ ቅብብል ለማከናወን የሚያስችል ወይም ግብይቱን የሚያሳልጥ ዘዴ ወይም ስርዓት፤ እና

ለ) ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ድጋፎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሰጥ ስርዓት ነው፤

፲/ ‹‹**የመዝጊያ ማቻቻያ**›› ማለት በሁለት ሰዎች መካከል በተደረገ ስምምነት ዉስጥ ያሉ የተወሰኑ ድንጋጌዎችን ተፈጻሚ ማድረግ ሆኖ፡-

ሀ) ሌላኛውን ወገን በተመለከተ ግዴታን ባለመወጣት የሚከሰት ሁኔታ ወይም ሌላ የውል ማቋረጫ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም በውሉ በተመለከተው መሰረት በአንዳንድ ሁኔታዎች ወዲያውኑ ሊከሰት ወይም አንዱ ሰው ለሌላው ሰው በሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ሊጀመር የሚችል፤እና

ለ) የሚከተለው ውጤት ሲኖረው፤

(፩) ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ወይም ግንኙነት እና ተገቢነት ባላቸው ውሎች ላይ በሚነሱ ወይም በተያያዙ ማናቸውም አሁን ወይም ወደፊት የሚከፈሉ ክፍያዎች ወይም የማስረከብ መብቶች ወይም ግዴታዎች ሲቋረጡ፣ ሲጣሩ እና / ወይም ሲፋጠኑ፤

(፪) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ለ(፩) መሰረት የተቋረጠን፤ ሂሳቡ የተጣራን ወይም የተፋጠነን እያንዳንዱን መብትና

certificates; or

(2) which permits or facilitates the registration, clearing and settlement of securities transactions or dealings in securities without the physical delivery of certificates; and

b) that provides other facilities and services incidental thereto;

10/ **"Close-Out Netting''** means the operation of a set of provisions in an agreement between two persons that:

a) may be commenced by notice given by one person to the other person upon the occurrence of an event of default with respect to the other party or other termination event or that may, in certain circumstances, occur automatically as specified in the agreement: and

b) has the following effect:

(1) the termination, liquidation and/or acceleration of any present or future payment or delivery rights or obligations arising under or in connection with one or more eligible contracts;

(2) the calculation or estimation of a close-out value, market value, liquidation value, or

ግዴታ ወይም የመብቶችና ግዴታዎች መደብን በተመለከተ የመዝጊያ ዋጋ ፣ የገበያ ዋጋ፣ የማጣሪያ ዋጋ ወይም ምትክ ዋጋ ስሌት ወይም ግምት እና እያንዳንዱን ዋጋ ወደ አንድ አይነት መገበያያ ገንዘብ ሲለወጥ፤

(፫) አንድ ሰው የተጣራውን ሂሳብ መጠን የሚያህል ክፍያ ለሌላ ሰው እንዲፈጽም ግዴታ የሚጥል በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ለ(፪) መሰረት የተሰላን የተጣራ ዕዳን /ሂሳብን/ የመክፈል ግዴታን በማቻቻል ወይም በሌላ መንገድ መወሰን

ነው፤

፲፩/ ‹‹**የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ**›› ማለት፦

ሀ) ሰዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወይም ሌሎች ንብረቶችን በባለቤትነት በመያዝ፣ በይዞታ በማቆየት፣ በማስተዳደር፣ ወይም በማስተላለፍ ገቢ ወይም ትርፍ ለማግኘት የሚሳተፉበት ወይም ይህን ዓይነት ዓላማ ወይም ውጤት ለማስገኘት ታስቦ የተቋቋመ ወይም ከእንደዚህ ዓይነት አሰራር ከሚገኝ ገቢ ወይም ትርፍ የሚከፈልበት የስምምነት መዋቅር፤

ለ) በስምምነት መዋቅሩ ውስጥ የሚሳተፉ ኢንቨስተሮች የጋራ ማዕቀፉ ሀብቶች የዕለት-ተለት አስተዳደር ቁጥጥር የማይዙበት፤ እና

ሐ) የፈንዱን ሀብቶች የሚያስተዳድረው ሰው የፈንዱን ሀብት እና የአባላቱን ሂሳቦች በኃላፊነት የሚያስተዳድርበት

ነው፤

replacement value in respect of each right and obligation or group of rights and obligations terminated, liquidated and/or accelerated under Paragraph b(1) of this sub- article and the conversion of each such value into a single currency; and

(3) the determination of the net balance of the values calculated under Paragraph b(2) of this Sub- Article, whether by operation of set-off or otherwise, giving rise to the obligation of one person to pay an amount equal to the net balance to the other person;

11/ **“Collective Investment Scheme”**means any arrangement where:

a) it is made for the purpose, or having the effect, of providing facilities for persons to participate in or receive profits or income arising from the acquisition, holding, management or disposal of securities, or any other property or sums paid out of such profits or income;

b) investors who participate in the arrangements do not have day-to-day control over the management of the scheme's assets; and

c) the scheme's assets are managed by a person who is responsible for the management of the scheme's assets and client accounts;

፲፪/ ‹‹**የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስራ አከናዋኝ**›› ማለት ለአንድ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ የስራ አመራር እና አፈጻጸም አጠቃላይ ኃላፊነት ያለበት ተቋም ነው፤

፲፫/ ‹‹**ኩባንያ**›› ማለት በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ መሠረት የተቋቋመ የአክሲዮን ኩባንያ ነው፤

፲፬/ ‹‹**ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት**›› ማለት የአንድን ተቋም፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጭ ብድርን የመመለስ አቅም በተመለከተ ተቀባይነት ያላቸው እና የታወቁ የመመዘኛ መስፈርቶችን በመጠቀም የሚሰጥ አስተያየት ነው፤

፲፭/ ‹‹**ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲ**›› ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በተሰጠ የባለስልጣኑ ፈቃድ ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት የሚሰጥ ሰዉ ነዉ፤

፲፮/ ‹‹**ጠባቂ**›› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የደንበኞችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለጥበቃ ዓላማ ወይም ለምቹ አያያዝ ሲባል በይዞታው ስር የሚያስቀመጥ የገንዘብ ተቋም ነው፤

፲፯/ ‹‹**ቀናት**›› ማለት በኢትዮጵያ ካላንደር መሠረት ከቅዳሜ፣ ከእሁድ እና ከሕዝብ በዓላት ውጭ ያሉ ቀናት ማለት ነው፤

፲፰/ ‹‹**በሰነደ ሙዓለ ንዋይ መገበያየት**›› ማለት ለራስ ወይም ስለ ሌሎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን፡-

ሀ) መሸጥ ወይም መግዛት፣
ለ) ማውጣት ወይም ለሽያጭ ማቅረብ፣
ሐ) ማስቀመጥና መጠበቅ፣
መ) ክፍያ ማጣራትና መፈጸም፤
ሠ) ማበደር ወይም ማስያዝ፣ ወይም

12/ **"Collective Investment Scheme Operator"** means a legal entity that has overall responsibility for management and performance of the functions of a collective investment scheme;

13/ **"Company"** means a share company as defined in the Commercial Code of Ethiopia;

14/ **"Credit Rating Service"** means an opinion regarding the credit worthiness of an entity, a security or an issuer of securities using an established and defined rating systems or rating categories;

15/ **"Credit Rating Service Agency"** means a person licensed by the Authority under this Proclamation to provide credit rating services;

16/ **"Custodian"** means a financial institution that holds customers' securities for safe-keeping or convenience as per the provisions of this proclamation;

17/ **"Days"** means calendar days excluding Saturdays, Sundays and public holidays in Ethiopia;

18/ **"Dealing in Securities"** means dealing in securities for own account or for the account of others by:

a) selling or purchasing,
b) issuing or public offering,
c) depositing or taking custody of,
d) clearing and settling,
e) lending or pledging, or

https://ethiodata.et/

ረ) ሌላ ማንኛውም ባለስልጣኑ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ የሚደረግ ግብይት ነው ብሎ የሚወስነው ስራ ነው፤

፲፱/ ‹‹**የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋይ**›› ማለት ማንኛውም በኩባንያ የሚወጣ ወይም ሊወጣ የታቀደ የዕዳ ሰነድ፣ ዋስትና ያለው የዕዳ ሰነድ፣ የብድር ስቶክ፣ ቦንድ፣ ወይም የተስፋ ሰነድ ሆኖ ባለዕዳነትን የሚፈጥር ወይም የሚያረጋግጥ ነው፤

፳/‹‹**ግዑዝ-አልባ ማድረግ**›› ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማውጣት እና መመዝገብ ነው፤

፳፩/ ‹‹**ግዑዝ-አልባ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ**›› ማለት የሰነዱ ባለቤትነት በኤሌክትሮኒክ የምዝገባ ደብተር ባለቤትነትን በማስገባት ብቻ የሚረጋገጥበት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ነው፤

፳፪/ ‹‹**ተዛማጅ**›› **ወይም** ‹‹**ተዛማጅ ውል**›› ማለት ዋጋው ከሌላ መሠረታዊ ከሆነ እንደ አክሲዮን፣ ቦንድ፣ ወይም ምርቶች እና ገንዘቦች ያሉ ሀብቶች ወይም ምጣኔዎች የሚመነጭ ሆኖ እንደ አክሲዮን ወይም ሌላ የገንዘብ ሰነድ የሚሸጥ፣ የሚገዛ ወይም ግብይት የሚደረግበት ገንዘብ ነክ ሰነድ ነው፤

፳፫/ ‹‹**የተዛማጅ ውሎች ገበያ**›› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በገበያው ተመዝግበው ግብይት ሊደረግባቸው የሚችሉ ተዛማጅ ውሎች እንዲመዘገቡበት በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ወይም ለዚሁ ዓላማ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት ይሁንታ የተሰጠው ገበያ ነው፤

፳፬/ ‹‹**ተገቢነት ያለው ውል**›› ማለት ተዛማጅ ውል፣ መልሶ የመግዛት ውል ወይም ባለስለጣኑ በመመሪያ ተገቢነት ያለው ብሎ የሚወስነው ሌላ ግብይት ነው፤

f) any other transaction that the Authority considers as "dealing in securities;

19/ **"Debt Security"** means any instrument creating or acknowledging indebtedness issued or proposed to be issued by a company including a debenture, debenture stock, loan stock, bond or note;

20/ **"Dematerialisation"** means the issuance and recording of securities in electronic format;

21/ **"Dematerialised Security"** means a security whereby the prima facie evidence of legal title to the security is established by an electronic book entry;

22/ **"Derivatives" or "Derivatives Contract"** means financial instruments which derive their value from the value of the relevant assets or rates such as shares, bonds, commodities, and currencies, and which can be purchased or sold or traded in a similar method as the trading of shares or of any other financial assets;

23/ **"Derivatives Exchange"** means a securities exchange which has been granted a license to list exchange-traded derivative contracts by the Authority under this Proclamation or approved for such purposes and in accordance with the regulations or directives issued thereunder;

24/ **"Eligible Contract"** means derivative contract, repo contract or any other transactions which the Authority designates as an eligible contract by directive;

፳፭/ **‹‹የውጭ ኦዲተር››** ማለት የኦዲት አገልግሎት እንዲሰጥ በሚመለከተው የመንግስት አካል ፈቃድ የተሰጠው ገለልተኛ ኦዲተር ነው፤

፳፮/ **‹‹ሀሰተኛ መረጃ››** ማለት በአቀራረቡ እና በተገለጸበት አውድ ውስጥ ሲታይ አሳሳች የሆነ አገላለጽ ሲሆን በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ ሳይካተት የቀረ ወይም ሆን ተብሎ ኢንቨስተሮችን ወይም የገበያ ተሳታፊዎችን ለማሳሳት የተገለጸን ማንኛውም በጽሁፍ የቀረበ ነገርን ይጨምራል፤

፳፯/ **‹‹የገንዘብ ሰነዶች››** ማለት በተዋዋዮች መካከል የሚደረጉ፣ የሚሻሻሉ፣ ግብይት እና ክፍያ የሚደረግባቸው ገንዘባዊ ይዘት ያላቸው ውሎች ናቸው፤

፳፰/ **‹‹የውጭ አገር ኢንቬስተር››** ማለት እንደ ኢትዮጵያዊ መቆጠር የሚፈልግ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጭ አገር ዜጋን ሳይጨምር በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ አገር ካፒታል በስራ ላይ ያዋለ ሆኖ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ) የውጭ አገር ዜጋ፤

ለ) የውጭ አገር ዜጋ የባለቤትነት ድርሻ የያዘበት ድርጅት፤

ሐ) ከኢትዮጵያ ውጭ በማንኛውም ኢንቬስተር የተመዘገበ ድርጅት፤

መ) በ ‹ሀ›፣ ‹ለ› እና ‹ሐ› ከተጠቀሱት ኢንቬስተሮች በሁለቱ ወይም በሦስቱ በጋራ የተቋቋመ ድርጅት፤ ወይም

ሠ) እንደ ውጭ አገር ኢንቬስተር መስተናገድ የመረጠ በቋሚነት በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ፤

25/ **“External Auditor”** means a public auditor licensed by the pertinent government organ to provide audit service,

26/ **“False Statement”** includes a statement that is misleading in the form and context in which it is made. It also includes an omission from a prospectus or written statement of any matter that, in the context, is calculated to mislead investors or market participants;

27/ **“Financial Instruments”** are assets that consist of monetary contracts between parties and that can be created, modified, exchanged, and settled;

28/ **“Foreign Investor”** means any one of the following who has invested foreign capital in Ethiopia:

a) A foreign national;

b) An enterprise in which a foreign national has an ownership stake;

c) An enterprise incorporated outside of Ethiopia by any investor;

d) An enterprise established jointly by two or three of the investors specified under paragraphs (a), (b) and (c) of this sub-article; or

e) An Ethiopian permanently residing abroad and preferring treatment as a foreign investor;

but, doesn’t include foreign nationals of Ethiopian origin who prefer to be treated as Ethiopian nationals;

https://ethiodata.et/

፳፱/ ‹‹**መንግስት**›› ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ነው፤

፴/ ‹‹**ሰነድን ማስቀመጥ**›› ማለት በወረቀት መልክ ያለን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የምስክር ወረቀቶች በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በማስቀመጥ የሰነዶቹ ዝውውር በሂሳብ መዝገብ ለውጥ ብቻ እንዲከናወን ማስቻል ነው፤

፴፩/ ‹‹**ተቀማጭ የተደረገ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ**›› ማለት የመሠረታዊው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የምስክር ወረቀት በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት እንዲመዘገብና እንዲቀመጥ የተደረገ ሰነድ ነው፤

፴፪/ ‹‹**የመጀመሪያ ዙር የሕዝብ ሽያጭ**›› ማለት:-

ሀ) አስቀድሞ የኩባንያው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሕዝብ በሽያጭ ባልቀረቡበት ሁኔታ፤ ወይም

ለ) አስቀድሞ ለህዝብ በሽያጭ የቀረቡት የኩባንያው አክሲዮኖች ከጊዜ በኋላ ሙሉ በሙሉ በኩባንያው ተመልሰው በተገዙበት ሁኔታ፣

ማንኛውንም የአንድ ኩባንያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሕዝብ ለመሸጥ ማቅረብ ነው፤

፴፫/ ‹‹**ኢንቨስተር**›› ማለት ትርፍ ለማግኘት ሲል በዚህ አዋጅ መሰረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የሚገዛ፣ የሚሸጥ ወይም የሚይዝ ማንኛዉም ሰዉ ነዉ፡፡

፴፬/ ‹‹**የኢንቨስትመንት ባንክ**›› ማለት ተቀማጭ ገንዘብ የማይሰበስብ የገንዘብ ተቋም ሆኖ በሌሎች ኩባንያዎች፣ በመንግስት ወይም በሌላ ተቋም የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በውክልና በመሸጥ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪውን ከገበር ሕብረተሰብ ጋር በማገናኘት ካፒታል

29/ **"Government"** means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

30/ **"Immobilization"** means depositing of physical certificates of securities in a central securities depository to facilitate book-entry transfers;

31/ **"Immobilized Security"** means a security where the underlying physical certificates have been deposited with and are held by a central securities depository;

32/ **"Initial Public Offering"** means an offer to the public of any securities or a company, if:

a) no securities of that company have previously been the subject of an offer to the public; or

b) all of the securities of that company that had previously been the subject of an offer to the public have subsequently been re-acquired by the company;

33/ **"Investor"** means any person who sells, buys, or holds securities in accordance with this Proclamation with the expectation of a financial return from such transactions.

34/ **"Investment Bank"** means a non-deposit taking financial institution that facilitates the creation of capital for other companies, governments, and other entities through underwriting, acting as an intermediary between a securities issuer and the investing public, facilitating

በማሰባሰብ፣ የኩባንያዎችን ውህደት እና ዳግም መልሶ የማዋቀር ስራዎችን በማገዝ፣ ለደንበኞቹ እንደ ደላላ እና ገንዘብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የአማካሪነት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤

፴፭/ ‹‹**ኢንቨስትመንት**›› ማለት ቀጥለው የተዘረዘሩትን ያካትታል፡-

ሀ) ለህዘብ በሽያጭ የቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣

ለ) በውጭ አገር የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም የግብይት መድረክ የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት በተፈቀደ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያለ የባለቤትነት ድርሻ ወይም ክፍልፋይ፣

መ) ከላይ የተጠቀሱ ዓይነት የባለቤትነት ድርሻዎችን ወይም ክፍልፋዮችን እና ሌሎች መሰል ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት የተመደቡ ገንዘቦች፣ ወይም

ሠ) ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በባለስልጣኑ በሚወጣ መመሪያ ኢንቨስትመንት ነው ተብሎ የተፈረጀ ሌላ ማንኛውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይን፡፡

፴፮/ ‹‹**የኢንቨስትመንት አማካሪ**›› ማለት ፈቃድ ተሰጥቶት እና፡-

ሀ) ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ሌሎችን የማማከር ስራ የሚሰራ፤

ለ) ኢንቨስትመንትን የተመለከቱ ሪፖርቶችን እና ትንተናዎችን የማውጣት እና የማሰራጨት ስራን መደበኛ ስራው አድርጎ የሚሰራ፤ ወይም

ሐ) እንደ ቦንድ፣ ምርት፣ የጋርዮሽ ገንዘብ እና አክሲዮን በመሳሰሉ የተወሰኑ የኢንቨስትመንት ዓይነቶች ላይ የተለየ ፈቃድ ተሰጥቶት በገንዘብ ነክ እና

mergers and other corporate reorganizations and acting as a broker or financial adviser for institutional clients;

35/ **“Investment”** refers to:

a) securities publicly offered;

b) securities listed on a foreign securities exchange or facility;

c) ownership interests and/or units in a collective investment scheme approved under this Proclamation;

d) funds intended for the purchase of such securities, units or other instruments; or

e) any other instruments declared to be investments for the purposes of this Proclamation by a directive of the Authority.

36/ **“Investment Adviser”** means a licensed person who:

a) carries out the business of advising others concerning investments;

b) as part of a regular business, issues or promulgates analyses or reports concerning investment; or

c) a financial institution licensed to provide investment advice on particular type of investment such as bonds, commodities, mutual funds,

በኢንቨስትመንት ጉዳዮች ላይ ምክር የሚሰጥ ሰው ነው፡፡

፴፯/ ‹‹**አውጪ**›› ማለት መንግስት፣ ኩባንያ ወይም ሌላ ሕጋዊ ድርጅትን ጨምሮ ማንኛውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለሽያጭ የሚያወጣ፣ ወይም ለማውጣት መዘጋጀቱን የሚያስተዋውቅ ሰው ነው፤

፴፰/ ‹‹**ፈቃድ**›› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ባለስልጣኑ ለአንድ ሰው በማንኛውም ባለስልጣኑ በሚቆጣጠረው ዘርፍ ላይ እንዲሰማራ የሚሰጠው የንግድ ፈቃድ ነው፤

፴፱/ ‹‹**ፈቃድ ያለው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ**›› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ነው፤

፵/ ‹‹**የምዝገባ መስፈርቶች**›› ማለት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ገበያ በተመለከተ የሚከተሉት ጉዳዮች የሚገዙበት ውስጠ-ደንብ ነው፡-

ሀ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመመዝገብ ወይም ለሽያጭ እንዲቀርቡ የመፍቀድ አሰራር፣ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከምዝገባ ለመሰረዝ ወይም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች፤ ወይም

ለ) በመዝገቡ ውስጥ ስለገቡ አውጪዎች ወይም ሌሎች በመዝገብ እንዲገቡ ስለተፈቀደላቸው ሰዎች አሰራር ወይም ስነምግባር በሚመለከት የሚወጡ ውስጠ-ደንቦች ሆነው፤

(፩) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የወጡ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው መሠረታዊ ሰነዶች የተካተቱ፤ ወይም

(፪) በሌላ ሰው ወጥተው በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው በሥራ ላይ የዋሉ፡፡

and stocks.

37/ **“Issuer”** means any person who issues or proposes to issue any security; and shall include a government, company or other legal entity that offers securities to the public;

38/ “**License”** means a business license that is granted by the Authority to a person to carry out a business in any regulated activity;

39/ “Licensed Securities Exchange” means a securities exchange to which an exchange license has been issued under this Proclamation;

40/ **“Listing Requirements”** mean, in relation to a securities exchange, rules governing or relating to:

a) The grant of permission to listing or dealing in securities on a securities exchange or the removal from listing or for other purposes; or

b) The activities or conduct of issuers and other persons who are admitted to that list, whether those rules are made by:

(1) the securities exchange or are contained in any of the constituent documents of the securities exchange; or

(2) another person and adopted by the securities exchange.

፵፩/ ‹‹**የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች**›› ማለት ፈቃድ ባለው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ የተመዘገቡ ወይም ለሽያጭ የቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማለት ነው፤

፵፪/ ‹‹**ገበያ ከፋች**›› ማለት ባለስልጣኑ ተግባራዊ በሚያደርገው የቁጥጥር ስርዓት መሠረት ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አቅርቦት እና ፍላጎት እንዲኖር የሚያደርግ ሰው ነው፤

፵፫/ ‹‹**ከፍ አድርጎ መዝጋት**›› ማለት ሆን ብሎ የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን የመዝጊያ ዋጋ ከፍ ለማድረግ በማሰብ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በእለቱ የግብይት ማብቂያ የመጨረሻ ሰዓት ላይ ገበያው ላይ ካለው ዋጋ እጅግ ከፍ ባለ ዋጋ መግዛት ነው፤

፵፬/ ‹‹**የጋርዮሽ ገንዘብ**›› ማለት ከኢንቨስተሮች ገንዘብን የማሰባሰብ እና የኢንቨስትመንት ስጋቶችን የመጋራት ዓላማ ወይም ውጤት ያለውና ትርፍ እዲከፋፈሉ፣ ወይም ኢንቨስትመንቶቹን ከመግዛት፣ ከመያዝ፣ ከማስተዳደር እና ከማስተላለፍ የሚገኙ ጥቅሞችን በጋርዮሽ ገንዘቡ ለሚሳተፉ ኢንቨስተሮች የሚያስገኙ የባለቤትነት ድርሻዎችን ወይም ክፍልፋዮችን የሚሸጥ ኩባንያ ወይም ሽርክና ማህበር ነው፤

፵፭/ ‹‹**ብሔራዊ ባንክ**›› ማለት በተሻሻለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፩/፪ሺ መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

፵፮/ ‹‹**የማቻቻያ ስምምነት**›› ማለት ስለማቻቻል የሚደነግግ በሁለት ሰዎች መካከል የተደረገ ስምምነት ሆኖ ያለምንም ገደብ:-

41/ **“Listed Securities”** means securities listed or quoted on a licensed securities exchange;

42/ **“Market Maker”** means a person who ensures the availability of supply and demand for one or more securities according to such controls as may be laid down by the Authority;

43/ **“Mark the close”** means buying a security at the very end of the trading day at a significantly higher price than the current price of the security with the intention to raise the closing price of the security;

44/ **“Mutual Fund”** means a company or partnership that issues equity interests or units, the purpose or effect of which is the pooling of investor funds with the aim of spreading investment risks and enabling investors in the mutual fund to receive profits or gains from the acquisition, holding, management or disposal of investments;

45/ **“National Bank”** means the National Bank of Ethiopia established under the National Bank of Ethiopia Establishment (as amended) Proclamation No. 591/2008;

46/ **“Commensurable Agreement”** means an agreement between two persons that provides for netting, including, without limitation:

ሀ) ከሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ የማቻቻያ ስምምነቶች መሰረት ክፍያቸው የደረሰ ገንዘብን የሚያቻችል ስምምነትን፣ እና

ለ) ከማቻቻያ ስምምነት ጋር ተያያዥ ወይም የስምምነቱ አካል የሆነ የዋስትና አደረጃጀትን

ያካትታል፡፡

፵፯/ ‹‹**የተውሶ ስም**›› ማለት አንድ ሰው ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤት ጋር ባደረገው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የመጠበቅ ስምምነት መሠረት ሰነዱ በስሙ በገቢና ወጪ መዝገብ ውስጥ የተመዘገበ ሆኖ የሰነዱ ባለቤትና ተጠቃሚ ሌላ ሰው የሆነበት አሰራር ነው፤

፵፰/ ‹‹**ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ**›› ማለት ዕውቅና ከተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ውጭ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና/ወይም ተዛማጆች በሻጮችና በገዢዎች መካከል በቀጥታ (ፊት ለፊት ወይም እንደ ስልክ እና የኮምፒዩተር መረብ) በሚደረግ ግንኙነት ግብይት የሚደረግበት ገበያ ነው፤

፵፱/ ‹‹**የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ**›› ማለት በውክልና ሻጮች አስተባባሪነት አዳዲስ አክሲዮኖችን፣ ቦንዶችን፣ የተስፋ ሰነዶችን፣ እና ሌሎች ገንዘባዊ ሰነዶችን በመሸጥ አዲስ ካፒታል የሚሰበሰብባቸው ገበያ ናቸው፤

፶/ ‹‹**የመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪ**›› ማለት ቁጥጥር በሚደረግባቸዉ ተግባራት ላይ ተቀዳሚ የመቆጣጠር እና በበላይነት የመከታተል ስልጣን ያለው የፌዴራል መንግስት ኤጀንሲ ነው፤

፶፩/ ‹‹**ለግል ሽያጭ ማቅረብ**›› ማለት ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ ሳያቀርቡ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ኢንቬስተሮች ማቅረብ ነው፤

a) An agreement that provides for the netting of amounts due under two or more netting ageements; and

b) a collateral arrangement relating to or forming part of a netting agreement.

47/ **“Nominee”** means a person in whose name securities are recorded on a book-entry register and held for the beneficial owner of the securities under a custodial agreement with the beneficial owner;

48/ **“Over-the-Counter Market”** means a market in which securities and/or derivatives are traded by parties directly (face-to-face or using communication devices such as telephones and networked computers) with each other rather than through a recognized exchange;

49/ **“Primary Market”** means a market facilitated by underwriters in which new capital is created or raised by selling newly issued stocks, bonds, notes, and other financial instruments;

50/ **“Primary Regulator”** means a federal regulatory authority having a primary jurisdiction and supervising authority over a regulated activity;

51/ **“Private Placement”** means the act of offering securities to a limited number of investors, according to a Directive to be issued by the Authority, rather than to the general public.

፶፪/ **‹‹ደንበኛ ሳቢ መግለጫ››** ማለት በአክሲዮን ኩባንያ ወይም በኩባንያው ስም የወጣ እና ኩባንያው ስላወጣቸው አክሲዮኖች፣ የዕዳ ሰነዶች፣ ወይም ሌሎች የኩባንያው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባህሪ፣ እና ዓላማ የሚገልጹ መረጃዎችን በማካተት ሕዝብ እንዲገዛ ጥሪ የሚደረግበት የጽሁፍ ሰነድ ወይም ሕትመት ነው፤

፶፫/ **‹‹የሕዝብ ኩባንያ››** ማለት ሰነዶቹ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ቢመዘገቡም ባይመዘገቡም አክሲዮኖቹ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የሚሸጡ የአክሲዮን ኩባንያ ነው፤

፶፬/ **‹‹የህዝብ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋይ››** ማለት በመንግስት ወይም በመንግስት ስም ወይም በመንግስት ተቋማት ስም የሚወጣ ባለዕዳነትን የሚፈጥር ወይም የሚያረጋግጥ ማንኛውም የብድር ስቶክ፣ ቦንድ፣ የተስፋ ሰነድ፣ ወይም ሌላ መሰል ሰነድ ነው፤

፶፭/ **‹‹የመንግስት የልማት ድርጅት››** ማለት ሙሉ በሙሉ በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ነው፤

፶፮/ **‹‹ለሕዝብ ማቅረብ››** ማለት አንድ ኩባንያ በንግድ መዝገብ ከመመዝገቡ ወይም አውጪው ኩባንያ ሰነዶቹን ከመሸጡ በፊት ካፒታሉን ለማሰባሰብ በአደራጆቹ አማካኝነት የሚደረግ ሰነዶቹን ለሕዝብ ለሽያጭ የማቅረብ ተግባር ነው፤

፶፯/ **‹‹ለሕዝብ የሚሸጥ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ››** ማለት በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ የሚሸጥ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ነው፤

፶፰/ **‹‹ቁጥጥር የሚደረግበት ሰው››** ማለት በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው እና ባለስልጣኑ የስራ እንቅስቃሴውን

52/ **“Prospectus”** refers to a document or a publication by, or on behalf of, a share company containing information on the character, nature, and purpose of an issue of shares, debentures, or other corporate securities that extends an invitation to the public to purchase the securities;

53/ **“Public Company”** is a share company, whether listed on a securities exchange or not, whose shares of stock are traded on a securities exchange or over-the-counter markets;

54/ **“Public Debt Security”** means any loan stock, bond, note or other instrument creating or acknowledging indebtedness issued by or on behalf of the Government and other government entities;

55/ **“Public Enterprise”** means an enterprise wholly owned by the government;

56/ **“Public Offer”** means the act of offering securities to the general public in order to raise capital by the promoters prior to the incorporation of the company, or by the issuing company prior to the issuance of said securities;

57/ **“Publicly Traded Security”** means a security traded on a securities exchange or through over-the-counter markets;

58/ **“Regulated Person”** means any person who has been granted a license under this Proclamation, or any other Proclamation

https://ethiodata.et/

በተመለከተ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት ሰው ወይም ፈቃድ የተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም ፈቃድ ከተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ጋር ወይም ከባለፈቃድ ሰው ጋር የሚሰራ ማንኛውም ሰው ነው፤

፶፱/ ‹‹ **መልሶ የመግዛት ውል** ›› ማለት በተወሰነው ቀን በተወሰነ ዋጋ ወይም ባልተገለጸ ወደ ፊት ባለ ቀን በተወሰነ ዋጋ ለመሸጥና በመቀጠልም መልሶ ለመግዛት የሚደረግ ውል ሲሆን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መሸጥንና መልሶ መግዛትን ወይም መግዛትንና መልሶ መሸጥን ያካትታል፤

፷/ ‹‹**ውስጠ-ደንቦች**›› ማለት ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ወይም ራሱን በራሱ ከሚቆጣጠር ድርጅት ጋር በተያያዘ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ፣ ወይም ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እና የአባላቶቻቸዉ የገበያ እንቅስቃሴ እና የአሰራር ስነ-ምግባር የሚገዙባቸው ድንጋጌዎች ናቸው፤

፷፩/ ‹‹**ሁለተኛ ደረጃ ገበያ**›› ማለት ኢንቬስተሮች በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ በቀጥታ ከአውጪው ወይም ከአገናኙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከሚገዙበት ውጪ አስቀድመው የወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከሌሎች ኢንቬስተሮች የሚገዙበት ገበያ ማለት ነው፤

፷፪/ ‹‹**ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች**›› ማለት በማንኛውም ሕጋዊ መልክ ያለ በገንዘባዊ ግብይት የድርሻ ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ እና በባለስልጣኑ ፈቃድ መሠረት የሚተላለፍ ሆኖ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

for whose administration the Authority is wholly or partly responsible or an approved securities exchange or any persons associated with such licensees or approved securities exchanges;

59/ “**Repurchase Agreement**” means a contract to sell and subsequently repurchase securities at a specified date and price; or unspecified future date for a specified price; and includes an agreement to sell and buy back or buy and sell back securities;

60/ **“Rules”** means, in relation to a securities exchange, a securities depository and clearing company, or a self-regulatory organization, the rules governing the activities and market conducts of a securities exchange, a securities depository and clearing company, or a self-regulatory organization and their respective members;

61/ **“Secondary Market”** means market or markets where investors buy previously issued securities from other investors as opposed to the primary market, where investors buy new securities directly from the issuer or an intermediary;

62/ **“Securities”** means any instrument - in any legal form - that evidences ownership of a share in a financial transaction and that is negotiable pursuant to approval from the Authority, such as:

ሀ) በኩባንያ ካፒታል ውስጥ የወጡ ወይም የሚወጡ አክሲዮኖችን፤

ለ) በኩባንያ የወጡ ወይም የሚወጡ ባለዕዳነትን የሚፈጥሩ ወይም የሚያረጋግጡ ማናቸውም ሰነዶች፤

ሐ) ብድሮች፣ ቦንዶች፣ እና ሌሎች ወደ ኩባንያ ካፒታልነት ሊቀየሩ የሚችሉ ሰነዶችን፤

መ) ሁሉም በመንግስት እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የወጡና ለግብይት የሚውሉ የህዝብ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤

ሠ) ማንኛውም ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር የተያያዘ እንደ ኦፕሽን እና ለወደፊት የሚፈፀም ውል ዓይነቶች መብትን፣ ወይም ተዛማጅን፤

ረ) በጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያለ የድርሻ ክፍልፋይን፤

ሰ) ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል ማንኛውም በባለስልጣኑ ሰነድ ነው ተብሎ የተፈረጀ ወረቀትን ወይም መሳሪያን

ነገር ግን እንደ ቼክ፣ የተስፋ ሰነድ፣ የሃዋላ ወረቀት፣ የንግድ ወረቀቶችን፣ ሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ ጥሬ ገንዘብ ማስተላለፍ እና በባንኮች መካከል እርስ በርስ ብቻ የሚተላለፉ ሰነዶችን፣ የመድን ፖሊሲዎችን፣ እና ለተጠቃሚዎች ከጡረታ ክፍያዎች የሚመነጩ መብቶችን አያካትትም፡፡

፷፫/ ‹‹**የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ**›› ማለት ኮሚሽን እያስከፈለ በሌሎች ስም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የመሸጥ እና የመግዛት ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

a) shares issued or proposed to be issued in the capital of a company;

b) any instrument that creates or acknowledges a debt issued or to be issued by a company;

c) loans, bonds, and other instruments that can be converted to shares in the capital of a company;

d) all public debt instruments that are tradable and issued by the Government and other government entities;

e) any right or derivative contracts relating to securities (such as options and futures);

f) units in a collective investment scheme;

g) any paper or instrument considered by the Authority as a security for the purposes of implementing this Proclamation

but does not include commercial papers such as cheques, promissory notes, bills of lading, letters of credit, cash transfers and instruments negotiated by banks exclusively between each other, insurance policies and rights arising from retirement funds established for the benefit of the beneficiaries therefrom.

63/ **"Securities Broker"** means a person which conducts the business of purchase and sale of securities for the account of others in consideration of a commission;

https://ethiodata.et/

፷፬/ **‹‹የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ አከናዋኝ››** ማለት በሙሉ ጊዜው ወይም በትርፍ ጊዜው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ እንደ ወኪል፣ ደላላ፣ ወይም ራሱ ተገበያይ ሆኖ በሌላ አካል የወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሽያጭ በማቅረብ፣ ለግዥ በማቅረብ ወይም በግብይት ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤

፷፭/ **‹‹የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ››** ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የማስቀመጥ፣ ክፍያዎችን የማጣራትና የመፈጸም እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን የሚያከናውን ሕጋዊ ድርጅት ነው፤

፷፮/ **‹‹የሰነድ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪ ፈፃሚ ኩባንያ አባል››** ማለት የካፒታል ገበያ ተሳታፊ፣ ባንክ፣ በተወሰ ስም የሚሰራ፣ ወይም ሌላ የፋይናንስ ተቋም ሆኖ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግብይት ክፍያ ለማጣራትና ለመፈጸም የሚያስችል፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሚቀበልበት፣ የሚይዝበት እና የሚያስተላልፍበት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሂሳብ መዝገብ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ያለው ነው፤

፷፯/ **‹‹የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ››** ማለት ፈቃድ ያላቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያን የመስሪያ ቦታ በተመለከተ የገበያ መሰረተ-ልማቶችን አካትቶ የሚያቀርብ፣ የሚያዘጋጅ፣ የሚያመቻች ሲሆን በመሠረተ-ልማቱ አማካኝነት፡-

ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሽያጭ፣ ግዥ እና ልውውጥ በቋሚነት የሚደረግበት፤

ለ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተቀባይነት እንዲያገኙ የታሰቡ ወይም በምክንያታዊነት የሚጠበቁ ሰነደ ሙዓለ

64/ **"Securities Dealer"** means any person who engages either for all or part of his time, directly or indirectly, as agent, broker, or principal, in the business of offering, buying, selling, or otherwise dealing or trading in securities issued by another person;

65/ **"Securities Depository and Clearing Company"** means any legal entity that offers securities depository, clearing and settlement, and other related services;

66/ **"Securities Depository and Clearing Company Member"** means a capital market participant, a Bank, a Nominee, or any other Financial Institution that has one or more accounts with the securities depository and clearing company for receiving, holding or delivering securities to facilitate the clearance and settlement of securities transactions;

67/ **"Securities Exchange"** means, in relation to premises of a licensed securities exchange, the one place in those premises which constitutes, maintains or provides a market or a facility by means of which:

a) offers to sell, purchase or exchange securities are regularly made or accepted;

b) offers or invitations are regularly made, being offers or invitations that are intended, or may reasonably be

ንዋዮችን ለመሸጥ፣ ለመግዛት ወይም ለመለዋወጥ የሚደረጉ ጥሪዎች ወይም ግብዣዎች በቋሚነት የሚደረጉበት፤

ሐ) የተወሰኑ ሰዎች፣ ወይም የተወሰነ መደብ ሰዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመሸጥ፣ ለመግዛት፣ ወይም ለመለዋወጥ ስለሚያቀረቡት ዋጋ ወይም በምክንያታዊነት ያቀርባሉ ተብሎ ስለሚጠበቅበት የሽያጭ ዋጋ፣ ወይም በልዋጭ ስለሚሰጡበት ዋጋ መረጃ በቋሚነት የሚሰጥበት ቦታ፤ ወይም

መ) በገበያው ላይ ግብይት ስለተደረገባቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ክፍያ የመፈጸም ስራ የሚሰራበት፤ ቦታ ነው፤

፷፰/ ‹‹**ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ማበደር**›› ማለት ተመሳሳይ ቁጥር ያለውን ያንኑ ዓይነት ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ወደፊት ባለ ቀን መልሶ ከማስረከብ ግዴታ ጋር በመልሶ የመግዛት ስምምነት እና በመሸጥና መልሶ በመግዛት ስምምነት ዓይነት በአጠቃላይ ጥሬ ገንዘብን ወይም ቢያንስ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸውን ሌሎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በዋስትና በማስያዝ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በጊዜያዊነት መለዋወጥ ነው፤

፷፱/ ‹‹**ለማይሸጡ ሰነዶች የግብይት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መፍጠር**›› ማለት ሀብትን ለአንድ ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋም ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በውሰት ለመስጠት መዘጋጀት ሲሆን ይህም፡-

ሀ) ለሽያጩ፣ ለማስተላለፉ ወይም ለምደባው ዋጋ የሚከፈለው በባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋሙ ወይም በሌላ ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋም በሚወጡ የዕዳ ሰነዶች ወይም የዕዳ ሰነድ ክፍልፋዮች ሲሆን፣ እና

expected to result, whether directly or indirectly, in the making or acceptance of offers to sell, purchase or exchange securities;

c) information is regularly provided concerning the prices at which, or the consideration for which, particular persons or particular classes of persons, propose, or may reasonably be expected, to sell, purchase or exchange securities; or

d) clearing service for securities traded in the exchange takes place;

68/ **"Securities Lending"** means the temporary exchange of securities which requires collateral generally in cash or other securities of at least an equivalent value, with an obligation to redeliver a like quantity of the same securities on a future date and is in the nature of a securities loan, a repurchase agreement and a sell-buy back agreement;

69/ **"Securitization Transaction"** means an arrangement that involves the sale, transfer or assignment of assets to a special purpose vehicle where

a) such sale, transfer or assignment is funded by the debentures or units of debentures issued by that special purpose vehicle or another special purpose vehicle; and

https://ethiodata.et/

ለ) ለዕዳ ሰነዶቹ ወይም ለዕዳ ሰነድ ክፍልፋዮቹ የሚከፈለው ክፍያ በዋናነት የሚገኘው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሀብቱን ከሚያስገኙት የገንዘብ ፍሰት ሲሆን ነው፤

፸/ ‹‹**ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት**›› ማለት የራሱን አባላቶች ፍትሃዊና ሀቀኛ እንዲሆኑ እንዲሁም በካፒታል ገበያው ቀልጣፋ አሰራር እንዲሰፍን እና የኢንቬስተሮች እና የህብረተሰቡ ጥቅም እንዲከበር ለማድረግ አባላቱ እንዲከተሉ የሚገባቸውን የስነ-ምግባር ውስጠ-ደንቦች አውጥቶ በአባላቱ ቁጥጥር እንዲያደርግ በዚህ አዋጅ መሠረት እውቅና የተሰጠው ተቋም ነው፤

፸፩/ ‹‹**ከፍተኛ ባለሙያ**›› ማለት ለቅጥሩ ወይም ለሹመቱ የባለስልጣኑ ስምምነት ወይም ቅደመ-ይሁንታ የሚያስፈልገው የባለፈቃድ ድርጅት ከፍተኛ የስራ አስፈጻሚ ወይም ሰራተኛ ነው፤

፸፪/ ‹‹**አክሲዮን**›› ማለት በአክሲዮን ኩባንያ ላይ ያለ የባለቤትነት ጥቅም ወይም በጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያለ የጥቅም ወይም የድርሻ መጠን ነው፤

፸፫/ ‹‹**ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋም**›› ማለት፡-

ሀ) ለማንኛቸውም በሃብት የተደገፈ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባለቤቶች ለሆኑ ሰዎች የሚከፈሉ ክፍያዎችን የሚያስገኙ ሀብቶችን እንደ ባለቤት ወይም እንደ አላባ ተጠቃሚ ለመያዝ፤ እና/ወይም

ለ) በሃብት የተደገፈ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለማውጣትና ለመሸጥ ብቻ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤

b) payments in respect of such debentures or units of debentures are or will be principally derived, directly or indirectly, from the cash flows generated by the assets;

70/ **“Self-Regulatory Organization”** means an entity that is recognized under this Proclamation to regulate its own members through the adoption and enforcement of rules of conduct for fair, ethical, and efficient practices in the capital market; with a view to promoting the protection of investors and the public interest;

71/ **“Senior Personnel”** means senior executive or any employee of a licensed person whose appointment requires consent or prior approval of the Authority;

72/ **“Share”** means a portion of ownership interest in a share company, or an interest or stake in any collective investment scheme;

73/ **“Special Purpose Institution”** means an entity that is established solely in order to do either or both of the following:

a) hold (whether as a legal or equitable owner) the assets from which payments to holders of any asset-backed securities are or will be primarily derived; and/or

b) issue any asset-backed securities.

https://ethiodata.et/

፸፬/ **‹‹ተቀጥላ የሆነ ኩባንያ››** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሌላ ኩባንያ ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ስር ያለ ኩባንያ ነው፤

፸፭/ **‹‹በውክልና ሻጭ››** ማለት ማንኛውም አውጪው ያወጣቸውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በአውጪው ስም ለሽያጭ ለማቅረብ ወይም ለመሸጥ በማሰብ ከአውጪው የሚገዛ ወይም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በውክልና የመሸጥ ተግባር ውስጥ የሚሳተፍ ወይም ተሳትፎ ያለው ሰው ነው፤

፸፮/ **‹‹የዋስትና ሰነድ››** ማለት ማንኛውም በዋስትና ሰነድ የተደገፈ ቢሆንም ባይሆንም አክሲዮኖችን ወይም የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት መብት የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

፸፯/ **‹‹ሰው››** ማለት የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ሰው ማለት ነው፤

፸፰/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠ አገላለጽ ሁሉ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

ክፍል ሁለት
የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

፫. የካፒታል ገበያ ባለስልጣን መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን (ከዚህ በኋላ ‹‹ባለስልጣኑ›› እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ባለስልጣኑ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል፡፡

፫/ ባለስልጣኑ የሚከተሉትን ተግባራት ለመፈጸም የሕግ አቅም ይኖረዋል፦

ሀ) የመክሰስ እና የመከሰስ፤

74/ **"Subsidiary Company"** means any company which is owned or controlled directly or indirectly by another company;

75/ **"Underwriter"** means any person who has purchased from an issuer with a view to, or offers or sells on behalf of the issuer in connection with, the distribution of any security, or participates or has a participation in the direct or indirect underwriting of any such undertaking;

76/ **"Warrant"** means any right, whether, conferred by warrant or otherwise, to subscribe for shares or debt securities;

77/ **"Person"** means a physical or juridical person;

78/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

PART TWO
CAPITAL MARKET AUTHORITY

3. Establishment of the Capital Market Authority

1/ The Ethiopian Capital Market Authority (hereinafter "the Authority") is hereby established as an autonomous Federal Government Regulatory Authority with its own juridical personality.

2/ The Authority shall be accountable to the Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

3/ The Authority shall have the capacity to:

a) sue and be sued;

https://ethiodata.et/

ለ) የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት የመግዛት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ በይዞታው ስር የማስገባት፣ የማስያዝ፣ ወይም የማስተላለፍ፤

ሐ) ውል የመዋዋል፤ እና

መ) በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባራት ለመፈጸም የሚያስፈልጉትንና አንድ ራሱን የቻለ የመንግስት አካል ሊፈጽማቸው የሚችላቸው ሌሎች ማናቸውም ተግባራት የማከናወን፡፡

b) purchase or otherwise acquire, hold, charge and dispose of both movable and immovable property;

c) enter into contracts; and

d) perform all such other things or acts necessary for the proper performance of its functions under this Proclamation which may lawfully be done by autonomous government organ.

፬. ዋና መስሪያ ቤት

የባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

4. Head Office

The Head Office of the Authority shall be in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as deemed necessary.

፭. የባለስልጣኑ ዓላማ

ባለስልጣኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዓላማዎች ኖሩታል፡-

፩/ ኢንቨስተሮችን መጠበቅ ወይም ከለላ መስጠት፤

፪/ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የማውጣት እና የግብይት ስራ ስርዓት፣ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ እና ግልጽነት በሰፈነበት ሁኔታ የሚካሄድበትን የተሟላ የካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳር እንዲኖር ማድረግ፤

፫/ የካፒታል ገበያው ተአማኒ እንዲሆን በማድረግ መዋቅራዊ የአደጋ ስጋቶችን መቀነስ፤ እና

፬/ የረጅም ጊዜ ኢንቬስትመንቶችን የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የካፒታል ገበያን ማስፋፋት፡፡

5. Objective of the Authority

The principal objectives of the Authority shall be to:

1/ Protect investors;

2/ Ensure the existence of a capital market environment in which securities can be issued and traded in an orderly, fair, efficient and transparent manner;

3/ Reduce systemic risk by ensuring the integrity of the capital market and transactions; and

4/ Promote the development of the capital market by creating enabling environment for long term investments.

፮. የባለስልጣኑ ስልጣን እና ተግባራት

ባለስልጣኑ የተቀመጡለትን ዓላማዎች ለማሳካት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

6. Powers and Duties of the Authority

For the purpose of carrying out its objectives, the Authority shall have the following powers and duties:

፩/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ የተዛማጅ ገበያ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ፣ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ፣ ያልተማከሉ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አገልግሎቶችን ወይም ሌሎች ባለስልጣኑ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ቁጥጥር የሚደረግባቸው አገልግሎቶች ናቸው ብሎ የወሰናቸውን ተግባራት ለማከናወን ለሚፈልጉ ሰዎች ፈቃድ ይሰጣል፡፡

፪/ የአገልግሎቱን ወጪዎች ለመሸፈን የሚያስፈልገውን ወይም ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች መከፈል ያለበትን ተመጣጣኝ ዋጋ ተመን ይወስናል፣ ከካፒታል ገበያ ተዋናዮች ላይ ይሰበስባል፡፡

፫/ ፈቃድ በተሰጣቸው አገልግሎት ሰጪዎች ወይም በሌሎች የገበያው ተሳታፊዎች በሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል ትስስር እንዲፈጠር የሚያደርግ የመረጃ ቴክኖሎጂ አውታሮችን በማበልጸግ የሚከተሉት ተግባራት ይፈፀማል፡-

ሀ) በተለያዩ አውታሮች ውስጥ እና በአውታሮች መካከል የገበያ መረጃ እንዲተላለፍ እና እንዲሰራጭ በማድረግ ለብዙሀኑ ተጠቃሚዎች መረጃ እንዲዳረስ ያደርጋል፤

ለ) ፈቃድ በተሰጣቸው ሰዎች ለሽያጭ የሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወይም አገልግሎቶችን በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚቀርቡበትን፣ የሚዳረሱበትን ወይም የሚተላለፉበትን መንገድ ያመቻቻል፣ እና

ሐ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግብይቶች የግብይቱ ተሳታፊዎች በአንድ ቦታ በአካል መገናኘት ሳያስፈልጋቸው እንዲፈጸሙ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፡፡

1/ Grant license to any person to operate as a securities exchange, derivatives exchange, securities depository and clearing company, capital market services provider, over-the-counter trading facility or any other activity deemed by the Authority as a regulated activity under its jurisdiction.

2/ Determine and collect reasonable levies and fees from capital market participants for its services or to cover the cost of its operations.

3/ Develop a framework to facilitate the use of information technology to effect linkages among functions provided by licensed persons or other market participants to allow:

a) the transfer and dissemination of market information to a wider number of users within and between networks;

b) the offer, distribution or delivery in electronic form of securities or services ordinarily provided by licensed persons; and

c) the execution of securities transactions without the need for parties to the transaction to be physically present at the same location.

፬/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲከስር ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን መከላከያ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ እንዲሁም የገበያ አገናኞች የገቡባቸውን ግዴታዎች መወጣት ሊሳናቸው የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች በመገምገም ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡

፭/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ሲጣሱ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወስዳል፡-

ሀ) የጥፋቶችን ክብደት ወይም ግዝፈት በማመዛዘን የተመጣጣኝነት መርህን መሠረት አድርጎ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሚፈጸሙ ጥፋቶች የገንዘብ መቀጮ ይጥላል፤

ለ) በማንኛውም ሰው የተፈጸመ የሕገ-ወጥ ድርጊትን አስተዳደራዊ የምርመራ ውጤት ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠን የንግድ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤ ወይም

መ) በተሠጠው ስልጣን መሠረት በየጊዜው የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ተከትሎ ሌሎች ማናቸውም አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

፮/ በስራ ቦታቸው ላይ በመገኘት ወይም ከስራ ቦታቸው ውጭ፣ ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ወይም ሳይሰጥ፡-

ሀ) በሁሉም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች እና ፈቃድ በተሰጣቸው ሰዎች ላይ እንዲሁም ማናቸውም አስፈላጊ የሆኑ መዝገቦቻቸው እና ሪኮርዶቻቸው ላይ፤ እና

4/ Develop plans for dealing with the eventuality of a licensed person's failures as well as an early warning system about potential defaults by market intermediaries.

5/ Take the following administrative measures for the breach of the provisions of this Proclamation or the Regulations or Directives made thereunder:

a) levying of financial penalties pursuant to a Directive that will be issued by the Authority with a principle of proportionality to the gravity or severity of the breach;

b) publishing administrative findings of malfeasance by any person;

c) suspending or cancelling licenses or authorizations or approvals granted under this Proclamation; or

d) any other administrative measures the Authority may determine by a directive, from time to time, in line with its mandate

6/ Conduct off-site surveillance activities and onsite inspections, with or without prior notice:

a) of all securities markets and licensed persons' activities, with access to all necessary books and records; and

https://ethiodata.et/

ለ) በማናቸውም ግብይቶች እና ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች በሚነግዷቸው ወይም ለሕዝብ በሚሸጧቸው ገንዘብ ነክ ሰነዶች ሁሉ ላይ

ቅኝት እና ምርመራ ያደርጋል፡፡

፯/ በስራ ቦታ በመገኘት የሚያደርገውን አስተዳደራዊ ምርመራ ወይም ከስራ ቦታ ዉጭ የሚያደርገውን ቅኝት ለማከናወን እንዲረዳዉ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ከራሱ ሰራተኞች በተጨማሪ የፖሊስ ሰራዊትን፣ ዐቃቤ ህግን እና ኦዲተሮችን ሊጠቀም ይችላል፡፡

፰/ በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠውን የማንኛውንም ሰው እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዩቹን በተፈቀደ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ለሕዝብ ያቀረበ ወይም የተገበያየ ማናቸውንም የሕዝብ ኩባንያ የውስጥ ጉዳይ ይመረምራል ወይም መመሪያ ይሰጣል፡፡

፱/ ፈቃድ የተሰጣቸው እና ይሁንታ ያገኙ የገበያ ተዋናዮችን የውጭ ኦዲተር ሹመት ያፀድቃል፡፡

፲/ የማናቸውንም ፈቃድ የተሰጣቸው እና ይሁንታ ያገኙ የገበያ ተዋናዮችን ገንዘብ ነክ የስራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ልዩ ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ልዩ ምርመራ የሚያደርጉ የውጭ ኦዲተሮችን በኦዲት ተደራጊው የገበያ ተዋናይ ወጪ ቀጥሮ ኦዲት ማስደረግ ይችላል፡፡

፲፩/ የካሳ ፈንድ በአግባቡ እንዲመራ ያመቻቻል፣ እንዲሁም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የውል ግዴታውን ባለመወጣቱ የገንዘብ ጉዳት ለሚደርስበት ኢንቬስተር ካሳ ይከፍላል፡፡

b) over any transactions and financial instruments traded by licensed persons or sold to the public.

7/ In order to carry out its on-sight inspections or off-site surveillance, the Authority may use, in addition to its staff, police officers, prosecutors, and auditors.

8/ Inquire into the affairs of or give directions to any person to which the Authority has granted a license and any public company the securities of which are publicly offered or traded on an approved securities exchange or on an over the counter market.

9/ Approve the appointment of external auditors of licensed and authorized market participants.

10/ Appoint an external auditor to carry out a specific audit of the financial operations of any licensed and authorized market participants, when such an audit is necessary, at the expense of such market participants.

11/ Facilitate the management of a compensation fund and grant compensation to any investor who suffers pecuniary loss resulting from the failure of a capital market service provider or securities exchange to meet his contractual obligations.

፲፪/ ማንኛውም በድርጊቱ ወይም ማድረግ ያለበትን ባለመፈጸሙ ምክንያት ከካሳ ፈንዱ ላይ ገንዘብ ወጪ ተደርጎ እንዲከፈል ያስደረገ ሰው ላይ ክስ ያቀርባል፡፡

፲፫/ ራስን በራስ ለሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እውቅና ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፡፡

፲፬/ የገበያ ቅኝት መርሃ ግብር በማዘጋጀት በሰነድ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ በሚካሄደው ግብይት ላይ ወይም የግብይት ስርዓት ላይ የለት ተለት ቅኝት ማድረግን ጨምሮ ገበያውን በበላይነት በመቆጣጠር፡-

ሀ) የገበያ አገናኞችን አሰራር በቅርበት ይከታተላል፤

ለ) በግብይት ስርዓቱ ላይ በሚደረግ ቅኝት አማካኝነት የተሰበሰበን ማስረጃ ያደራጃል፤ እንዲሁም ይተነትናል፤ እና

ሐ) ከገበያ ተአማኒነት፣ ከገበያ ቅኝት፣ ስጋቶችን በቅርበት ከመከታተል እና ለስጋቶች ምላሽ ከመስጠት አቅም ጋር በተገናኘ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ያለበትን ኃላፊነቶች መወጣቱን ያጣራል፡፡

፲፭/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚያከናውነው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ወይም የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በኤሌትሮኒክ የግብይት መድረኮች የሚካሄድበትን አግባብ ይቆጣጠራል፡፡

፲፮/ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች የሚደረጉ ድንበር ዘለል ተግባራትን ለመቆጣጠር እና በገንዘብ ስርዓቱ ላይ መዋቅራዊ አደጋዎች እንዳይከሰቱ ለመከላከል ከሌሎች ተቆጣጣሪ አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል ወይም የጋራ ትብብር ስምምነት ውስጥ ይገባል፡፡

12/ Have recourse against any person whose act or omission has resulted in a payment from the compensation fund.

13/ Give recognition to and oversee the activities of self-regulatory organizations.

14/ Be in charge of the surveillance of the market, including with the oversight of day-to-day trading activity on the exchange or trading system through a market surveillance program with the aim to:

a) monitor the conduct of market intermediaries;

b) collect and analyse information gathered through market surveillance; and

c) verify compliance by the exchange with its responsibilities related to market integrity, market surveillance, the monitoring of risks and the ability to respond to such risks.

15/ Regulate the use of electronic trading platforms for dealing in securities or services ordinarily carried out by a licensed person.

16/ Co-operate or enter into agreements for mutual co-operation with other regulatory authorities to regulate cross-border activities in capital markets and address systemic risk in the financial system.

https://ethiodata.et/

፲፯/ በመጀመሪያ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ገበያዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሽያጭ የሚቀርቡበትንና በኋላም የሚግበያዩበትን ሁኔታ ይቆጣጠራል እንዲሁም ይከታተላል፡፡

፲፰/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መመዝገብ እና ከምዝገባ መሰረዝ በበላይነት ይከታተላል፡፡

፲፱/ በቂ ምክንያት ሲኖር አስተዳደራዊ ምርመራዎችን ያደርጋል፤ እንዲሁም በቁጥጥር ሥራ ሂደት ከማንኛውም በሚመረመረው ጉዳይ ላይ ተሳትፎ ካለው ወይም በሚመረመረው ጉዳይ ላይ መረጃ ሊሰጥ ከሚችል ሰው፣ ቁጥጥር ከሚደረግበት ወይም ከማይደረግበት ሦስተኛ ወገን ተቋም ወይም ግለሰብ ዳታን፣ መረጃን፣ የጽሁፍ ሰነዶችን፣ መዝገቦችን እና ሪከርዶችን እና በፈቃደኝነት የሚሰጡ የምስክርነት ቃሎችን ይቀበላል፡፡

፳/ ይህን አዋጅ በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በፖሊስ እና በዐቃቤ ህግ ውጤታማ የሆነ የምርመራ እና የክስ ሥራ ማከናወን እንዲቻል ከፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እና ከፖሊስ ተቋም ጋር የቅርብ ትብብርና ቅንጅት ይፈጥራል፡፡

፳፩/ በካፒታል ገበያው ላይ በተፈጸሙ የማጭበርበር ድርጊቶች የተገኙ ገቢዎችን ለማስመለስ አዳጋች እንደሚሆን የሚያሰጋ ሁኔታ ለመኖሩ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ባለስልጣኑ ፋይናንስ ተቋማት ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማዘዝ ይችላል፡-

ሀ) የካፒታል ገበያው ተዋናይ ወይም የተዋናዩ ስራ አስፈጻሚ ሂሳብ እንዲታገድ፤

ለ) በፋይናንስ ተቋሙ ውስጥ ባለ በጥንቃቄ የሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ የተቀመጠ ማንኛውም የካፒታል ገበያ

17/ Regulate and oversee the issue, and subsequent trading, both in primary and secondary markets, of securities.

18/ Supervise the listing and delisting of securities.

19/ With a good cause, conduct administrative investigation and obtain data, information, documents, books and records, and voluntary statements or testimony from any person, including third party entities and individuals, whether regulated or unregulated, that are either involved in relevant conduct or who may have information relevant to a regulatory or enforcement investigation.

20/ Closely collaborate and coordinate with the Federal Attorney General and Federal Police to enable them investigate and prosecute offenses committed in violation of this Proclamation.

21/ When there is reasonable cause to believe that recovery of gains from fraudulent activities will be impeded, issue administrative order on a financial institution requiring the financial institution to do one or more of the following:

a) to block the accounts of the capital market participant or any one of its officers;

b) freeze access to any cash, valuables, precious metals, or other assets of the participant, in a safe deposit box

ተዋናዩ ጥሬ ገንዘብ፣ውድ እቃ፣ የከበረ ጌጣጌጥ፣ ወይም ሌላ ንብረት እንዳይንቀሳቀስ፤ እና

ሐ) በጥንቃቄ በሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ ስለሚገኙ ሀብቶች ተገቢውን መረጃ ለባለሥልጣኑ እንዲሰጥ፡፡

፳፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፳፩ መሰረት ባለስልጣኑ ለፋይናንስ ተቋሙ የማገጃ ትዕዛዝ በደረሰው በ፲ (አስር) ቀናት ጊዜ ውስጥ እገዳው እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማግኘት አለበት፡፡

፳፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፳፪ ላይ በተመለከተው አግባብ የእግድ ትእዛዝ ከፍርድ ቤት ካልመጣ እገዳው እንደጸና እግድ አይቆጠርም፡፡

፳፬/ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ለሕዝብ ወይም ለተወሰነ የሕበረተሰብ ክፍል ያቀረበን ኩባንያ መልካም አስተዳደር በተመለከተ ማስታወቂያዎችን እና የአሰራር መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

፳፭/ ግልጽ፣ ሚዛናዊ፣ ፍትሃዊ እና ወጥነት ያላቸውን የአሰራር ሥርዓት አውጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፳፮/ የኢንቬስተሮችን ስልጠና እና ንቃት ያሳድጋል፡፡

፳፯/ ለኢንቬስተሮች ተገቢውን ጥበቃ ለማድረግ የገበያውን ፍትሃዊነት፣ዉጤታማነት እና ግልጽነት ለማረጋገጥ እና ሌሎች የገበያ ስጋቶችን ለማስወገድ እንዲያስችለው ሰነዶችን፣ ገበያዎችን፣ የገበያ ተዋናዮችን እና ተግባሮቻቸውን በየጊዜው ይገመግማል፡፡

፳፰/ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች መካከል የሚፈጠርን የጥቅም ግጭት እና በማትጊያ ክፍያዎችና

held by the financial institution; and

c) provide information relating to the accounts or contents of the safe deposit box.

22/ To sustain the order under Sub-Article (21) of this Article, the Authority shall obtain a court authorization for the order within 10 (Ten) days of service of the notice of the order on the financial institution.

23/ If there is no court authorization of the order obtained within 10 (Ten) days of service of notice of the order under Sub-Article (22) of this Article, the order shall lapse.

24/ Prescribe notices or guidelines on corporate governance of a company whose securities have been issued to the public or a section of the public.

25/ Implement transparent, fair, equitable and consistent operational procedures.

26/ Promote investor education.

27/ Conduct a regular review of products, markets, market participants and activities to identify and assess possible risks to investor protection and market fairness, efficiency and transparency or other risks to financial markets.

28/ Ensure that conflicts of interest among regulated capital market service providers and misalignment of incentives

በሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል የሚከሰትን ያለመጣጣም ይለያል፣ ይከላከላል፣ ያስወግዳል፣ ይፋ ያደርጋል፣ ወይም ይቆጣጠራል፡፡

፳፱/ ተለዋዋጭ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን፣ እየተፈጠሩ ያሉ አዳዲስ ስጋቶችን፣ እንዲሁም የቁጥጥር ስርዓቱን መሻሻል አስፈላጊነትን ለመዳሰስና ለመለየት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የቁጥጥር ወሰን በየጊዜው ይገመግማል፡፡

፴/ ዓላማዉን ለማሳካት እና ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

፯. የባለስልጣኑ አቋም

ባለስልጣኑ፡-

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ (ከዚህ በኋላ ‹‹ቦርዱ›› እየተባለ የሚጠራ)፣

፪/ ዋና ዳይሬክተር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እንዲሁም

፫/ አስፈላጊ ሰራተኞች

ይኖሩታል፡፡

፰. የቦርዱ አባላት ስብጥር እና አመዳደብ

፩/ ቦርዱ ከሚከተሉት አካላት የተውጣጣ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ— ቋሚ አባል፤

ለ) የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ዋና ዳይሬክተር— ቋሚ አባል፤

ሐ) ሌሎች በዘርፉ ሙያዊ ብቃት ያላቸው አራት ሰዎች— አባል፤ እና

መ) የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር— ያለ ድምፅ የሚሳተፍ አባል፡፡

are identified, avoided, eliminated, disclosed or otherwise managed.

29/ Regularly review the perimeters of securities regulations in order to identify and assess evidence of changing circumstances and emerging risks and the need for revisions of regulatory framework.

30/ Do all such other acts as may be incidental or conducive to the attainment of the objectives of the Authority or the exercise of its powers under this Proclamation.

7. Organisational Structure of the Authority

The Authority shall have:

1/ Board of Directors (hereinafter the “Board”);

2/ A Director General and deputy Director Generals as necessary; and

3/ The necessary staff.

8. Composition and Appointment of Board of Directors

1/ The Board shall have seven members, consisting of:

a) The Governor of the National Bank of Ethiopia— permanent ex-officio member;

b) The Director of the Accounting and Audit Board of Ethiopia— permanent ex-officio member;

c) Four other individuals to be appointed based on qualification— members; and

d) The Director General of the Authority— non-voting member.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) የተጠቀሱት የቦርድ አባላት የሚሾሙት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

፫/ የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላቶቹ መካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሾማል፤ ሆኖም ግን ዋና ዳይሬክተሩ የቦርዱ ሰብሳቢ መሆን አይችልም፡፡

፬/ የቦርዱ ሰብሳቢ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) የተጠቀሱት የቦርድ አባላት የሚመረጡት በሕግ፣ በፋይናንስ፣ በምጣኔ ሀብት፣ በስራ አመራር እና ተያያዥ የሙያ ዘርፎች ልምድና የሙያ ብቃት ካላቸው ሰዎች መካከል ይሆናል፡፡

፭/ ቦርዱ ዋና ዳይሬክተሩ የማይገባበትና ቢያንስ ሦስት አባላቱን ያካተተ የኦዲት ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

፮/ ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ኮሚቴዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

፯/ የቦርድ አባላቱ የስራ ዋጋ እና አበል መንግስት በሚወስነው መሠረት ከባለስልጣኑ ጠቅላላ ፈንድ ላይ የሚከፈል ይሆናል፡፡

፱. **የጥቅም ግጭት**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) የተጠቀሱት የቦርድ አባላት የጥቅም ግጭት ውስጥ የሚያስገቧቸውን ሌሎች ኃላፊነቶች ሊቀበሉ አይችሉም፡፡

፪/ የቦርድ አባላት የጥቅም ግጭት ውስጥ በሚያስገቧቸው ጉዳዮች ላይ ድምጽ ከመስጠት ራሳቸውን በራሳቸው ማግለል አለባቸው፡፡

2/ Members of the Board under Sub-Article (1) (c) of this Article shall be appointed by the Prime Minister.

3/ The Chairperson of the Board shall be appointed by the Prime Minister amongst the Board members; however, the Director General may not be a Chairperson.

4/ The Chairperson and every member of the Board appointed under Sub-Article (1) (c) of this Article shall be appointed from amongst persons who have experience and expertise in legal, finance, economics, management, or related disciplines.

5/ The Board shall have an Audit Committee composed of at least three Board members, excluding the Director General.

6/ The Board may have other committees as needed.

7/ The members of the Board shall be paid such remuneration and allowances out of the general fund of the Authority as may be determined by the Government.

9. **Conflicts of Interest**

1/ Members of the Board under Article (8), Sub-Article (1)(c) of this Proclamation may not hold other positions that may cause conflict of interests.

2/ Members of the Board shall recuse themselves from participating and voting in matters which may have conflict of interests.

፲. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን

፩/ የቦርዱ ሰብሳቢ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) የተጠቀሱት የቦርድ አባላት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፣ የቦርዱ አባላት የአገልግሎት የስራ ዘመን ለሌላ አምስት ዓመት ሊራዘም ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ቢኖርም፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) መሠረት ከሚሰየሙ የመጀመሪያው ዙር ቦርድ አባላት መካከል የሁለቱ አባላት የሥራ ዘመን ስድስት ዓመት ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሰረት የስራ ዘመናቸው ስድስት ዓመት የሚሆነው የቦርድ አባላት እነማን እንደሆኑ ለሹመት በሚቀርቡበት ጊዜ ይወሰናል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የሥራ ዘመናቸው ስድስት ዓመት የሆኑ የቦርዱ አባላት የአገልግሎት ዘመናቸው ሊራዘም አይችልም፡፡

፲፩. የቦርዱ አባላት ከሀላፊነት ስለመነሳት ወይም ስለመልቀቅ

፩/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) መሠረት የተሾመ የቦርድ አባል ከሀላፊነቱ የሚነሳው ወይም የሚለቀው፡-

ሀ) ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የመልቀቂያ ጥያቄ ሲያቀርብ እና የመልቀቂያ ጥያቄው ተቀባይነት ሲያገኝ፤

ለ) በአእምሮ ሕመም ወይም በአካል ሕመም ምክንያት የመስራት አቅም ሲያጣ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ኃላፊነቱን

10. Tenure of Board Members

1/ The tenure of the Chairperson and every member of the Board appointed under Article (8), Sub-Article (1)(c) of this Proclamation shall be five years.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the tenure of Board members may be renewed for an additional term of five years.

3/ Notwithstanding Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the tenure of two Board members appointed under Article 8, Sub-Article (1)(c) of this Proclamation for the first round shall be six years.

4/ The specific Board members whose tenure will be six years under Sub-Article (3) of this Article shall be determined at the time of their appointment.

5/ The tenure of Board members who will be appointed for six years under Sub-Article (3) of this Article may not be renewed for an additional term.

11. Removal or Resignation of Board Members

1/ Any member of the Board appointed under Article (8), Sub-Article (1)(c) of this Proclamation shall be removed from office if he፡

a) delivers to the Prime Minister a written resignation of his appointment, and his request for resignation is accepted by the Prime Minister;

b) is found to be incapacitated by mental or physical illness or is

ለመወጣት የማይችል ወይም የማይበቃ ሲሆን ወይም በአባልነት መቀጠል የማይችል ከሆነ፤

ሐ) ፈቃድ ሳይሰጠው ወይም በቂ ምክንያት ሳይኖረው ከሦስት በላይ በሆኑ ተከታታይ የቦርዱ ስብሰባዎች ሳይገኝ ከቀረ፤

መ) የመክሰር ውሳኔ የተወሰነበት ከሆነ ወይም ከባለገንዘቦቹ ጋር የመጠባበቂያ ስምምነት ውስጥ ከገባ፣

ሠ) ስድስት ወር ወይም ከዚያ የሚበልጥ የእስር ውሳኔ በፍርድ ቤት የተላለፈበት ከሆነ፤ ወይም

ረ) ከእምነት ማጉደል፣ ከማታለል ወይም ከስነምግባር ንቅዘት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠበት ነዉ፡፡

፪/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) መሠረት የተሾመ የቦርድ አባል የስራ ዘመኑን ሳያጠናቅቅ ከኃላፊነቱ የተነሳ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተሰናባቹ የቦርድ አባል ሳያጠናቅቅ የቀረውን የስራ ዘመን የሚያጠናቅቅ ተተኪ የቦርድ አባል ይሾማል፡፡

፫/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) መሠረት የተሾመ የቦርድ አባል ለተወሰነ ጊዜ ኃላፊነቱን መወጣት የማይችልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አባሉ ለማይኖርበት ለተወሰነው ጊዜ ሌላ የቦርድ አባል ይሾማል፡፡

፲፪ . <u>የቦርዱ ስልጣን እና ተግባራት</u>

፩/ ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት አሉት፡-

ሀ) በባለስልጣኑ የሚወጡ መመሪያዎችን ማጽደቅ፤

otherwise unable or unfit to discharge the functions of a member or is unable to continue as a member;

c) has been absent from three consecutive meetings of the Board of Directors of the Authority without leave or good cause;

d) is adjudged bankrupt or enters into a composition scheme or arrangement with his creditors;

e) is sentenced by a court to imprisonment for a term of six months or more; or

f) is convicted of an offence involving dishonesty, fraud or moral turpitude.

2/ In the event that the office is vacated by any member appointed under Article (8), Sub-Article (1)(c) of this Proclamation, the Prime Minister shall appoint another person to hold office until the expiry of the term of the member in whose place he is appointed.

3/ If any member of the Board appointed under Article (8), Sub-Article (1)(c) of this Proclamation is temporarily unable to perform his duties, the Prime Minister shall appoint another person to act in his place during the period of his absence.

12. <u>Powers and Duties of the Board</u>

1/ The Board shall have the following powers and duties:

a) approve directives to be issued by the Authority;

https://ethiodata.et/

ለ) የባለስልጣኑን በጀት ማጽደቅ፣

ሐ) የባለስልጣኑን እስትራቴጅያዊ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የስራ መርሐ-ግብሮችን እና የስራ አፈጻጸም ሪፖርት መገምገም፣

መ) በዋና ዳይሬክተሩ በሚቀርብ የውሳኔ ሀሳብ መሠረት የባለስልጣኑን የሰራተኞች የደሞዝ እና የጥቅማጥቅም መዋቅር ማጽደቅ፣

ሠ) የባለስልጣኑን ስልጣንና ተግባር በበላይነት መምራት፣

ረ) የባለስልጣኑን ሂሳቦች የሚመረምሩ የዉጭ ኦዲተሮችን መሾም፣ እና

ሸ) ባለስልጣኑ በውክልና ለሌሎች የሚሰጣቸውን ስልጣኖች እና ኃላፊነቶች ማጽደቅ፡፡

፪/ የቦርዱ ኦዲት ኮሚቴ የውስጥ እና የውጭ ኦዲተሮች የሚያቀርቡትን ሪፖርቶች ግኝቶች እና የውሳኔ ሀሳቦች ተቀብሎ ይመረምራል፣ እንዲሁም ለአፈጻጸሙም አስፈላጊ ትዕዛዞችን ይሰጣል፡፡

፲፫. የቦርዱ የስብሰባ ስነ-ሥርዓት

፩/ ከቦርዱ አባላት አራቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ይሟላል፡፡

፪/ ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ይሁን እንጂ የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ሰብሳቢው ከሌለ እሱ የወከለው ሰው በማንኛውም ጊዜ ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ወይም ከአባላቱ ሦስቱ ስብሰባ እንዲደረግ ከጠየቁ አስቸኳይ የቦርድ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

፫/ ሁሉንም የቦርድ ስብሰቦች የሚመራው ሰብሳቢው ወይም በሰብሳቢው የተወከለ ሰው ይሆናል፡፡

b) approve the budget of the Authority;

c) review the strategy, annual work program, and performance report of the Authority;

d) upon the recommendation of the Director General, approve the salary and benefit structure of employees of the Authority;

e) oversee the power and functions of the Authority;

f) appoint external auditors of the Authority; and

g) approve the delegated powers and functions of the Authority.

2/ The Board's Audit Committee shall receive and examine the findings and recommendations of the internal and external auditors and also give the necessary direction for the implementation.

13. Meeting Procedures of the Board

1/ The presence of four members of the Board shall constitute a quorum.

2/ The Board shall meet at least monthly; provided, however, that the Chairperson or, in his absence, the person delegated by him, may call urgent meetings at any time or when the Director General or three Board members so request.

3/ The Chairperson or a Board member delegated by him shall preside at every meeting of the Board.

https://ethiodata.et/

፬/ ሁሉም የቦርድ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው በተገኙት አባላት ተራ የድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡ ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

፭/ ቦርዱ የራሱ ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

፮/ የቦርዱ ስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች በትክክል መመዝገብና አያያዛቸው እና አጠባበቃቸው ቦርዱ በሚወስነው ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡

፯/ ቦርዱ ካልወሰነ በቀር የቦርድ ቃለ ጉባኤዎች ሚስጢራዊነት የተጠበቀ ይሆናል፡፡

፰/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ ስርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፬. <u>የዋና ዳይሬክተር ሹመት፣ ስልጣን እና ተግባራት</u>

፩/ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የሚሾመው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው፡፡

፪/ በዋና ዳይሬክተርነት የሚሾም ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊያሟላ ይገባል፡-

ሀ) በፋይናንስ፣ በምጣኔ ሀብት፣ በስራ አመራር፣ በሕግ ወይም ተዛማጅ የሙያ ዘርፎች በከፍተኛ የስራ አመራር ደረጃ ቢያንስ የአስር ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤ እና

ለ) በገንዘብ ነክ ጉዳዮች ወይም በካፒታል ገበያ ወይም በፋይናንስ ልዩ ብቃት ያለው፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ከምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ዉጭ ሌሎች ከፍተኛ የስራ አስፈጻሚዎችን በማጨት ቦርዱ ሹመታቸውን እንዲያጸድቅ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

4/ All decisions of the Board shall be made by a simple majority vote of the members present. In case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

5/ The Board shall have its own secretary.

6/ Minutes of meetings of the Board shall be recorded accurately and in such form as the Board may determine.

7/ Unless the Board decides otherwise, minutes of the Board shall be confidential.

8/ Notwithstanding the provisions of this Article, the Board may adopt its rules of meeting procedures.

14. <u>Appointment, Powers, and Duties of Director General</u>

1/ The Director General shall be appointed by the Prime Minister.

2/ A person appointed as a Director General shall meet the following qualifications:

a) has at least ten years' experience at a senior management level in matters relating to finance, economics, management, law or related issues; and

b) has expertise in matters relating to money or capital markets or finance.

3/ The Director General shall nominate and recommend other senior executives of the Authority, excluding deputy Director Generals, for approval to the Board.

፬/ ዋና ዳይሬክተሩ በአዋጁ መሠረት እና ቦርዱ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች መሰረት የባለስልጣኑን አስተዳደር እና የስራ ሂደት በበላይነት ይከታተላል፣ ይመራል፡፡

፭/ ዋና ዳይሬክተሩ የበለስልጣኑን የስራ ዕቅድና የዓመት በጀት ያዘጋጃል፣ በቦርዱ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፮/ ዋና ዳይሬክተሩ የባለስልጣኑ ዋና እንደራሴ ነው፣ በእንደራሴነት ስልጣኑም ቀጥለው የተመለከቱትን ያከናውናል፡-

ሀ) ባለስልጣኑ ከሌሎች ሰዎች፣ ከመንግስት፣ እና አባል ከሆነባቸው ዓለም-አቀፍ ተቋማት ጋር በሚያደርጋቸው ማንኛውም ግንኙነቶች ባለስልጣኑን ይወክላል፣

ለ) ብቻውን ወይም ከሌሎች ኃላፊነት ከተሰጣቸው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ጋር በጣምራ ባለስልጣኑ በሚገባባቸው ውሎች፣ በወቅታዊ ሪፖርቶች፣ በሂሳብ ሚዛን፣ በትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ፣ በደብዳቤ ልውውጦች እና በሌሎች የባለስልጣኑ ሰነዶች ላይ ይፈርማል፣

ሐ) ባለስልጣኑ በሚከሰስበትም ሆነ በሚከስበት ወቅት ሁሉ ራሱ ወይም በነገረ ፈጅ አማካኝነት የባለስልጣኑ ወኪል ይሆናል፣ እና

መ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የባለስልጣኑን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፯/ የባለስልጣኑን የለት ተለት ስራ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ዋና ዳይሬክተሩ ካለው ስልጣንና ኃላፊነት ላይ እንዳስፈላጊነቱ በከፊል ለምክትሎቹ ወይም ለሌሎች ሰራተኞች በውክልና ሊሠጥ ይችላል፡፡

4/ The Director General shall direct and supervise the administration and operations of the Authority in accordance with this Proclamation and the decisions of the Board.

5/ The Director General shall prepare the plans and annual budgets of the Authority and, upon approval by the Board, implement the same.

6/ The Director General shall be the principal representative of the Authority, and in this capacity shall:

a) represent the Authority in its all relations with other persons, the Government, and international bodies in which the Authority is a member;

b) sign individually or jointly with other authorized officers of the Authority contracts concluded by the Authority, periodic reports, balance sheets, profit and loss statements, correspondence and other documents of the Authority;

c) represent the Authority, either personally or through counsel, in any legal proceeding to which the Authority is a party; and

d) hire and administer employees of the Authority in accordance with a regulation issued by the Council of Ministers.

7/ The Director General may delegate part of his powers and duties to his deputies and other officers of the Authority, as may be required to ensure the business continuity of the Authority.

፲፭. ምክትል ዋና ዳይሬክተር

፩/ የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ ዋና ዳይሬክተር ሆኖ ማገልገል የሚያስችል ብቃት ያላቸው ሆነዉ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ይሆናሉ፡፡

፪/ የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ዋና ዳደሬክተሩን ያግዛሉ፤ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ የዋና ዳይሬክተሩን ስራዎች ያከናውናሉ፡፡ የተቋሙን ስራዎች በማቀድ፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፣ በዘርፍ ተለይቶ የሚሰጡዋቸውን የስራ ክፍሎች ይመራሉ፡፡

፲፮. ስልጣን እና ተግባራት በውክልና ስለመስጠት

፩/ ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ማንኛውንም ስልጣን እና ተግባራት፡-

ሀ) ለአንድ የተለየ ተልዕኮ ለተቋቋመ ኮሚቴ፤

ለ) እውቅና ለተሰጠው ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት፤ ወይም

ሐ) ለግለሰቦች

በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፪/ ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ማንኛውንም ተግባርና ኃላፊነት ውክልና በሚሰጥበት ጊዜ፣ ውክልና የተሰጠው አካል ማከናወን ስለሚችላቸው ተግባርና ሀላፊነቶች በግልፅ ለይቶ ማስቀመጥ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሰጠ ውክልና መመሪያ ለማውጣት አይሰራም፡፡

፬/ ባለስልጣኑ በማንኛውም ጊዜ የሰጠውን የውክልና ስልጣን ለመሻር ይችላል፡፡

15. Deputy Director General

1/ The deputy Director Generals of the Authority, who shall have similar qualifications to a person who is eligible to be Director General, shall be appointed by the Prime Minister.

2/ The deputy Director Generals of the Authority shall assist the Director General and, in the absence of the Director General, shall discharge all the functions conferred on the Director General.

16. Delegation of Power and Duties

1/ The Authority may delegate any of its powers and duties under this Proclamation to:

a) a committee that is established for specific purpose;

b) a recognized self- regulatory organization; or

c) a person.

2/ When delegating any of its powers and duties under this Proclamation, the Authority shall clearly state the specific duties and powers that the delegated person may exercise.

3/ A delegation made under this Article shall not include issuing directives.

4/ The Authority may, at any time, revoke a delegation under this Article.

፲፯. ለባለስልጣኑ መረጃ ስለመስጠት

፩/ ባለስልጣኑ ወይም በባለስልጣኑ የተወከለ ማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ የቁጥጥር ስልጣን ውስጥ በሚካተቱ የስራ ዘርፎች ላይ የተሰማራን ማንኛውም ሰው በጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት በማስታወቂያው በተጠቀሰው አግባብና ጊዜ ውስጥ ለባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ ለወከለው ሰው መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ የባለስልጣኑን ዓላማ ለማሳካት ካልሆነ በቀር ወይም በህግ ወይም በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በቀር ባለስልጣኑ ወይም ማንኛውም የባለስልጣኑ ሰራተኛ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተገኘን ማንኛውንም መረጃ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተገለጸው ቢኖርም ባለስልጣኑ ጥያቄ ሲቀርብለት ወይም በራሱ ተነሳሽነት ለሌሎች በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ላሉ ተቆጣጣሪ ተቋማት የሕግ ወይም የቁጥጥር ደንብ ጥሰት የፈጸመ ወይም እየፈጸመ ያለን ሰው ለይተው ሲያመለክቱ ያንን በተመለከተ የሚያደርጉትን አስተዳደራዊ ምርመራ ለማገዝ መረጃን ሊያጋራ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገዉ የመረጃ ማጋራት ተፈፃሚ የሚሆነው፡-

ሀ) ባለስልጣኑ ከመረጃ ጠያቂዉ የውጭ አቻ ተቋም ጋር የመረጃ ልውውጥ ስምምነት ካለዉ ወይም ኢትዮጵያ የገባችበት የዓለም አቀፍ ስምምነት ካለ፤ እና

17. Furnishing of Information to the uthority

1/ The Authority or any person officially authorized on its behalf may, by notice in writing, require any person engaged in activities under the Authority's jurisdiction to furnish information to the Authority or to the authorized person, in the form and within such period as is specified in the notice. Details shall be prescribed by the directives of the Authority.

2/ The Authority or any officer of the Authority shall not disclose to any person or use any information acquired under Sub-Article (1) of this Article except for the purpose of achieving the objectives of the Authority or required to do so by a court or law.

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, the Authority may share information, upon request or on unsolicited basis, with other regulatory bodies, whether established within or outside Ethiopia, for assistance in administrative investigations of a person specified by the regulatory body who has contravened or is contravening any legal or regulatory requirements.

4/ The information sharing under Sub-Article (3) of this Article shall have an effect only if:

a) the Authority has entered into information sharing agreements with such foreign counterparts or any international agreement to which Ethiopia is a party; and

https://ethiodata.et/

ለ) ምርመራው የሚደረግበት ጉዳይ ጠያቂው የውጭ ተቆጣጣሪ ተቋም የሚያስፈጽመው ወይም የሚያስተዳድረው ጉዳይ ከሆነ፤ ወይም በጠያቂው ተቋም የስልጣን ወሰን ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ

ብቻ ነው፡፡

፭/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈጻጸም ዓላማ በንዑስ አንቀጹ የተጠቀሰው የሕግ ወይም የቁጥጥር ደንብ ጥሰት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተፈጸመ የሕግ ጥሰት ተቆጥሮ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደ አግባቡ ተፈጻሚ ይደረጋሉ፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት እገዛ የሚጠይቅ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን፡-

ሀ) የተጠየቀው እገዛ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል አስፈላጊ መሆኑን፤ ወይም

ለ) የተጠየቀው እገዛ የጠያቂውን ባለስልጣን ተግባራቱን እና ግዴታዎቹን ለመወጣት እንደሚጠቅመው ማሳየት አለበት፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) ላይ የተገለጸው ቢኖርም፣ ባለስልጣኑ ለተጠየቀው እገዛ ውሳኔ ለመስጠት፡-

ሀ) እገዛውን ለማድረግ ያወጣውን ወጪ እገዛ ጠያቂው ባለስልጣን መሸፈን አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን፣ እና

ለ) ከኢትዮጵያ ተመሳሳይ የእገዛ ጥያቄ ቢቀርብለት በተራው እገዛ ለማድረግ የሚፈቅድ እና አቅም ያለው መሆን አለመሆኑን

ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

b) the issue under administrative investigation is enforced or administered by, or is under the jurisdiction of the requesting foreign regulatory body.

5/ For the purposes of Sub-Article (3) of this Article, the provisions of this Proclamation shall, mutatis mutandis, apply and have effect as if the contravention of the legal or regulatory requirement referred to in Sub-Article (3) of this Article were an offence under this Proclamation.

6/ A regulatory body which requests for assistance under Sub-Article (3) of this Article shall demonstrate that:

a) the assistance requested is in the interest of the public; or

b) the request assists the regulatory body in the discharge and performance of its functions.

7/ Notwithstanding the requirement under Sub-Article (6) of this Article, the Authority shall, in deciding whether to provide the requested assistance, take into account whether the regulatory body shall:

a) pay the Authority any of the costs and expenses incurred in providing the assistance; and

b) be able and willing to provide reciprocal assistance within its jurisdiction in response to a similar request for assistance from Ethiopia.

https://ethiodata.et/

፰/ የሚደረገው ትብብር ወይም የሚፈጸመው ቅንጅት በዚህ አዋጅ ከተመለከቱት ዓላማዎቹ ጋር የሚጻረር እስካልሆነ ድረስ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ማንኛውም ድንጋጌ ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ስልጣን ተግባራዊ ለማድረግ ከሌላ ማናቸውም ተቆጣጣሪ ተቋማት ጋር ከመተባበር ወይም ስራውን ከማቀናጀት ሊከለክለው አይችልም፡፡

፱/ የባለስልጣኑ ሰራተኞች የጥቅም ግጭትን መለየት፣ መከላከል ወይም ማሳወቅ እንዲሁም ፍትሃዊ የስነ-ስርዓት ደንቦችን መከተል አለባቸው፡፡

፲፰. የባለስልጣኑ የገንዘብ ምንጮች

፩/ የባለስልጣኑ የገንዘብ ምንጭ፡-

ሀ) በመንግስት ከሚመደብለት የማቋቋሚያ በጀት፤

ለ) ባለስልጣኑ ከሚሰጣቸው ፈቃዶች እና በዚህ አዋጅ መሰረት ከሚሰጡ ሌሎች ተግባራት ጋር በተያያዘ ከሚከፈሉ የአገልግሎት ክፍያዎች፤

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚጣሉ አስተዳዳራዊ መቀጮዎች ጋር በተያያዘ ከሚሰበሰቡ ገንዘቦች፤ እና

መ) ሌሎች በድጋፍ ከሚገኙ ገንዘቦች

የተውጣጣ ይሆናል፡፡

፪/ በአጭር ጊዜ ውስጥ የማይፈለጉ ገንዘቦችን ባለስልጣኑ በሚወስነው መሠረት በኢንቬስትመንት ላይ ያውላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የባለስልጣኑ የገንዘብ ምንጮች የባለስልጣኑን ወጪዎች ለመሸፈን የማይበቃ በሚሆንበት ጊዜ ጉድለቱ በመንግስት ከሚመደብ በጀት ይሸፈናል፡፡

8/ Nothing in this Article shall be construed to limit the powers of the Authority to cooperate or coordinate with any other regulatory body in the exercise of its powers under this Proclamation; in so far any such cooperation or coordination is not contrary to the objectives of this Proclamation.

9/ The staff of the Authority shall identify, avoid or disclose conflict of interest and observe procedural fairness.

18. Funds of the Authority

1/ The funds of the Authority shall consist of:

a) Initial budget allocated by the Government;

b) fees payable to the Authority for licenses issued and other duties performed in terms of this Proclamation;

c) such sums of money as are paid under this Proclamation as administrative fines or penalties; and

d) any other sums of money received as grant to the Authority.

2/ Funds not immediately required by the Authority may be invested in such a manner as the Authority may determine.

3/ In the instance where the Authority's funds under Sub-Article (1) of this Article falls short of covering its budget, the shortfall shall be covered by budget allocated by the Government.

https://ethiodata.et/

፲፱. የባለስልጣኑ ሂሳቦች

፩/ ባለስለጣኑ ስራዎቹ፣ ገንዘቦቹ እና ንብረቶቹ በአግባቡ ለመጠበቃቸው ተገቢ የሂሳብ መዝገቦች እና ሌሎች ሪከርዶች መያዛቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ የበጀት ዓመቱ ካበቃ በኋላ ባሉት ፫ (ሶስት) ወራት ውስጥ ባለስልጣኑ የሂሳብ ሪፖርት እና ሌሎች የስራ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት አለበት፡፡

፫/ የባለስልጣኑ የሂሳብ ሪፖርቶች አዘገጃጀት ዓለም አቀፍ የሂሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት መንገድን የተከተለ ወይም የሚመለከተው የመንግስት ባለስልጣን የሚያወጣውን ሌላ የሂሳብ አዘገጃጀት ስርዓት የተከተለ መሆን አለበት፡፡

፳. የባለስልጣኑን ሂሳቦች በውጭ ኦዲት ለማስመርመር

፩/ የባለስልጣኑ ሂሳቦች በየዓመቱ በውጭ ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

፪/ የፋይናንስ ዓመቱ ካበቃ በኋላ ባሉት ፫ (ሶስት) ወራት ውስጥ የኦዲት ሪፖርቱ ተጠናቆ ቦርዱ እንዲመረምረው እና እንዲያጸድቀው ለቦርዱ የኦዲት ኮሚቴ መቅረብ አለበት፡፡

፫/ በውጭ ኦዲተር በአግባቡ ተመርምሮ የተፈረመው የኦዲት ሪፖርት ባለስልጣኑ በሚያሳትመው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ መካተት አለበት፡፡

፳፩. የባለስልጣኑ የበጀት ዓመት

የባለስልጣኑ የበጀት ዓመት በየዓመቱ ከሐምሌ ፩ ጀምሮ ያለው ተከታታይ የአስራ ሁለት ወራት ክፍለ ጊዜ ነው፡፡

19. Accounts of the Authority

1/ The Authority shall ensure that proper accounts and other records relating to the accounts are kept in respect of all its activities, funds and property.

2/ Within 3 (three) months after the end of each year, the Authority shall prepare statement of financial accounts and all other transactions.

3/ The financial statements of the Authority shall be prepared in line with the international financial reporting standards or other frameworks as determined by a pertinent Government authority.

20. External Audit of the Authority's Accounts

1/ The accounts of the Authority shall be audited by external auditor annually.

2/ The audit report shall be completed and issued to the Board's Audit Committee for review and approval by the Board within 3 (three) months from the end of each financial year.

3/ A duly audited financial statement signed by external auditor shall be published in the annual report to be issued by the Authority.

21. Financial Year of the Authority

The financial year of the Authority shall be the period of twelve months beginning the 1st day of July of each year.

https://ethiodata.et/

ክፍል ሶስት
ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እውቅና ስለሚያገኝበት ሁኔታ

፳፪. እውቅና ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩/ በካፒታል ገበያ ባለስልጣን የቁጥጥር ስልጣን ስር የሚንቀሳቀስ እና እንደ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ዕውቅና ተሰጥቶት መስራት የሚፈልግ ተቋም በተዘጋጀው የማመልከቻ ፎርም መሠረት ለባለስልጣኑ ማመልከት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው ቢኖርም በባለስልጣኑ እውቅና የተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልገው ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሚቀርብ ማመልከቻ አመልካቹ ዕውቅና ከተሰጠው በኋላ ስለሚያከናዉናቸዉ ሥልጣንና ተግባራት መጥቀስ አለበት፡፡

፬/ ባለስልጣኑ ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት እውቅና የሚሰጠው አመልካቹ ድርጅት፡-

ሀ) ከዚህ አዋጅ፣ እና ተያያዥነት ካላቸው ደንቦችና መመሪያዎች ጋር የተጣጣመ ውስጠ-ደንቦችና ፖሊሲዎች ያሉት መሆኑን፣

ለ) የሕግና እና ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸው መመሪያዎች ጥሰት መቆጣጠርን ጨምሮ የተጣለበትን ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚያሰችል የገንዘብ አቅም እና የአስተዳደራዊ ብቃት ያለው መሆኑን፤

ሐ) ብቁ እና ተገቢ መሆኑን፤

PART THREE
RECOGNITION OF A SELF-REGULATORY ORGANIZATION

22. Application for Recognition

1/ An entity under the jurisdiction of the Capital Market Authority which intends to be recognized and operate as a self-regulatory organization shall apply to the Authority, in the prescribed form.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, an exchange and a securities depository and clearing company shall be recognized as self-regulatory organization without submitting an application.

3/ An application made under Sub-Article (1) of this Article shall specify the functions and powers that the entity is seeking to exercise upon recognition.

4/ The Authority may recognize a self-regulatory organization where it is satisfied that the organization፡

a) has internal rules and policies which are consistent with this Proclamation or related regulations and directives;

b) has the financial capacity and administrative resources necessary to carry out its functions as a self-regulatory organization, including dealing with a breach of the law or of any other applicable guidelines;

c) is fit and proper;

መ) ስራውን ለማከናወን የሚችሉ ብቃት ያላቸው ሰራተኞች ያሉት መሆኑን፣ እና

ሠ) ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚወስናቸውን ሌሎች መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን፤

ያረጋገጠ ከሆነ ነው፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የቀረበን ማመልከቻ በተመለከተ አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን የውለታ ቃሎችን እና ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ አመልካቹ አካል እውቅና የተሰጠው ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት መሆኑን ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ለሕዝብ ያስታውቃል፡፡

d) has competent personnel for the carrying out of its functions; and

e) satisfies such other conditions as may be determined by a directive to be issued by the Authority.

5/ The Authority may, in respect of an application made under Sub-Article (1) of this Article, subject to such terms and conditions as it considers necessary, by notice in a widely circulated newspaper, declare an entity to be a recognized self-regulatory organization.

፳፫. <u>ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት በውክልና የሚሰጥ ሥልጣን እና ተግባራት ማካተት ስላለባቸው ሁኔታዎች</u>

ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት የሚሰጥ የሥልጣን እና ተግባራት ውክልና ከዚህ ቀጥለው የተመለከቱትን ማካተት አለበት፡-

፩/ ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት በውክልና የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር፤

፪/ የዲሲፕሊን እርምጃች እንዲወስድ የተሰጠው የስልጣን ውክልና እና ሊወስዳቸው የሚችላቸው አስተዳደራዊ የቅጣት ወሰን እስከምን ድረስ እንደሆነ፤

፫/ በውክልና የተሰጠው ስልጣን ወይም ተግባር ስለሚፈጸምበት ሁኔታ የሚያመላክቱ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች፤

፬/ ራሱን በራሱ በሚቆጣጠር ድርጅት ስም በውክልና የተሰጠውን ስልጣን ወይም ተግባር እንዲያስፈጽሙ የተወከሉ ግለሰቦች፤

፭/ በውክልና የተሰጠውን ስልጣን ወይም ተግባር አፈጻጸም በተመለከተ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ለባለስልጣኑ በየወቅቱ ሪፖርቶችን ስለሚያቀርብበት አግባብ፣ እና

23. <u>Conditions for Delegation of Power and Duties to a Self-Regulatory Organization</u>

A delegation of power and duties made to a self-regulatory organization shall specify:

1/ the function or power delegated to the self-regulatory organization;

2/ the extent of disciplinary powers delegated and the scope of sanctions that may be imposed;

3/ the terms and conditions upon which the power or function has been delegated and may be exercised;

4/ the persons authorized to exercise the delegation on behalf of the self-regulatory organization;

5/ the manner in which a self-regulatory organization shall submit a periodical report to the Authority in respect of the exercise of a delegated power or function; and

፮/ ባለስልጣኑ በውክልናው ላይ የሚያመለክተው ማንኛውም ሌላ ጉዳይ፡፡

፳፬. <u>የራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ውስጠ-ደንቦች</u>

፩/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በውክልና ከተሰጠው ተግባር ጋር በተያያዘ የሚጣሉ ማናቸውም ቅጣቶችን እና የሚሠራባቸውን የዲሲፒሊን ስልጣኖቹን ጨምሮ ከቁጥጥርና በበላይነት ክትትል የማድረግ ሥራው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ውስጠ-ደንቦችን ያወጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡት ውስጠ-ደንቦች ቀጥለው የተመለከቱትን ጉዳዮች ማመልከት አለባቸው፡-

ሀ) የአባላቱን፣ የኢንቬስተሮችን እና የአገልግሎታቸው ተጠቃሚዎችን ጥቅም፣ መብትና ተጠያቂነትን ታሳቢ ያደረገ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት አስተዳደራዊ መዋቅርን እና የባለ አክሲዮኖች መብቶችን፤

ለ) የአባልነት ውስጠ-ደንቦች እና የአባልነት ጥያቄ ስለሚጸድቅበት እና አባል ስለሚቀበልበት ቅድመ ሁኔታዎች፤

ሐ) ሁሉም አባላት የሚስተናገዱበት ፍትሃዊ እና ወጥነት ያለው አሰራር እና በዳይሬክተሮች አመራረጥ እና በአስተዳደሩ አባላት ስለሚኖራቸው ፍትሃዊ ውክልና፤

መ) በአባላት፣ በተጠቃሚዎች፣ በኢንቬስተሮች እና በደንበኞቻቸው መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት መንገድ እና ለባለስለጣኑ ወይም ለሌላ የመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪ ይግባኝ ለማቅረብ ስለሚኖራቸው መብት፤

6/ any other matter as the Authority may prescribe.

24. <u>Rules of a Self-Regulatory Organization</u>

1/ A self-regulatory organization shall make rules relating to the matters for which it has regulatory or supervisory functions, including any sanction and disciplinary powers to be exercised in connection with the functions delegated to it.

2/ The rules made under Sub-Article (1) of this Article shall make provisions relating to:

a) management structures and shareholding rights of the self-regulatory organization taking into consideration the interests, rights and liabilities of its members, investors, and users of their services;

b) rules of membership and conditions for approval and admission of members;

c) fair and consistent treatment of all members; and fair representation of members in the selection of its directors and administration;

d) procedures for dispute resolution between members, users, investors and their clients and the right of appeal to the Authority or other relevant primary regulator;

ሠ) ሊፈጠሩ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶች ስለሚፈቱበት መንገድ እና ከባለስልጣኑ ጋር የህግና ደንብ ጥሰቶችን ስለመመርመር እንዲሁም ሕግና ደንብን ለማስፈጸም ስለሚደረግ ትብብር፤

ረ) ከባለስልጣኑ ውጭ ላለ ለማንኛውም የመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪ ስለሚኖር ተጠያቂነት እና ስለ ሪፖርት አቀራረብ የሚደነግግ ውስጠ-ደንቦች እና ስነ-ስርዓቶች፤

ሰ) በባለስልጣኑ በተቀመጠው የመረጃ ጥበቃ መርሆች መሠረት የመረጃ ባለቤቶች መረጃ ስለሚጠበቅበት መንገድ፤

ሸ) ጸረ-ውድድር አሰራሮችን ስለማስቀረት፤

ቀ) ስለ አባላቱ ስነ-ምግባር፤ እና

በ) ስለ ኢንቨስተሮች ጥበቃ እና ስለ ገበያው ተአማኒነት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚዘጋጅ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ውስጠ-ደንብ ለባለስልጣኑ ቀርቦ ከመጽደቁ በፊት ተግባራዊ መሆን የለበትም፡፡

፬/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ የሚያደርጋቸውን ማንኛውም ማሻሻያዎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት ለባለስልጣኑ አቅርቦ ማስጸደቅ አለበት፡፡

፳፭. ውሳኔ ላይ ስለሚደረግ ገደብ

ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት፡-

e) procedures to address potential conflicts of interest and cooperate with the Authority to investigate and enforce laws and regulations;

f) the rules and procedures of self-regulatory organization with respect to reporting and accountability to any primary regulator other than the Authority;

g) mechanisms of protecting personal data of the data subjects in compliance with the principles of data protection as set out by the Authority;

h) avoidance of anti-competitive practices;

i) standards of behaviour for its members; and

j) investor protection and market integrity.

3/ The rules of self Regulatory organization made under Sub-Article (1) of this Article shall not be implemented unless approved by the Authority.

4/ A self-regulatory organization shall submit any amendments to its memorandum of association to the Authority for approval before the amendments come into effect.

25. Restrictions on Decision

A self-regulatory organization shall not make a decision, under its rules, which adversely affect the rights of a person unless the self-regulatory organization:

https://ethiodata.et/

፩/ መብቱ የሚነካበት ሰው በጉዳዩ ላይ የራሱን አስተያየት እንዲያቀርብ ዕድል ካልሰጠ፤ ወይም

፪/ የውሳኔው መዘግየት የሸማቾች መብትን አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን ምክንያታዊነትን መሠረት አድርጎ ካልገመተ፤

በስተቀር በራሱ ውስጠ-ደንቦች መሠረት የአንድን ሰው መብት የሚጎዳ ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም፡፡

፳፮. የዲሲፕሊን እርምጃ

፩/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የውስጠ-ደንቦቹን ድንጋጌ በሚጥስ በማንኛውም አባሉ ላይ ራሱ በሚያወጣው ውስጠ-ደንብ መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃዎችን መውሰድ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት የሚወስደው የዲሲፕሊን እርምጃ ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፈቃድ የሰጠውን ሰው በተመለከተ ተጨማሪ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣኑን አይገድብም፡፡

፫/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወስድ በሁለት ቀናት ውስጥ የአባሉን ስም፣ የተወሰደውን እርምጃ ምክንያት፣ የተጣለውን የገንዘብ መቀጮ መጠን እና የእገዳ እርምጃ ተወስዶ ከሆነ እገዳው ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በተወሰነው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው ያመለከተ እንደሆነ ባለስልጣኑ ቅሬታ ላቀረበው ሰውና ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠረው ድርጅት የመሰማት መብት ከሰጠ በኋላ ውሳኔውን በድጋሚ በመመርመር ሊያጸናው፣ ሊለውጠው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

1/ has given that person an opportunity to make representations about the matter; or

2/ considers, on a reasonable ground, that a delay in making the decision will prejudice a class of consumers.

26. Disciplinary Action

1/ A self-regulatory organization may take a disciplinary action against any of its members in accordance with its rules, if the member contravenes any provisions of the rules.

2/ Any action taken by a self-regulatory organization under Sub-Article (1) of this Article shall not prejudice the power of the Authority to take any further action as it considers necessary with regard to the licensed person.

3/ self-regulatory organization shall, where it has taken a disciplinary action under Sub-Article (1) of this Article, within two days inform the Authority, in writing, of the name of the member, the reason and the action taken, the amount of any fine and the period of suspension if any.

4/ The Authority may, on application by an aggrieved person, review any disciplinary action taken under Sub-Article (1) of this Article and may affirm, modify or set aside the decision after giving the aggrieved person and the self-regulatory organization an opportunity to be heard.

https://ethiodata.et/

፭/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም እንኳን ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት አባሉ ላይ እርምጃ ሳይወስድ የቀረ እንደሆነ ባለስልጣኑ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠርን ድርጅት አባል ከማገድ፣ ከአባልነቱ ከማስወገድ ወይም ሌሎች የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ከመውሰድ ሊያግደው አይችልም፡፡

፮/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት ማንኛውንም ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት ፈቃድ የተሰጠውን ሰው እና ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠረው ድርጅት በጉዳዩ ላይ የመሰማት መብት ይጠብቅላቸዋል፡፡

፯/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተመለከቱትን ማናቸውንም ጉዳዮች አስመልክቶ ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠረው ድርጅት ተገቢውን የመሰማት ዕድል እንዲያገኝ ካደረገ በኋላ በጽሁፍ ተገቢውን ትዕዛዝ ሊሰጠው ይችላል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሰረት የሚሰጥ ትዕዛዝ፡-

ሀ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት መመስረቻ ጽሑፍ ወይም ውስጠ-ደንቦች በሚሰጠው ትእዛዝ ወይም መመሪያ ለተመለከተው ጊዜ እንዳይሰራበት ለማገድ፤

ለ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ሰነዱን ወይም ውስጠ-ደንቦቹን እንዲያሻሽል ማድረግ፤ ወይም

ሐ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት መመስረቻ ጽሑፉን ወይም ውስጠ-ደንቦቹን እንዲያስፈጽም ወይም እንዲተገብር ማድረግ ፤

ሊሆን ይችላል፡፡

5/ Nothing in this Article shall preclude the Authority, in any case where a self-regulatory organization fails to act against its member, from suspending, expelling or otherwise disciplining a member of the self-regulatory organization.

6/ The Authority shall, before taking any action under Sub-Article (5) of this Article, give the licensed person and the self-regulatory organization an opportunity to be heard.

7/ The Authority may, after giving a self-regulatory organization reasonable opportunity to be heard in respect of any matter, give direction, in writing, to the self-regulatory organization in terms of this Article.

8/ A direction given under Sub-Article (7) of this Article may:

a) suspend a provision of the memorandum of association or rules of a self-regulatory organization for a period specified in the direction;

b) require a self-regulatory organization to amend its rules; or

c) require a self-regulatory organization to implement or enforce its memorandum of association or its rules.

፳፯. የከፍተኛ ባለሙያ ሹመት እና ለውጥ

፩/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ለማድረግ ያሰበውን የከፍተኛ ባለሙያ ሹመት ወይም ለውጥ አስቀድሞ በጽሁፍ ለባለስልጣኑ ሳያሳውቅ ከፍተኛ ባለሙያ ሊሾም ወይም ለውጥ ሊያደርግ አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ማሳወቂያ ሲሰጠው ባለስልጣኑ ተቃውሞውን በ፲፭ ቀናት ውስጥ ያልገለጸ እንደሆነ የከፍተኛ ባለሙያው ሹመት ወይም ለውጥ የጸና ይሆናል፡፡

፳፰. ከፍተኛ ባለሙያን ስለማንሳት

ባለስልጣኑ በበቂ ምክንያት፡-

፩/ የራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ከፍተኛ ባለሙያ ድርጅቱን ለመምራት ብቃት እና ተገቢነት የለውም ብሎ ሲያምን፤ ወይም

፪/ የከፍተኛ ባለሙያው መሾም ወይም በሹመቱ መቀጠል ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት አደጋ ላይ ይጥላል የሚል እምነት ካለው ወይም የኢንቬስተሮችን እና የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ጥቅም ይጎዳል ወይም የአንድ የተለየ ዘርፍ ወይም ኢንዱስትሪ አባላትን ጥቅም ይጎዳል ብሎ ሲያምን፤

ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠረው ድርጅት እና ለከፍተኛ ባለሙያው የመሰማት ዕድል ከሰጣቸው በኋላ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት ከፍተኛ ባለሙያውን እንዳይሾመው ወይም ከኃላፊነት እንዲያነሳው ለማዘዝ ይችላል፡፡

27. Appointment and Change of Senior Personnel

1/ A self-regulatory organization shall not appoint or change its senior personnel except with the prior written notification to the Authority of such intention to appoint or change.

2/ Under Sub-Article (1) of this Article, if the Authority does not express its objection within 15 days, the appointment or change of senior personnel shall be effective.

28. Removal of a Senior Personnel

The Authority may, if it reasonably believes that:

1/ A senior personnel of a self-regulatory organization is not a fit and proper person to be an officer of the organization; or

2/ The appointment of a person or continuing in office as a senior personnel of a self-regulatory organization is likely to be detrimental to the self-regulatory organization or may prejudice the interest of investors and consumers of financial services or members of the relevant sector or industry;

after giving the senior personnel and the self-regulatory organization an opportunity to be heard, direct the self-regulatory organization not to appoint or to remove the senior personnel from office.

https://ethiodata.et/

፳፱. ዓመታዊ ሪፖርት

፩/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እያንዳንዱ የበጀት ዓመት ካበቃ በኋላ ባሉት አራት ወራት ውስጥ ለባለስልጣኑ የዓመቱን ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ሪፖርት የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካተተ መሆን አለበት፡-

ሀ) ራሱን በራሱ ስለሚቆጣጠር ድርጅት መልካም አስተዳደር ፖሊሲ እና አፈጻጸም ሪፖርትን፤

ለ) ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት የሂሳብ መግለጫቸውን እንዲያዘጋጁ በሚገደዱበት አኳሃን የተዘጋጀ የሂሳብ መግለጫን፤ እና

ሐ) ሌላ በባለስልጣኑ መመሪያ የተቀመጡ አስፈላጊ መረጃዎችን፡፡

፫/ የውጭ ኦዲተር በምርመራው ወቅት የሚከተሉትን ጥፋቶች ለመኖራቸው በቂ ምክንያት ኖሮት የጠረጠረ ከሆነ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) ራሱን በራሱ ከሚቆጣጠር ድርጅት ስራ ጋር በተያያዘ የስጋቶች ደረጃ በአሳሳቢ መልኩ ስለመቀየሩ ወይም ተቀይሮ እንደነበር እና ይህም የድርጅቱን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን፤

ለ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ማንኛውንም የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ወይም ባለስልጣኑ የሰጠውን ትዕዛዝ ጥሶ ሊሆን እንደሚችል፤

ሐ) የፋይናንስ ወንጀል ተፈጽሞ ከሆነ ወይም ሊፈጸም የሚችል ከሆነ፤ ወይም

29. Annual Report

1/ A self-regulatory organization shall, within four months after the end of every financial year, submit its annual report to the Authority.

2/ The report in Sub-Article (1) of this Article shall include:-

a) a report on the corporate governance policy and practices of the self-regulatory organization;

b) financial statements prepared and audited in accordance with the accounts and audit requirements for regulated persons; and

c) such other requirements as may be specified by directive of the Authority.

3/ An external Auditor who, in the course of his audit, has reason to believe that:

a) there is or has been an adverse change in the risks inherent in the business of a self-regulatory organization with the potential to jeopardize its ability to continue as a going concern;

b) the self-regulatory organization may be in contravention of any provisions of this Proclamation, or directions issued by the Authority;

c) a financial crime has been or is likely to be committed; or

መ) ከፍተኛ የአሰራር መዛባት ተከስቶ ከሆነ፡፡

፬/ ኦዲተሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት ሪፖርት ማቅረቡ የኦዲተርን ግዴታ እንደጣሰ ሊቆጠርበት አይችልም፡፡

ክፍል አራት
የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ

፴. ሕገ ወጥ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን ስለመከልከል

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ሳያገኝ ወይም ፈቃዱ በባለስልጣኑ ሳይፀድቅለት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን ወይም የተዛማጅ ውሎች ገበያን ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አገልግሎት ለማቋቋምና ለመስራት ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም የተዛማጅ ውሎች ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አገልግሎት ለመክፈት ወይም ለመጀመር አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው ‹‹የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ›› ወይም ‹‹የተዛማጅ ውሎች ገበያ›› የሚሉ ቃላቶችን ከንግድ ስራው ጋር በተያያዘ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

፴፩. የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን ስለመመስረት

፩/ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ (ከዚህ በኋላ ‹‹ገበያው›› እየተባለ የሚጠራ) በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ፣ የውጭ ኢንቨስተሮችን ጨምሮ፣ ትብብር በአክሲዮን ኩባንያ መልክ ይቋቋማል፡፡

d) serious irregularities have occurred;

shall report the matter, in writing, to the Authority.

4/ A report made under Sub-Article (3) of this Article shall not constitute a breach of the duties of the external Auditor.

PART FOUR
SECURITIES EXCHANGE

30. Prohibition of Unlawful Securities Exchange

1/ A person shall not establish or launch a business as a securities exchange or a derivatives exchange or over-the-counter trading facility, or hold himself out as creating a securities market or a derivative contracts market or over-the-counter trading facility that is not licensed or approved as a securities exchange or a derivatives exchange or over-the-counter trading facility by the Authority under this Proclamation.

2/ It is prohibited for any person to use the words “securities exchange” or “derivatives exchange” in connection with a business except with an exchange license granted by the Authority.

31. Establishment of the Ethiopian Securities Exchange

1/ The Ethiopian Securities Exchange (hereunder the “Exchange”) shall be established as a share company by the Government in partnership with the private sector, including foreign investors.

https://ethiodata.et/

፪/ የመንግስትና በመንግስት የተያዙ ድርጅቶች ከገበያው ካፒታል ላይ የሚኖራቸው ድርሻ ከ ፳፭ በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለጸው ቢኖርም ከግሉ ዘርፍ የገበያውን ካፒታል ድርሻ ለመያዝ በቂ ፍላጎት ከሌለ መንግስት ገበያውን ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ያህል ተጨማሪ ካፒታል ለመያዝ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተገለጸው ቢኖርም ከግሉ ዘርፍ፣ የውጭ ኢንቬስተሮችን ጨምሮ፣ የገበያውን ካፒታል ድርሻ ለመያዝ ምንም ፍላጎት ከሌለ ገበያው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ ይቋቋማል፡፡

፭/ ባለስልጣኑ ገበያው የአነስተኛ የካፒታል መመዘኛ፣ የተገቢነት እና ብቁነት መስፈርት፣ የስራ እና ስራ አመራር ሁኔታን፣ የብቃት ማስረጃ፣ እና ሌሎች ባለስልጣኑ በመመሪያ የሚደነግጋቸው ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ የገበያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

፮/ በዚህ አንቀፅ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ሌሎች በንግድ ህጉ የተደነገጉ ተገቢነት ያላቸዉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፴፪. <u>ሌሎች የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎችና የግብይት መድረኮች</u>

፩/ ባለስልጣኑ ለሌሎች በአክሲዮን ኩባንያነት ለሚቋቋሙ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያዎች፣ ወይም ለተዛማጅ ገበያዎች ወይም ላልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ መገበያያ መድረኮች የስራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ The total ownership of the Government and government-owned entities shall not exceed 25% of the Exchange's capital.

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, and if there is insufficient interest from the private sector, the Government's ownership of the Exchange can be increased to whatever amount is needed to establish the Exchange.

4/ Notwithstanding Sub-Articles (2) and (3) of this Article, and if there is no interest at all from the private sector, including from foreign investors, the Exchange shall be established as a fully Government owned public enterprise by regulation of the Council of Ministers.

5/ The Authority shall grant an exchange license to the Exchange upon its establishment and meeting minimum capital requirements, fit and proper criteria, conditions of work and management, evidence of competence, and any other requirements to be specified by directive of the Authority.

6/ Notwithstanding the provisions of this Article, other relevant provisions of the commercial code shall have an effect.

32. <u>Other Securities Exchanges and Trading Platforms</u>

1/ The Authority may grant license to other securities exchanges or derivatives exchanges or over-the-counter trading platforms which shall be established as share companies.

https://ethiodata.et/

፪/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለሚሰጠው የስራ ፈቃድ የአነስተኛ የካፒታል መመዘኛን፣ የተገቢነት እና ብቁነት መስፈርትን፣ የስራ እና ስራ አመራር ሁኔታን፣ የብቃት ማስረጃን፣ እና ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎችን በመመሪያ ይደነግጋል፡፡

፫/ የዚህ አዋጅ ማናቸውም ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ ባለስልጣኑ ባልተማከለ ጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የሚካሄዱ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወይም ተዛማጅ ውሎችን ግብይት በተመለከተ ተዋንያንን፣ ውሎችን፣ ሁኔታዎችን እና መስፈርቶችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

፴፫. <u>በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያና የግብይት መድረኮች ላይ ስለሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

፩/ ባለስልጣኑ፡-

ሀ) ገበያው በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አቅርቦት እና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ዋጋን ማመላከት እንዳይችል የሚያደርግ ከፍተኛ የግብይት መስተጓጎል ሲከሰት፤

ለ) ተጨባጭ ወይም ተገማች የሆነ ገበያን የማዛባት ድርጊት ሲኖር፤

ሐ) ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ወይም ኢንቬስተሮችን ለመጠበቅ ጠቃሚ ወይም አስፈላጊ ነው ብሎ ባለስልጣኑ ሲያስብ፤ ወይም

2/ The Authority shall determine, by a directive, minimum capital requirements, fit and proper criteria, conditions of work and management, evidence of competence, and any other requirements for licencing under Sub-Article (1) of this Article.

3/ Notwithstanding any provision of this Proclamation, the Authority shall determine by directive the participants, contracts, conditions, and requirements regarding trading of securities and derivative contracts in the over-the-counter market.

33. <u>Administrative Measures against a Securities Exchange and Trading Platforms</u>

1/ The Authority may direct, by notice in writing, that a securities exchange or derivative exchange shall be closed for such period as may be specified in the direction, where:

a) there is a major market disruption which prevents the market from accurately reflecting price signals based on the forces of demand and supply for such securities;

b) there is a threatened or actual manipulation of the market;

c) the Authority considers it necessary or beneficial in the interest of the public or for the protection of investors' interest; or

መ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግብይት ሊያስቆም የሚችል እርምጃ መንግስት ሲወስድ፤

በጽሁፍ በሚያስተላልፈው ትዕዛዝ መሠረት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም የተዛማጅ ገበያ በትዕዛዙ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ እንዲዘጋ ለመወሰን ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም በማናቸውም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መደቦች የሚደረጉ ግብይቶች ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ግብይት የሚደረግባቸው ተዛማጅ ውሎች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ወይም የተጓደለ ካለ እንዲስተካከል ለማድረግ፣ ወይም

ለ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መደቦች ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ግብይት ሚደረግባቸው ተዛማጅ ውሎች እንዲሸጡ ለማድረግ፤

አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

፫/ ባለስልጣኑ የገበያውን ፈቃድ ለተወሰነ ጊዜ ወይም አንድ ዓይነት ተግባር እስከሚፈጸም ድረስ ሊያግድዉ ይችላል፡፡ ባለስልጣኑ ይህንን እርምጃ የሚወስደው ገበያው፡-

ሀ) ከተሰጠው የስራ ወሰን ወይም ከተፈቀደለት የስራ ዘርፍ ዉጭ የሆነ ተግባር ከፈጸመ፤

ለ) ከተሰጠው ፈቃድ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ቅድመ ሁኔታዎች ከጣሰ ወይም ካላከበረ፤

ሐ) የባለስልጣኑን ትዕዛዝ ከጣሰ፤

d) there is in place, an act of Government affecting the trading of securities.

2/ The Authority may take such steps as it considers necessary to:

a) maintain or restore a fair, efficient, and transparent trading in securities or any classes of securities or exchange-traded derivative contracts; or

b) liquidate any position in respect of any securities or any classes of securities or exchange-traded derivative contracts.

3/ The Authority may suspend the license of an Exchange for such period or until the occurrence of such event as the Authority may specify if the exchange:

a) carries out any activity outside the scope of the exchange or approved activities;

b) has contravened or failed to comply with any condition applicable in respect of the license;

c) fails to comply with a direction of the Authority;

መ) ባለስልጣኑ የሚጠይቀውን ማንኛውንም መረጃ ካልሰጠ፤

ሠ) ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ከሰጠ፤ ወይም

ረ) የዚህን አዋጅ ወይም አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦች ወይም መመሪዎች ድንጋጌ ጥሶ ከተገኘ፤

ነዉ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚደረግ ገበያውን የማገድ ውሳኔ ከ ፫ (ሦስት) ወራት በላይ ሊቆይ አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ ባለስልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ ካመነ እገዳውን ለተጨማሪ ከሦስት ወራት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የተወሰነው የሦስት ወር የዕገዳ ጊዜ ሲያበቃ ባለስልጣኑ እንደ አስፈላጊነቱ እገዳውን ሊያነሳ ወይም የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል፡፡

፮/ ገበያው:-

ሀ) ወደ ሀብት ማጣራት ውስጥ ከገባ ወይም ሂሣቡ ተጣርቶ እንዲዘጋ ትዕዛዝ ከተሰጠ፤

ለ) ለፈቃዱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ፤

ሐ) ፈቃዱን ለመመለስ ካመለከተ እና ማመልከቻዉ ተቀባይነት ካገኘ፤

መ) ከዚህ በፊት የፈቃድ እግድ ያስከተለበትን ጥፋት ደግሞ ከሰራ፤ ወይም

ሠ) በሌላ በማናቸውም ምክንያት ፈቃዱን ይዞ ለመቀጠል ብቁ እና ተገቢ ሆኖ ካልተገኘ፤

ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ሊሰርዝበት ይችላል፡፡

d) fails to provide the Authority with such information as it may require;

e) provides false or misleading information; or

f) is in breach of any other provision under this Proclamation or regulations or directives issued thereunder.

4/ A suspension of a license under Sub-Article (3) of this Article shall not exceed a period of 3 (three) months; the Authority, if deemed necessary, may extend the suspension for a further period not exceeding three months.

5/ The Authority shall, at the expiry of the suspension period specified under Sub-Article (4) of this Article, lift the suspension or revoke the license, as the Authority considers appropriate.

6/ The Authority may revoke the license of an Exchange if the Exchange:

a) goes into liquidation or an order is issued for its winding up;

b) fails to rectify the failings that led to the suspension of its license within the specified time given by the Authority;

c) has requested it and its request is accepted by the Authority;

d) has committed a violation that has led to suspension of its license in the past; or

e) for any other reason, is no longer a fit and proper person to hold the license.

፯/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት ፈቃዱን ለመሰረዝ ከመወሰኑ በፊት ባለፈቃዱ ተቃውሞ ካለው ተቃውሞውን በደብዳቤ እንዲያቀርብ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፰/ ባለፈቃዱ ያቀረበው ተቃውሞ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ወይም ባለፈቃዱ የባለሥልጣኑ ማስታወቂያ ደብዳቤ በደረሰው በ፴(ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካላቀረበ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

፱/ ባለሥልጣኑ የገበያውን ፈቃድ የሰረዘበትን ውሳኔ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እንዲታተም ያደርጋል፡፡

፲/ የፈቃዱ መሰረዝ ውሳኔ በጋዜጣ ከወጣበት ወይም ባለሥልጣኑ ከሚወስነው ሌላ ማናቸውም ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

፴፬. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ስራ አመራር

፩/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ስራ የሚመራው በገበያው ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚመረጥ እና በባለስልጣኑ ይሁንታ በሚሾም የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገዉ ቢኖርም፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሹመት የሚፀድቀዉ የባለስልጣኑን ይሁንታ ካገኘ በኋላ ነዉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቀርበውለት ባለስልጣኑ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካልገለጸ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ የባለስልጣኑን ይሁንታ እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

7/ The authority, before deciding to revoke the license pursuant to sub-article (6) of this Article, shall notify the licensed person by a letter to submit his objection in writing, if any.

8/ If the objection of the licensed person is not found to be satisfactory or the licensed person fails to submit his objection within 30 (thirty) days of receipt of Authority's letter, his license shall be revoked.

9/ The decision to revoke the license of an Exchange shall be published by the Authority in a newspaper of wide circulation.

10/ The revocation of license shall become effective on the date of its publication or on any other date as the Authority may specify.

34. Management of a Securities Exchange

1/ The affairs of a securities exchange shall be managed by a board of directors whose members shall be elected by the shareholders of the securities exchange.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the election of board of directors of the securities exchange shall be effective subject to consent of the Authority.

3/ Under Sub-Article (1) of this Article, if the Authority does not express its objection within 30 (thirty) days, the election of board of directors of the securities exchange shall be considered as having received the consent of the Authority.

፬/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በኃላፊነት ዘመኑ ሁሉ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) መልካም ስምን የሚያጎድፍ ወይም እምነት የማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ አለመገኘት፤

ለ) የመጨረሻ የመክሰር ውሳኔ ያልተሰጠበት መሆን፤

ሐ) መልካም ስምና ዝናውን መጠበቅ፤ እና

መ) በፋይናንስ፣ በስራ አመራር፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ልምድ እና ብቃቱን በቀጣይነት ማሻሻል፡፡

፭/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ገበያው ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተመስርተው የወጡትን ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲሁም የራሱን የገበያውን ውስጠ-ደንቦች አክብሮ መስራቱን ማረጋገጥ እና፡-

ሀ) የገበያውን አጠቃላይ ስራዎች በበላይነት መቆጣጠር፤ እና

ለ) ተገቢውን የፋይናንስ ስራ አመራር መዋቅር እና ሂደቶች በመፍጠር የገበያውን አመራር በበላይነት መከታተል፤

አለበት፡፡

፮/ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የዚህ አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ተመስርተው የወጡት ደንቦች እና መመሪያዎች ድንጋጌዎች ጥሰቶች ሲፈጸሙ በጋራ እና በተናጠል ኃላፊነት የመወሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡

4/ A member of the board of directors of a securities exchange shall at all times, while remaining in his position, be subject to the following conditions:

a) not have been convicted of a crime of breach of honour or trust;

b) not have been declared bankrupt under a final judgment;

c) be of good reputation; and

d) Continuously work towards improving his qualification and experience in finance, management, economics, legal, or related affairs.

5/ The board of a securities exchange shall ensure that the exchange is operated in compliance with this Proclamation, as well as regulations and directives made in accordance with this Proclamation, and the exchange's own rules and shall:

a) be responsible for the general oversight of the affairs of the exchange; and

b) oversee the administrative affairs of the exchange in order to ensure sound financial management structures and processes.

6/ The members of the board of directors of a securities exchange shall individually and collectively be responsible for any non-compliance with the provisions of this Proclamation, as well as regulations and directives made in accordance with this Proclamation.

፯/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በባለስልጣኑ ይሁንታ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም ዋና ስራ አስፈፃሚ ይኖረዋል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት የዋና ስራ አስፈጻሚ ሹመት ቀርቦለት ባለስልጣኑ በ ፴(ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካልገለጸ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የዋና ስራ አስፈጻሚ ሹመት የባለስልጣኑን ይሁንታ እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

፱/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢን እና የዋና ስራ አስፈጻሚን ስልጣኖች ደርቦ መያዝ የተከለከለ ነው፡፡

፴፭. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ዉስጠ-ደንቦች

በባለስልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ለገበያው እና በገበያው ለሚካሄድ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አስተዳደር፣ አሠራር፣ አመራር እና ቁጥጥር ተገቢ እና አስፈላጊ የሆኑ ዉስጠ-ደንቦችን እና ሥነ-ሥርዐቶችን ማውጣት ይኖርበታል፡፡

፴፮. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ኃላፊነቶች

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ለሚከተሉት ጉዳዮች ኃላፊነት ይኖሩበታል፡-

፩/ ፍትሃዊነትን፣ ቅልጥፍናን፣ ግልጽነትን እና የኢንቬስተሮች ጥበቃን እንዲሁም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የቁጥጥር ማዕቀፍ መከበሩን ለማረጋገጥ ገበያውን እና አባላቱን በቅርበት መከታተል፣ ቅኝት ማድረግ እና በበላይነት መከታተል፤

፪/ በገበያው ላይ የሚፈጠሩ ያለመግባባቶች የሚፈቱበት ስነ-ስርዓት እና የይግባኝ አሰራር፣ ከገበያው አሰራር ጉድለት ጋር የተያያዙ የቴክኒክ ዘዴዎች እና አሰራሮች፣ የሪኮርድ

7/ A securities exchange shall have a Chief Executive Officer appointed by the Board of directors of the exchange; and subject to the consent of the Authority.

8/ Under Sub-Article (7) of this Article, if the Authority does not express its objection within 30 (thirty) days, the appointment of the chief executive officer of the exchange shall be considered as having received the consent of the Authority.

9/ It is prohibited to conjoin the position of the chairman of the board of directors with the position of the chief executive officer of a securities exchange.

35. Rules of a Securities Exchange

Subject to the approval of the Authority, a securities exchange shall make such rules or procedures of the exchange as it considers necessary or desirable for the proper and efficient regulation, operation, management and control of the exchange and the securities market operated by the exchange.

36. Responsibilities of a Securities Exchange

A securities exchange shall be responsible for:

1/ Monitoring, surveillance and supervision of the exchange and its members to ensure fairness, efficiency, transparency, and investor protection, as well as compliance with the securities regulatory framework;

2/ Having a market's dispute resolution and appeal procedures as appropriate, technical systems standards and procedures related to operational failure,

አያያዝ ዘዴ፣ የህግ ጥሰት ስለመኖሩ ያሉ ጥርጣሬዎች ላይ የሚቀርብ ሪፖርት፣ እንደተፈጻሚነቱ የደንበኞችን ገንዘቦች እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ስለሚጠበቁበት አግባብ እንዲሁም ስለግብይት ውሎች አፈጻጸም እና የክፍያ መረጃ የሚሰጥበት ስርዓት እንዲኖር ማድረግ፤

፫/ የገበያ መድረኩ ያላስፈላጊ የዋጋ መዋዠቅን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው የግብይት መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ማለትም የግብይት ማስቆሚያ፣ የዋጋ መዋዠቅ ማቋረጫ ዘዴዎች፣ እንዲሁም የዕለት ጣሪያ እና ወለል መቆጣጠሪያዎች እና ሌሎች የግብይት መቆጣጠሪያዎች እንዲኖሩት ማድረግ፤

፬/ በገበያው ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ላይ ከፍተኛ ስጋት ሊያስከትሉ የሚችሉ መልስ ያላገኙ የመሸጥ ወይም የመግዛት ግብዣዎችን ወይም ያልተከፈሉ ዕዳዎች ወይም ያልተጠናቀቁ ግብይቶችን የቅርብ ክትትል የሚደረግበት ዘዴ ማበጀት፤

፭/ የግብይት አፈጻጸም ውስጠ-ደንቦችን እና የግብይት ትዕዛዞች የሚተላለፉበትን አሰራር ባለስልጣኑ እና የገበያ ተዋናዮች በግልጽ እንዲያውቁት መደረጉን እና ለሁሉም ተሳታፊዎች ወጥነት ባለው መንገድ ተፈጻሚ መሆኑን ማረጋገጥ፤

፮/ ለሁሉም ተሳታፊዎች ከኤሌክትሮኒክ መገበያያ ዘዴው ጋር እንዲተሳሰሩ እና የሚፈጥሩትን ትስስር ሳይቋረጥ እንዲያስቀጥሉ እኩል ዕድል መስጠት፤

፯/ በተለይም አባላት ተገቢ የስጋት ደረጃ ገደባቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችላቸውን በራሱ የሚሰራ ቅድመ-

record keeping system, reports of suspected breaches of law, arrangements for holding client funds and securities, if applicable, and information on how trades are cleared and settled;

3/ Ensuring that the trading venue has in place suitable trading control mechanisms including trading halts, volatility interruptions, limit-up/limit-down controls and other trading limitations to deal with volatile market conditions;

4/ Having mechanisms to monitor open positions, or credit exposures, on unsettled trades that are sufficiently large to pose a risk to the market or to the Securities Depository and Clearing Company;

5/ Making sure that execution rules and trade order routing procedures are clearly disclosed to the Authority and to market participants and consistently applied to all participants;

6/ Providing equal opportunity to all system users to connect, and maintain the connection to, the electronic trading system;

7/ Designing systems and controls to enable the management of risk about fair and orderly trading including, in particular,

ግብይት መቆጣጠሪያን ተግባራዊ ማድረግን ጨምሮ ፍትሃዊና ትክክለኛ ግብይት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት መፍጠር እና ተግባራዊ ማድረግ፤

፰/ ለሁሉም የገበያ ተዋናዮች የግብይት ውስጠ-ደንቦችን እና አሰራሮችን እንዲያውቁ እኩል ዕድል መስጠት፤

፱/ ለገበያው አባላት አስፈላጊ የቅድመ ግብይት እና የድህረ ግብይት መረጃዎችን በቀጥታ ማሰራጨት ወይም ቀጥታ ተደራሽነት እንዲኖረው ማድረግ፤

፲/ ከስራው ጠባይ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን የሚረዳ የስራ አመራር እንዲኖር ማድረግ፤

፲፩/ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው፣ በአባላቱ፣ በባለ አክሲዮኖቹ ወይም በስራ አመራሩ መካከል የጥቅም ግጭት ሲኖር የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም፤

፲፪/ ባለስልጣኑ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት አገልግሎቶቹን መስጠት እና ሥራውን ማከናወን፤

፲፫/ ስራዎቹን፣ አሰራሮቹን፣ እና የአባላቱን ስነ-ምግባር በገበያው ውስጠ-ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ እና አሰራሮች መሠረት መምራት እና ማቀናጀት፤

፲፬/ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የተመዘገቡ ኩባንያዎችን እና የሰራተኞቻቸውን አሰራሮች እና አተገባበሮች ተገቢ በሆኑ ደንቦች መሠረት መካሄዳቸውን መቆጣጠር፤

፲፭/ በሕግ ካልተጠየቀ ወይም እንዲያሳትም ወይም እንዲያሳውቅ ካልተገደደ በቀር በቁጥጥሩ ስር ያሉትን ማንኛውንም አባላቱን እና ደንበኞችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ሚስጢራዊነት መጠበቅ፤ ለባለስልጣኑ ወይም

automated pre-trade controls that enable members to implement appropriate risk limits;

8/ Providing market participants equitable access to market rules and operating procedures;

9/ Providing members access to relevant pre- and post-trade information on a real-time basis;

10/ Ensuring the existence of a management that is aware of the risks associated with its business and operations.

11/ Prioritizing the public interest in case of a conflict of interest with the securities exchange or its members, shareholders or management;

12/ Adhering to provide and operate its services in accordance with the Directives issued by the Authority.

13/ Adhering to organize its operations, standards of its practices and its members' behaviours in accordance with the rules, policies and procedures of the securities exchange;

14/ Adhering to organize the operations and standards of practices of the companies listed therein and their employees in accordance with the governing regulations;

15/ Maintaining the confidentiality of all information under its custody with respect to its members and customers, unless it is required by law to publish or disclose such information; not disclose such information except for the

https://ethiodata.et/

በባለስልጣኑ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በቀር እነዚህን መረጃዎች አሳልፎ አለመስጠት፤

፲፮/ የቅድመ ግብይት መረጃዎች፣ የድህረ ግብይት መረጃዎች፣ እና ስለተጠናቀቁ ግብይቶች መረጃዎች ለሁሉም የገበያ ተዋናዮች ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ የሚደርስበትን ውስጠ-ደንቦች ከነመመዘኛዎቻቸው ማውጣት፡፡

፴፯. ለባለስልጣኑ መረጃ ስለመስጠት፣ ሪፖርት ስለማድረግ፣ እና እገዛ ስለማድረግ

፩/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ከሥራው ወይም ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ጋር በተያያዘ ምላሾች እና መረጃዎች መስጠትን ወይም ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የተጣሉበትን ተግባሮች እና ግዴታዎች በአግባቡ ለመፈጸም የሚጠይቃቸው ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች ጨምሮ ባለሥልጣኑ ሥራውን እና ተግባሩን ለማከናወን ምክንያታዊነትን መሠረት አድርጎ ለሚያቀርበው ጥያቄ እገዛ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፡-

ሀ) ማንኛውም አባል የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያውን ውስጠ-ደንቦች ወይም የገንዘብ ሀብቶቹን መመሪያዎች የማያከበር ከሆነ፤

ለ) አባሉ ግዴታዎቹን ለመወጣት አቅም እንደሌለው ወይም የአባሉ ተገቢነት ላይ ችግር እንዳለ የሚያመለክት የተዛባ የሂሳብ አያያዝ ወይም ሌላ ትክክለኛ ያልሆነ አሰራር መኖሩን ሲገምት፤ ወይም

Authority or by an order from the Authority or the court;

16/ Issuing rules with requirements for providing pre-trade information, post-trade information and information on completed transactions on an equitable basis to all market participants.

37. Information Sharing, Reporting, and Assistance to the Authority

1/ A securities exchange shall provide such assistance to the Authority as the Authority may reasonably require for the performance of its functions and duties, including the furnishing of such returns and information relating to its business or in respect of dealings in securities or any other specified information as the Authority may require for the proper implementation of this Proclamation.

2/ A securities exchange shall inform the Authority immediately about the following issues:

a) if found that one of its members does not comply with any of the securities exchange's rules or its financial resources' regulations;

b) if it deemed there is a financial irregularity or any other situation that may indicate inappropriateness of the member or his incapacity to fulfil his obligations; or

ሐ) አባሉ ላይ ወይም ስራ አከናዋኝ ላይ ወይም በስሩ በሚሰሩት ሰዎች ላይ ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወሰድ፤

ጉዳዩን ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)(ሐ) መሰረት በማንኛውም አባሉ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወሰድ የተከሰተውን ጥፋት ዝርዝር፣ የሂደቱን ዝርዝር እና የቅጣቱን ዓይነት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ሰነዶች ቅጂዎችም በሙሉ ለባለስልጣኑ መላክ አለባቸው፡፡

፴፰. **<u>የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ዉስጠ-ደንቦችን ስለማሻሻል</u>**

፩/ ዉስጠ-ደንቦቹን በመሰረዝ፣ በመለወጥ ወይም በመጨመር ለማሻሻል የሚፈልግ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የታሰበውን የማሻሻያ ረቂቅ በቅድሚያ ለባለስልጣኑ አቅርቦ ማስጸደቅ አለበት፡፡

፪/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሰረት የቀረበለትን የማሻሻያ ሀሳብ በተቀበለ በ፳፰ (ሃያ ስምንት) ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የቀረበውን የዉስጠ-ደንብ ለውጥ ሃሳብ ውድቅ ማድረጉን በጽሁፍ ሊያሳውቅ ይችላል፤ ይህ ከሆነ ለውጡ ቢደረግም የሕግ ውጤት አይኖረውም፡፡

፫/ የዉስጠ-ደንብ ማሻሻያ ሃሳብ ከቀረበ በኋላ በ፳፰ (ሃያ ስምንት) ቀናት ውስጥ ከላይ የተመለከተው ዓይነት ማስታወቂያ ካልተሰጠ የቀረበው የዉስጠ-ደንብ ማሻሻያ ተቀባይነት እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

c) any disciplinary action is taken against any member, operator, or his subordinates.

3/ The board of directors of an exchange shall inform the Authority of any disciplinary action taken against any of its members under Sub-Article (2) (c) of this Article, the details of the violation committed, and the procedures taken and the penalty imposed. The Authority shall be provided with copies of all documents related to the subject.

38. **<u>Amendment to Rules of a Securities Exchange</u>**

1/ A securities exchange that wishes to make any amendment (whether by way of rescission, alteration or addition) to its rules shall submit a draft of the proposed amendment to the Authority for approval.

2/ The Authority may, within 28 (twenty eight) days after receipt of a draft in accordance with Sub-Article (1) of this Article, by notice to the exchange concerned disallow the amendment; whereupon the amendment, if made, ceases to have force or effect.

3/ If no such notice is given within 28 (twenty eight) days after the proposed amendment was submitted to the Authority, the proposed amendment shall be deemed to have been approved.

፬/ የባለስልጣኑ ቦርድ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያውን ከስራው ጋር በተያያዘ የተወሰኑ ድንጋጌዎችን እንዲያካትት ወይም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ውስጠ-ደንቹን እንዲያሻሽል ለማዘዝ ይችላል፡፡

፭/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት የተሰጠውን ትዕዛዝ ሳያከብር ከቀረ ወይም በታዘዘው ጊዜ ውስጥ ካላደረገ፡-

ሀ) ባለስልጣኑ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ወጪ የታዘዘውን የዉስጠ-ደንብ ዝግጅት ወይም የዉስጠ-ደንብ ማሻሻያ በራሱ ሊያደርግ ይችላል፣ እና

ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያውም በዚህ መንገድ የተሻሻሉትን ውስጠ-ደንቦች አክብሮ እንዲሰራባቸው ይገደድበታል፡፡

ክፍል አምስት
የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ

፴፱. የፈቃድ አሰጣጥ

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ወይም ፈቃዱ በባለስልጣኑ ሳይፀድቅለት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ማቋቋም፣ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የማስቀመጥ፣ ክፍያዎችን የማጣራትና የመፈፀም ወይም ሌሎች ተያያዥነት ያላቸዉን አገልግሎቶችን መስጠት አይችልም፡፡

፪/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ፈቃድ የሚሰጠው የዝቅተኛ ካፒታል መስፈርትን፣ የብቃትና ተገቢነት መስፈርትን፣ የስራ እና ስራ አመራር ሁኔታዎችን፣ የብቃት ማረጋገጫን እና ሌሎች ማናቸውንም በባለስልጣኑ

4/ The Board of Authority may direct a securities exchange to prepare specific provisions within its scope of work or amend its rules within a certain period.

5/ If the securities exchange fails to abide by the request or to meet the request within the specified period under Sub-Article (4) of this Article:

a) the Authority may prepare the rules or amend them on behalf of the securities exchange at the expense of the latter; and

b) the exchange shall have the obligation to abide by these amended rules.

PART FIVE
SECURITIES DEPOSITORY AND CLEARING COMPANY

39. Licensing

1/ No Person shall incorporate a Securities Depository and Clearing Company or provide securities depository, clearing, or related services without obtaining license from, or its license approved by, the Authority in accordance with this Proclamation.

2/ A Security Depository and Clearing Company license may only be granted to a share company that meets minimum capital requirements, fit and proper criteria, conditions of work and management, evidence of competence,

መመሪያ የሚወሰኑ መስፈርቶች ለሚያሟላ የአክሲዮን ኩባንያ ብቻ ነው፡፡

፫/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ስለሚሰጥ ፈቃድ ዝርዝር ሁኔታዎችን በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ሌሎች በንግድ ህጉ የተደነገጉ ተገቢነት ያላቸዉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፵. <u>የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ግዴታዎች</u>

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ስራን እንዲሰራ በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ቀጥለው የተመለከቱትን ግዴታዎች መፈጸም አለበት፡-

፩/ መልሶ የመግዛት ውልን እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማበደርን ጨምሮ ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የሚያስፈልገውን ፍትሃዊ እና ውጤታማ የርክክብ እና ክፍያ ስርዓት መዘርጋት፤

፪/ ከሚያከናውናቸው ተግባራት እና ከአሰራሩ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን በከፍተኛ የሙያ ብቃት መቆጣጠር፤

፫/ ከኩባንያው ጥቅም ይልቅ የሕዝብን ጥቅም እና ከኩባንያው ጋር የሚሰሩ አካላትን ጥቅም ማስቀደም፤

፬/ ስራውን ባለስልጣኑ ባጸደቃቸው ዉስጠ-ደንቦች መሠረት ማከናወን፤ እና መምራት፤

፭/ በባለስልጣኑ ወይም በህግ ወይም በፍርድ ቤት ይፋ እንዲደረግ ከተጠየቀው ውጭ ያሉ በእጁ የሚገኙ መረጃዎችን ሚስጢራዊነት መጠበቅ፤

፮/ ባለስልጣኑ ባጸደቀው ወይም ባዘዘው ወይም በወሰነው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት

and any other requirements to be specified by directive of the Authority.

3/ The Authority shall specify the conditions required for granting a license under Sub-Article (2) of this Article on its directive.

4/ Notwithstanding the provisions of this Article, other relevant provisions of the commercial code shall have an effect

40. <u>Obligations of Security Depository and Clearing Company</u>

A company licensed by the Authority as Security Depository and Clearing Company shall abide by the following obligations:

1/ Arrange for fair and effective clearing and settlement in relation to any commercial transactions of securities, including repo agreements and securities lending.

2/ Manage risks associated with its activity and operation at the highest levels of professionalism.

3/ Prioritize to the public interest and that of those who deal with the company over the company's own interests.

4/ Manage its services according to the related rules approved by the Authority.

5/ Maintain confidentiality of all information and data under its possession, except what is required by the Authority or by Law or by Court.

6/ Provide its services with an up-to-date technology and automated systems in

https://ethiodata.et/

ባለው እና ወቅታዊ በሆነ ቴክኖሎጂ እና ራስን በራሱ የሚያሰራ ዘዴን ተጠቅሞ አገልግሎቶችን መስጠት፡፡

፵፩. ውስጠ-ደንቦችና ውስጣዊ መመሪያዎች

፩/ ባለስልጣኑ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ርክክብ፣ ክፍያ እና ምዝገባ አሰራርን እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን የሚመለከቱ ውስጠ ደንቦችንና ውስጣዊ መመሪያዎችን እንዲያወጣ ወይም አስቀድሞ ያወጣቸውን ደንቦች ባለስልጣኑ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ እንዲያሻሽል የማዘዝ መብት አለው፡፡

፪/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው የተሰጠውን ትዕዛዝ በታዘዘው ጊዜ ውስጥ ሳያከብር ከቀረ፡-

ሀ) ባለስልጣኑ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው ወጪ የውስጠ-ደንብ ዝግጅት ወይም የዉስጠ-ደንብ ማሻሻያ በራሱ ሊያደርግለት ይችላል፤ እና

ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያውም ባለስልጣኑ ያዘጋጃቸዉን ውስጠ-ደንቦች እና መመሪያዎች አክብሮ እንዲሰራባቸው ይገደድበታል፡፡

፫/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ባለስልጣኑ ሳያጸድቅለት እንደ አዲስ ያወጣቸውን፣ ያሻሻላቸውን፣ የሻራቸውን፣ የለወጣቸውን ወይም የጨመራቸውን ውስጠ-ደንቦች በስራ ላይ ሊያውል አይችልም፡፡

line with international standards approved by the Authority or as requested or decided by the Authority.

41. Rules and Regulations

1/ The Authority shall require the Security Depository and Clearing Company to prepare rules and regulations related to the operations of clearing, settlement, and registration of securities and other activities that relate to the company's business, or to amend the same within a certain period.

2/ If the Security Depository and Clearing Company does not comply the order given within the specific period:

a) the Authority may prepare or amend the said rules on behalf of the Security Depository and Clearing Company at the expense of the latter; and

b) the Security Depository and Clearing Company shall have the obligation to abide by these.

3/ No rules issued by the Security Depository and Clearing Company nor amendments thereto, either by withdrawal, replacement or change, or addition thereof, shall be valid and effective unless they are approved by the Authority.

፬/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አዳዲስ ውስጠ-ደንቦችን የሚያወጣ ከሆነ ስለሚያወጣቸው ደንቦች ወይም ማሻሻያዎች ምክንያት እና ዓላማ እንዲሁም ውስጠ-ደንቦቹ ስለሚያስከትሉት ውጤት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፭/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የቀረበለትን አዲስ ዉስጠ-ደንብ ወይም ማሻሻያ ሊያጸድቅ፣ ወይም ላይቀበል ወይም ሊያሻሽል ይችላል፤ ሆኖም ውሳኔውን ከሰጠ በኋላ ቢያንስ በአንድ ሳምንት ውስጥ ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፮/ አንድ ተገበያይ የክፍያ ደንቦች የሚጥስ ከሆነ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው ተገበያዩ ዉስጠ-ደንብ በመጣሱ መቀጫ እንዲከፍል ለማዘዝ ይችላል፡፡

፵፪. <u>የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ</u>

፩/ የሚከተሉት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት መመዝገብ አለባቸው፡-

ሀ) ለህዝብ ሽያጭ የሚቀርቡ፤ እና

ለ) በአውጪዎቻቸዉ ፈቃድ ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የማስተላለፍ ዉክልና የተሰጡ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት የሕዝብ ኩባንያዎች እና ሌሎች የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች የሚያወጡትን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዓይነትና የሰነዶቹን ባለቤቶች መረጃ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

4/ When proposing new rules or amendments, the Security Depository and Clearing Company shall provide the Authority with the reasons and objectives of the proposed new rules or amendments, and highlight the desired effects.

5/ The Authority may approve, disapprove or amend new rules and amendments under Sub-Article (4) of this Article, and inform the Security Depository and Clearing Company in writing of its resolution within at latest one week of the resolution date.

6/ In case of noncompliance by any trader with the clearing rules, the Security Depository and Clearing Company may penalize that trader to pay the charges resulting from his noncompliance.

42. <u>Securities Registration</u>

1/ The following securities shall be registered at a central securities depository:

a) Publicly offered securities; and

b) Other securities, the issuers of which authorize the Securities Depository and Clearing Company to act as their transfer agents.

2/ Public companies and other issuers under Sub-Article (1) of this Article shall register the types of their securities and information on owners of the securities at the Central Securities Depository.

፵፫. ስለ ጥበቃ እና ሪከርድ አያያዝ

፩/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ በግምጃ ቤቱ ውስጥ ለተቀመጡት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ተገቢውን ጥበቃ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ግዑዝ-አልባ ተደርገው ከተቀመጡት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር በተያያዘ የሚደረጉ የባለቤትነት ለውጦችን በኮምፒዩተር የተደገፈ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት በመፍጠር በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መመዝገብ እና መያዝ አለበት፡፡

፫/ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው የሚይዛቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤትነት መዝገቦች በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በሚዘጋጅ ባለቤትነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚመዘገብበት የሂሳብ መዝገብ ስርዓት መተካት አለበት፡፡

፬/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተጠቀሰውን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ የምስክር ወረቀት የሚተካ እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ለመገበያየት፣ በጠቅላላ ጉባኤ ለመሳተፍ፣ የወለድ እና የትርፍ ክፍያ ለማድረግ፣ለመልሶ የመግዛት ውል እና ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማበደር፣ ለማስያዝ እና በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡት ደንቦች ወይም መመሪያዎች መሠረት የቅድሚያ እና ሌሎች መብቶችን ለመጠቀም የሚያስችል ሁሉን አቀፍ የምስክር ወረቀት ያዘጋጃል፡፡

፭/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ግዑዝ-አልባ የተደረጉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ኤሌክትሮኒክ የባለቤትነት ሪከርዶችን ይይዛል፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች፣ ባለቤቶች እና

43. Custody and Record keeping

1/ The Security Depository and Clearing Company shall provide custody and safekeeping for securities immobilized at its vaults.

2/ The Security Depository and Clearing Company shall create a computerized book-entry system to record changes of ownership electronically, using a computerized book-entry system, for securities that are dematerialized.

3/ The records of securities ownership maintained by the issuer shall be replaced with electronic records of securities ownership in the book-entry register maintained by the central securities depository.

4/ The Security Depository and Clearing Company shall create a global certificate to replace the securities certificates under Sub-Article (3) of this Article, for purposes of dealing, attending the general assembly, making interest and dividend payments, securities lending and repurchase agreements, pledging the security, and using priority and other rights, according to the provisions stipulated by this Proclamation and related regulations or directives issued in execution thereof.

5/ The Security Depository and Clearing Company shall maintain and update electronic ownership records of dematerialized securities and responds to inquiries of issuers, owners and other

ሌሎች ጥቅም አለን የሚሉ አካላት ለሚያቀርቡት ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል፡፡

፮/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የተሟላ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ምዝገባ ለማድረግ፣ ዝውውር ለማከናወን፣ እና ተያያዥ መረጃዎችን ለመቀበል እንዲሁም ከተውሶ ስሞች እውነተኛ የሰነድ ባለቤቶችን ስሞች፣ እና የባለቤትነታቸውን መጠን ለመያዝ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምነውን ሁሉ ለማድረግ ይችላል፡፡

፵፬. ክፍያ እና ርክክብ

፩/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አባላቱ ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ጋር ተያይዞ ያለባቸውን መብት እና ግዴታ በማጣራት በአባላቱ ስም ግዴታዎችን ይፈጽማል፡፡

፪/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ግዴታዎችን የሚፈጽመው ለእያንዳንዱ ርክክብ ክፍያዎችን በመፈጸም ነው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ግብይት በሚፈጸምበት ቀንና ክፍያና ርክክብ በሚደረግበት ቀን መካከል የሚኖረው ጊዜ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው በሚያወጣው ዉስጠ-ደንብ ከተቀመጠው ጊዜ መብለጥ የለበትም፡፡

፬/ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አባላት መካከል የሚደረግ የርክክብ እና ክፍያ ግዴታዎች አፈጻጸም በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በሚያዝ የሰነዶች ሂሳብ መዝገብ ውስጥ ገቢና ወጪ በማድረግ ይከናወናል፡፡

interested parties.

6/ The Security Depository and Clearing Company shall carry out all tasks it deems appropriate for the completion of securities registration, transfer of ownership of securities, and recording of related data, including obtaining from nominees the names of beneficial owners and their ownership of securities.

44. Clearing and Settlement

1/ The Security Depository and Clearing Company shall clear securities transactions for the account of its members to determine the rights and liabilities of every member.

2/ The Security Depository and Clearing Company shall settle securities transactions by delivery versus payment.

3/ The period between the trade date and settlement date of a transaction under Sub-Article (2) of this Article may not exceed the period specified by the Security Depository and Clearing Company rules.

4/ The discharge of settlement obligations between Security Depository and Clearing Company members shall be effected by book-entry made by the central securities depository on securities accounts opened on the book-entry register.

https://ethiodata.et/

፭/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባለቤትነት ከግብይቱ የሚመነጨው የክፍያና ርክክብ ግዴታ ሳይፈጸም ሊተላለፍ አይችልም፡፡

፮/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ውስጠ-ደንቦች፡-

ሀ) የርክክብ እና ክፍያ አፈጻጸምን በተመለከተ የሚተገበሩ የአሰራር ደንቦችን እና አካሄዶችን መደንገግ አለባቸው፤ እና

ለ) በራሱ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ላይ እና በኩባንያው ውስጥ በሚሳተፉ አባላት ላይ ሁሉ አስገዳጅ እና ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፵፭. <u>የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤትነት መተላለፍ የመጨረሻ ስለመሆኑ</u>

፩/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤትነት ዝውውር የመጨረሻ ስለመሆኑ እና በመዝገብ ከገባ በኋላ እንደማይሰረዝ በአሰራር ውስጠ ደንቡ መደንገግ የአሰራር ውስጠ ደንቦችን ማውጣት እና ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ውስጠ-ደንቦችን ተከትሎ የተደረገና በሰነደ ሙዓለ ንዋይ መዝገብ የተመዘገበ የባለቤትነት ዝውውር ዕዳን መክፈል ባለመቻል፣ በመክሰር፣ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ በማዋቀር፣ በሞግዚት አስተዳደር ስር በመሆን፣ የንግድ ሥራን በማፍረስ ወይም መልሶ በማደራጀት፣ ወይም ተዛማጅነት ባለው በማናቸውም ሥነ ሥርዓት ሊሰረዝ፣ ሊቀየር፣ ወይም ውድቅ ሊደረግ የማይችል የመጨረሻ፣ እና የሰነዱን መተላለፍ ለማገድ በሚወጣ ማናቸውም የአስተዳደራዊ መስሪያ ቤት ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊታገድ የማይችል ነዉ፡፡

5/ The ownership of securities shall not be transferred before the settlement and clearing of their transaction.

6/ The Security Depository and Clearing Company rules shall:

a) specify the operations and relevant procedures pertaining to the clearing and settlement of securities; and

b) be valid and binding on all participants of the central securities depository itself and any other party participating in the central securities depository.

45. <u>Finality of Securities Ownership Transfer</u>

1/ A Securities Depository and Clearing Company shall specify in its rule the finality of securities transfer and the irrevocability of orders once these have entered into the books of the system.

2/ The book-entry that has been effected in terms of rules issued under Sub-Article (1) of this Article shall be final and may not be revoked, reversed, or set aside, including, without limitation, by insolvency, bankruptcy, preventive restructuring, placement under receivership, winding up or reorganization or any related proceeding, and is not subject to any provision of law or order of an administrative or judicial authority that operates as a stay of that securities transfer.

፫/ ባለስልጣኑ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት፣ ክፍያ፣ ማቻቻል እና ፣ የኪሳራ ክፍፍል እና አመዳደብ የመጨረሻ ስለሚሆንበት አግባብ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

3/ The Authority may issue directives to prescribe finality of a securities trade, settlement, netting, and loss allocation and apportionment.

፵፮. <u>የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አባል መፍረስ ወይም የመክሰር ሥነ ሥርዓት ውስጥ መግባት</u>

ተቃራኒ የሆኑ ማናቸውም የሕግ ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አባል ዕዳን መክፈል ካለመቻል፣ ከመክሰር፣ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ከማዋቀር፣ በሞግዚት አስተዳደር ስር ከመሆን፣ የንግድ ሥራን ከማፍረስ ወይም መልሶ ከማደራጀት ጋር፣ ወይም ተዛማጅነት ካለው ማናቸውም ሥነ ሥርዓት ጋር በተያያዘ፣ አግባብነት ያለው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ኮፒ ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ ፈጻሚ ኩባንያ ከመቅረቡ በፊት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፭ መሠረት የመጨረሻ እና የማይሻርን በሂሳብ መዝገብ ወጪና ገቢ መደረግ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ መተላለፍ ላይ ምንም ውጤት አይኖረውም፡፡

46. <u>Winding Up or Placement in Bankruptcy Proceeding of a Securities Depository and Clearing Company Member</u>

Notwithstanding any provision of law to the contrary, the insolvency, bankruptcy, preventive restructuring, placement under receivership, winding up or reorganization or any related proceeding of a securities depository and clearing company member shall not affect the finality or irrevocability of any book-entry or securities transfer which became final and irrevocable in accordance with Article 45 of this Proclamation before the copy of the relevant order or decision was lodged with the securities depository and clearing company.

፵፯. <u>ሀብት አጣሪዎች ላይ ተፈጻሚ ስለሚሆኑ ውስጠ-ደንቦችና ስርዓቶች</u>

ዕዳን መክፈል ካለመቻል፣ ከመክሰር፣ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ከማዋቀር፣ በሞግዚት አስተዳደር ስር ከመሆን፣ የንግድ ሥራን ከማፍረስ ወይም መልሶ ከማደራጀት ጋር፣ ወይም ተዛማጅነት ካለው ማናቸውም ሥነ ሥርዓት ጋር ተያያዥ የሆኑ ማናቸውም ተቃራኒ የሕግ ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አባል ቢፈርስ፣ መክሰሩ ቢታወጅበት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ዉጤት

47. <u>Arrangements and Rules Binding Liquidators</u>

Notwithstanding any provision of law to the contrary relating to insolvency, bankruptcy, preventive restructuring, placement under receivership, winding up or reorganization or any related proceeding, if a securities depository and clearing company member is wound up or declared bankrupt by court or any proceeding that has a similar effect, any arrangement in relation to the securities depository and clearing company or any

ያለዉ የፍርድ ቤት ውሳኔ ቢሰጥበት፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያዉ ጋር የተያያዘ አደረጃጀት ወይም በኩባንያው ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ማናቸውም የማቻቻያ ደንቦች ወይም ልምዶች፣ የኪሣራ ማመልከቻ ባስገባና ባለገንዘቦች ሕጋዊ መብት ያቋቋሙበትን መያዣ በያዘ ሰው፣ በመልሶ የማደራጀት ኃላፊ፣ በንብረት ጠባቂ፣ በሞግዚት አስተዳዳሪ፣ በሂሣብ አጣሪ ወይም በሂደቱ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ባለ ተመሳሳይ አስተዳዳሪ ላይ አስገዳጅነት ይኖራቸዋል፡፡

፵፰. **ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዝውውር እና ክፍያ ግዴታ የሚሰጥ መያዣ**

፩/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ወይም አባላቱ ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዝውውር ወይም በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ ስራ ጋር በተያያዘ ለተፈጠረ ግዴታ በተሰጠ መያዣ ላይ ያላቸው ግዴታዎች፣ መብቶች፣ እና ጥቅሞች፡-

ሀ) ዕዳን መክፈል ካለመቻል፣ ከመክሰር፣ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ከማዋቀር፣ በሞግዚት አስተዳደር ስር ከመሆን፣ የንግድ ሥራን ከማፍረስ ወይም መልሶ ከማደራጀት ጋር፣ ወይም ተዛማጅነት ባለው ማናቸውም ሥነ ሥርዓት ወይም በማናቸውም የፍርድ ቤት ስልጣን፣ በመልሶ የማደራጀት ኃላፊ ወይም በከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂ ሊደናቀፉ፤ ወይም

ለ) በማናቸውም ባለገንዘቦች በማያዣው ላይ ያላቸውን መብት ወይም መፍትሔዎች እዳይሰሩበት በሚያደርግ የእገዳ ድንጋጌ ወይም ትዕዛዝ ሊገደቡ፤

አይችሉም፡፡

netting rules or practices applicable to the securities depository and clearing company, shall be binding upon the debtor-in-possession, supervisor, trustee, receiver, liquidator or similar administrator the proceedings.

48. Collateral for Securities Transfer and Settlement Obligation

1/ The obligations, rights and remedies of a securities depository and clearing company or its members on a securities transfer or eligible contract, or collateral granted to it as security for a securities transfer or the performance of an obligation incurred in a securities depository and clearing company may not be:

a) affected by insolvency, bankruptcy, preventive restructuring, placement under receivership, winding up or reorganization or any related proceeding or any power of the court, a supervisor in reorganization or a trustee in bankruptcy; or

b) the subject of any stay provision or order affecting the ability of creditors to exercise rights and remedies on the collateral.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት ዕዳን መክፈል ካለመቻል፣ ከመክሰር፣ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ከማዋቀር፣ በሞግዚት አስተዳደር ስር ከመሆን፣ የንግድ ሥራን ከማፍረስ ወይም መልሶ ከማደራጀት ጋር፣ ወይም ተዛማጅነት ካለው ማናቸውም ሥነ ሥርዓት ጋር በተያያዘ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አባል በቀረበ መያዣ ላይ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ከማናቸውም የይገባኛል ጥያቄዎች ሁሉ ቅድሚያ መብት አለው፤ እንዲሁም በዚያው መያዣ ላይ የኩባንያው ሌሎች አባላት የይገባኛል መብት ከሶስተኛ ወገን አበዳሪዎች የይገባኛል መብት ይልቅ ቅድሚያ አላቸው፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ከመዝጊያ ማቻቻያ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ብቁ የሆኑ ተጓዳኝ ወገኖችን እና ተገቢነት ያላቸውን ውሎች ወይም ግብይቶች እና ተፈጻሚ የሚሆኑትን መስፈርቶች በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

፵፱. በመዝገብ የገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መገበያየት የተከለከለ ስለመሆኑ

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ባለስልጣኑ ከፈቀደለት ዓላማ እና አግባብ ውጭ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ መዝገብ የተመዘገቡ ሰነዶችን በራሱ ስም ሊገዛ፣ ባለቤት ሊሆን ወይም ሊገበያይባቸው አይችልም፡፡

፶. ስለተዋዋይ ወገኖች ስለማሳወቅ

ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲከሰቱ በፍጥነት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡-

2/ In the case of insolvency, bankruptcy, preventive restructuring, placement under receivership, winding up or reorganization or any related proceeding under Sub- Article (1) of this Article, the security depository and clearing company claims against collateral provided by its member shall have priority over all other claims, and the claims of other members to that same collateral should have priority over the claims of third-party creditors.

3/ The Authority may determine, by a directive, eligible counter parties to benefit from the close-out netting regime and eligible contracts or transactions and requirements thereof.

49. Prohibition in Dealings in Book-Entry Securities

A Securities Depository and Clearing Company shall not purchase, acquire, or deal in book-entry securities as principal other than for a purpose and in a manner that may be permitted by the Authority.

50. Reporting on Counterparties

The Security Depository and Clearing Company shall inform the Authority at the earliest of the following:

፩/ በሌላ ወገን ያለ ማንኛውም ግዴታ ፈጻሚ በርክክብና ክፍያ ክንዋኔ ላይ ተፈጻሚ የሆኑ የትኛውንም ውስጠ-ደንቦች አለማክበሩን የደረሰበት እንደሆነ፤

፪/ በሌላ ወገን ያለ ግዴታ ፈጻሚ የገንዘብ አቋም እና ግዴታዎቹን የመፈጸም አቅሙ የመዋዠቅ ምልክት እያሳየ መምጣቱ ወይም የማያስተማምን መሆኑን ሲገምት፡፡

፶፩. **ስራን ስለማስቀጠል እና ከአደጋ ተመልሶ ስለማገገም**

፩/ በገበያው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል አደጋ፣ ቀውስ ወይም መረበሽ ሲያጋጥም ባለስልጣኑ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያውን ውስጠ-ደንቦቹን እንዲያሻሽል ወይም እንዲያግድ ለማዘዝ ይችላል፡፡

፪/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከባለስልጣኑ የተሰጠውን ትዕዛዝ ካላከበረ ባለስልጣኑ የግብይቶችን ፍትሃዊ አፈጻጸምና የተቀላጠፈ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይቶችን ወይም የተወሰነውን ክፍል ለማስቀጠል አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን እርምጃዎች ሊወሰድ ይችላል፡፡

፶፪. **በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ**

፩/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ፡-

ሀ) ከተፈቀደለት የሥራ ክልል ውጭ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ፤

1/ If it found that any of its counterparty became unable to abide by any of the rules applicable to operations of clearing and settlement.

2/ If it deemed that the financial position of counterparty and his ability to fulfil his obligations has given signs of instability, or his ability to fulfil his obligation has already become unstable.

51. **Business Continuity and Disaster Recovery**

1/ In case of disaster, crises and disturbance, which may result in substantial effects in the market, the Authority may direct the Security Depository and Clearing Company to amend or suspend any of its rules.

2/ If the Security Depository and Clearing Company fails to comply with the Authority's directions issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the Authority may take any procedure deemed necessary to maintain the fair settlement and efficiency of the commercial transactions of securities or any category thereof.

52. **Administrative Measures Against a Security Depository and Clearing Company**

1/ The Authority may suspend the license of a Securities and Clearing Company for such period or until the occurrence of such event as the Authority may specify if the company:

a) carries out any activity outside the scope of approved activities;

ለ) ፈቃድ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሁኔታዎችን ጥሶ ከተገኘ ወይም ካላከበረ፣

ሐ) በባለሥልጣኑ የተሰጠውን መመሪያ ካላከበረ፣

መ) በባለሥልጣኑ የተጠየቀውን መረጃ ካልሰጠ፣

ሠ) ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ከሰጠ፣ ወይም

ረ) የዚህን አዋጅ ወይም አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦች ወይም መመሪዎች ድንጋጌ ጥሶ ከተገኘ፣

ባለስልጣኑ ፈቃዱን ለተወሰነ ጊዜ ወይም ባለሥልጣኑ የሚወስነው ሁኔታ እስከሚፈጸም ድረስ ሊያገደው ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ እገዳ ከ፫ (ሦስት) ወራት መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ባለስልጣኑ ከሦስት ወራት ላልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዳበቃ ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ ባመነው መሠረት እገዳውን ማንሳት ወይም ፈቃዱን መሰረዝ አለበት፡፡

፬/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ፣

ሀ) ወደ ሀብት ማጣራት ውስጥ ከገባ ወይም ሂሣቡ ተጣርቶ እንዲዘጋ ትዕዛዝ ከተሰጠ፣

ለ) ለፈቃዱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ፣

b) has contravened or failed to comply with any condition applicable in respect of the license;

c) fails to comply with a direction of the Authority;

d) fails to provide the Authority with such information as it may require;

e) provides false or misleading information; or

f) is in breach of any other provision under this Proclamation or regulations or directives issued thereunder.

2/ A suspension of a license under Sub-Article (1) of this Article shall not exceed a period of 3 (three) months; the Authority, if deemed necessary, may extend the suspension for a further period not exceeding three months.

3/ The Authority shall, at the expiry of the suspension period specified under Sub-Article (2) of this Article, lift the suspension or revoke the license, as the Authority considers appropriate.

4/ The Authority may revoke the license of a Security Depository and Clearing Company if the company:

a) goes into liquidation or an order is issued for its winding up;

b) fails to rectify the failings that led to the suspension of its license within the specified time given by the Authority;

ሐ) ፈቃዱን ለመመለስ ካመለከተ እና ማመልከቻዉ ተቀባይነት ካገኘ፤

መ) ከዚህ በፊት የፈቃድ እግድ ያስከተለበትን ጥፋት ደግሞ ከሰራ፤ ወይም

ሠ) በሌላ በማናቸውም ምክንያት ፈቃዱን ይዞ ለመቀጠል ብቁ እና ተገቢ ሆኖ ካልተገኘ፤

ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ሊሰርዝበት ይችላል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ፈቃዱን ለመሰረዝ ከመወሰኑ በፊት ባለፈቃዱ ተቃውሞ ካለው ተቃውሞውን በደብዳቤ እንዲያቀርብ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፮/ ባለፈቃዱ ያቀረበው ተቃውሞ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ወይም የባለሥልጣኑ ማስታወቂያ ደብዳቤ በደረሰው በ ፴ (ሰላሣ) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካላቀረበ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

፯/ ባለሥልጣኑ የኩባንያውን ፈቃድ የሰረዘበትን ውሳኔ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እንዲታተም ያደርጋል፡፡

፰/ የፈቃዱ መሰረዝ ውሳኔ በጋዜጣ ከወጣበት ወይም ባለሥልጣኑ ከሚወስነው ሌላ ማናቸውም ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

፶፫. <u>የመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች</u>

፩/ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ወይም ሌሎች ተቃራኒ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ብሔራዊ ባንክ የሚከተሉትን ለማድረግ ብቸኛ ስልጣን ይኖረዋል፡-

c) has requested to return its license and its request is accepted by the Authority;

d) has committed a violation that has led to suspension of its license in the past; or

e) for any other reason, is no longer a fit and proper person to hold the license.

5/ The Authority, before deciding to revoke the license pursuant to Sub-Article (4) of this Article, shall notify the licensed person by a letter to submit his objection in writing, if any.

6/ If the objection of the licensed person is not found to be satisfactory or the licensed person fails to submit his objection within 30 (thirty) days of receipt of Authority's letter, his license shall be revoked.

7/ The decision to revoke the license of an Exchange shall be published by the Authority in a newspaper of wide circulation.

8/ The revocation of license shall become effective on the date of its publication or on any other date as the Authority may specify.

53. <u>Government Securities</u>

1/ Notwithstanding the provisions of this Part and any provisions to the contrary, the National Bank of Ethiopia shall have an autonomous power to:

https://ethiodata.et/

ሀ) ለመንግስት ሰነዶች ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤትን የማቋቋም፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ስራውን የማካሄድ፣ የመጠቀም እና የመቆጣጠር፤

ለ) የመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ አልባ ተደርገው ስለሚቀመጡበት ሁኔታ መመሪያ የማውጣት፤

ሐ) ከማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ፣ ከክፍያ ማጣራትና አፈጻጸም፣ ከርክክብ፣ እና ከመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ጋር የተያያዙ ውስጠ ደንቦችንና ውስጣዊ መመሪዎችን የማውጣት፤ እና

መ) በራሱ የማዕከላዊው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት የመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የመመዝገብ፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተገለጸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤትነት መተላለፍ የመጨረሻ ስለመሆኑ እና በአንቀጽ ፵፰ መሰረት ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ መተላለፍ እና ክፍያ ዋስትና ስለተሰጡ መያዣዎች የተደነገጉት እንደ አግባብነቱ ለመንግስት ሰነዶችም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፶፬. ልዩ ስልጣን

በዚህ አዋጅ በተቃራኒ የተደነገጉ ማናቸውም ድንጋጌዎች ቢኖሩም ባለስልጣኑ ከልዩ የውለታ ቃሎች እና ሁኔታዎች ጋር ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ግብይት ለሚደረግባቸው የግል ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሰነድ ማስቀመጥ እና ክፍያ የማጣራትና የመፈጸም ስራን እንዲሰራ ስልጣን ሊሰጠው ይችላል፡፡

a) Establish, own, operate, participate and regulate central securities depository for Government securities;

b) Issue directives to determine manner of dematerialization and immobilization of Government securities;

c) Issue directives and rules related to the operations of central securities depository, clearing, settlement and registration of Government securities; and

d) Register government securities at its central securities depository.

2/ Finality of securities transfer provided under Sub-Articles (1) and (2) of Article (45) and provisions of collateral for securities transfer and settlement obligations under Article 48 of this Proclamation as the case may appropriate shall apply *mutatis mutandis* to Government securities.

54. Special Authorization

Notwithstanding any provisions of this Proclamation to the contrary, the Authority may, with special terms and conditions, authorize the National Bank of Ethiopia to provide securities depository and clearing services to private securities traded at the securities exchange.

ክፍል ስድስት
ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ ስለመስጠት

፶፭. ቁጥጥር የሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ተግባራትና አገልግሎቶች

፩/ የሚከተሉት የካፒታል ገበያ ተግባራት በዚህ አዋጅ መሰረት ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡-

ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መግዛት፣ መሸጥ እና ማሻሻጥ፣

ለ) የኢንቨስትመንት ምክር፣

ሐ) የውክልና ሽያጭ፣

መ) የፈንድ አስተዳደር፣

ሠ) ከግዥ፣ ከመዋሃድ፣ አንድ ድርጅት የራሱ በሆነ ሌላ ድርጅት ውስጥ ያለውን ድርሻ ከመሸጥ ከመጣመር እንዲሁም ሌሎች ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መግዛትና መሸጥ የሚጠይቁ የድርጅት ገንዘብ አስተዳደር ተግባራት፣

ረ) ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የመጠበቅ እና የማስተዳደር አገልግሎቶች፣

ሰ) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች፣

ሸ) የብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎቶች፤ እና

ቀ) ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ቁጥጥር ይደረግባቸዋል ብሎ የሚቆጥራቸው ሌሎች ተግባራት::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ) ሰነደ ሙዓለ ንዋይን በተመለከተ የተሰጠው ምክር በመደበኛ ሥራቸው ሂደት እስካጋጠማቸው ድረስ በሚከተሉት ሰዎች ተፈጻሚ አይሆንም፡-

ሀ) በሚመለከተው የመንግስት አካል በተመዘገበና ዕውቅና በተሰጠው የህግ ባለሙያ፤ወይም የጥብቅና ሙያ ድርጅት፤

PART SIX
LICENCING OF CAPITAL MARKET SERVICE PROVIDERS

55. Regulated Capital Market Activities and Services

1/ The following capital market activities shall be regulated under this Proclamation:

a) buying, selling and dealing in securities,

b) investment advice,

c) underwriting,

d) fund management,

e) corporate finance advice relating to acquisitions, mergers, divestures, combinations and other activities that involve buying, selling, and exchanging securities,

f) custodial services,

g) collective investment schemes,

h) credit rating services, and

i) any other activity deemed by the Authority as a regulated activity pursuant to this Proclamation.

2/ Sub-Article (1) (b) of this Article shall not apply to any of the following persons, to the extent that the advice in securities to others is incidental to the ordinary course of their business:

a) A legal practitioner or a law firm registered and recognized by pertinent government organ;

https://ethiodata.et/

ለ) በሚመለከተው የመንግስት አካል በተመዘገበና ዕውቅና በተሰጠው የሒሳብ ባለሙያ ወይም ኦዲተር፤ እና

ሐ) ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር በተያያዘ ትንተናዎች ወይም ሪፖርቶች ላይ የሚሰጥ ምክር ታትሞ ለህዝብ የሚቀርብበት እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በተመለከተ የተሰጠው ምክር በመደበኛ የሥራቸው ሂደት ሊያጋጥማቸው የሚችሉ የጋዜጣ፣ የመጽሄት ወይም የሌሎች ወቅታዊ ህትመቶች አታሚዎችና አሳታሚዎች፡፡

፫/ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ተግባራት ሊከናወኑ የሚችሉት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ፈቃድ በተሰጣቸው በሚከተሉት ሰዎች ብቻ ነው፡-

ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላዎች፣

ለ) የኢንቨስትመንት አማካሪዎች፣

ሐ) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኞች፣

መ) የኢንቨስትመንት ባንክ፣

ሠ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ አከናዋኞች፣

ረ) የውክልና አስተዳዳሪዎች/ባላደራዎች፣

ሰ) ገበያ ከፋቾች፣

ሸ) ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲዎች፣

ቀ) የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ተሿሚ እንደራሴ፣ እና

በ) ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ዓላማዎች መሠረት ሊተዳደር የሚገባው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሥራ ነው ብሎ በሚፈርጀው ተግባር የሚሰማራ ወይም የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው፡፡

b) A public accountant or public auditor registered and recognized by pertinent government organ; and

c) The printer or publisher of a newspaper, magazine or other periodicals in which advice, in regard to securities analyses or reports are published to the public and the advice in regard to securities is incidental to the ordinary course of a business of the printer or publisher, as the case may be.

3/ Regulated capital market activities shall only be undertaken by the following persons who hold a capital market services license for that activity:

a) Securities Broker,

b) Investment Adviser,

c) Collective Investment Scheme Operator,

d) Investment Bank,

e) Securities Dealer,

f) Custodian,

g) Market Maker,

h) Credit Rating Agency,

i) Appointed representative of a capital service provider, and

j) Any person who conducts or participates in any activity that is deemed by the Authority to be an activity in securities to be regulated in accordance with the purposes of this Proclamation.

፬/ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ፈቃድ የብቁነትን እና የተገቢነት መሥፈርትን፣ ዝቅተኛውን የካፒታል መጠን፣ የውስጥ አደረጃጀት እና የአደጋ ስጋት አስተዳደር እንዲሁም በባለሥልጣኑ መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች የቁጥጥር እና የበላይ ክትትል መሥፈርቶችን ለሚያሟላ ማንኛውም ሰው ይሰጣል፡፡

፭/ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ሥራዎች ለመሠማራት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሕግ ጥሰትን ለመከላከል፣ ለመመርመር እና ለማረም የሚያስችል የሕግ ማስከበሪያ ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

፮/ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ሥራዎች ለመሠማራት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው አባል የሆነበት ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ለሚያወጣቸው ውስጠ-ደንቦችና ውስጣዊ መመሪያዎች ተገዢ መሆን አለበት፡፡

፯/ በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ስም ቁጥጥር የሚደረግበትን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሥራ የሚሠራ ሰው ፍቃድ ያለው ተሿሚ እንደራሴ መሆን አለበት፡፡

፰/ የተሿሚ እንደራሴነት ፍቃድ ለማውጣት መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች ባለስልጣኑ በመመሪያ ያወጣል፡፡

፱/ አንድ ሰው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የካፒታል ገበያ ተግባራት ላይ የመሠማራት ፍቃድ ሊሰጠው ይችላል፤ ባለስልጣኑ እንዲህ አይነት ፈቃድ የሚሰጥባቸውን የውሉታ ቃሎችን እና ሁኔታዎችን፣ እንዲሁም የአተገባበር መሥፈርቶችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

4/ The capital market services license is issued by the Authority to any person who satisfies the fit and proper criteria, minimum capital requirements, internal organization and risk management, and other regulatory and supervisory requirements to be determined by directive of the Authority.

5/ A person licensed to engage in regulated capital market activities shall establish a compliance system aimed at preventing, detecting, and correcting securities law violations.

6/ A person licensed to engage in regulated capital market activities shall comply with the rules and regulations of a self-regulatory organization to which it belongs.

7/ A person who conducts a regulated activity on behalf of a capital market service provider is required to be a licensed appointed representative.

8/ The Authority shall determine the requirements for obtaining license for appointed representative in a directive.

9/ A person may be licensed to perform two or more capital market activities; and the Authority shall determine the terms and conditions for granting such licenses, as well as the criteria for performing such activities in a directive.

፲/ ባለስልጣኑ በካፒታል ገበያ ሥራዎች ለመሠማራት ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ዓመታዊ ሪፖርትና ኦዲት የተደረገ የፋይናንስ መግለጫን ጨምሮ ሁሉንም ሥራዎቹን በተመለከተ በየጊዜው ሪፖርት እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

፲፩/ ከዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፲) ጋር በተያያዘ ባለስልጣኑ የካፒታል ገበያ ስራዎችን ለመስራት ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ሪኮርዶችን በሙሉ ሊገመግም፣ ሊያጣራ፣ የሪኮርዶችን ቅጂ ሊወስድ፣ ወይም ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ቅጂዎችን እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፶፮. <u>ብቁና ተገቢ ሰዎች</u>

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት፣ አንድ ሰው ብቁና ተገቢ መሆኑን ለመመዘን ባለስልጣኑ፡-

ሀ) የገንዘብ አቅምን፣

ለ) ፈቃድ ከሚያመለክትበት ሥራ ጋር ተያያዥ የሆነ በትምህርት ወይም በሌላ መንገድ የተገኘ ሙያዊ ብቃትን ወይም ልምድን፣

ሐ) ሊሰጥ ያሰበውን አገልግሎት በብቃት፣ በታማኝነትና በፍትሐዊነት የመፈጸም ችሎታን፤ እና

መ) የአመልካቹን መልካም ስም፣ ፀባይ፣ በገንዘብ አለመታለል እና ታማኝነትን፤

ከግንዛቤ ያስገባል፡፡

፪/ ለዚህ አዋጅ ዓላማዎች ባለስልጣኑ የብቁነትና የተገቢነትን መመዘኛዎች ሲመረምር በአመልካቹ የቀረበለት ቢሆንም ወይም ባይሆንም በእጁ ያለውን ማናቸውንም መረጃ ከግንዛቤ ሊያስገባ ይችላል፡፡

10/ The Authority may request from persons licensed to engage in capital market activities to submit periodic reports on all their activities, including annual reports and audited financial statements.

11/ In relation to Sub-Article (10) of this Article, the Authority may review and check all of the records of a person licensed to engage in capital market activities, and may take copies of these records or request a licensed person to submit copies thereof.

56. <u>Fit and Proper Persons</u>

1/ For purposes of this Proclamation, in considering whether a person is a fit and proper person, the Authority shall have regard to the:

a) Financial status;

b) Educational or other qualifications or experience with respect to the nature of the application;

c) Ability to perform his proposed function efficiently, honestly and fairly; and

d) Reputation, character, financial integrity and reliability of the applicant.

2/ For the purposes of this Proclamation, the Authority may have regard to any information in the possession of the Authority, whether furnished by the applicant or not in considering the fit and proper requirement.

https://ethiodata.et/

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) ማመልከቻ ከቀረበበት ሥራ ጋር በተያያዘ በአመልካቹ የተቀጠረ፣ ሊቀጠር የታሰበ ወይም ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው፤

ለ) ሥራውን በሚመለከት እንደ ተወካይ ሆኖ የሚያገለግልን ማንኛውንም ሰው፤

ሐ) አመልካቹ ኩባንያ ከሆነ ማናቸውም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን፣ የኩባንያው ዳይሬክተር ወይም ሥልጣን ያለውን ሠራተኛ፣ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ ካሉ ኩባንያዎች መካከል የሚመደብ ሌላ ኩባንያ፣ ወይም የኩባንያው ዳይሬክተር ወይም ሥልጣን ያለው ሠራተኛ፤ እና

መ) አመልካቹ የውጭ ሀገር ኢንቨስተር ከሆነ፣ ኢንቨስተሩ በሃገሪቱ የኢንቨስትመንት ህግ የተደነገገውን ዝቅተኛ መሥፈርት የሚያሟላ መሆኑን፤

ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከኩባንያው ጋር በተያያዘ ‹‹ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን›› ማለት በኩባንያው ውስጥ ባሉ አክሲዮኖች ጥቅም ያለው ሆኖ፡-

ሀ) መደበኛ የአክሲዮን ድርሻው ከኩባንያው ካፒታል አምስት በመቶ (5%) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ፤ ወይም በባለስልጣኑ መመሪያ የሚወሰን ሌላ መቶኛ(ፐርሰንት) ያለው፤ ወይም

3/ For the purpose of Sub-Article (1) of this Article, the Authority may take into account any matter relating to:

a) Any person who is or is to be employed by, or associated with, the applicant for the purposes of the proposed business to which the application relates;

b) Any person who will be acting as a representative in relation to such business;

c) Where the applicant is a company, any substantial shareholder, director or officer of the company, any other company in the same group of companies or to any director or officer of any such company; and

d) Where the applicant is a foreign investor, whether that investor meets the minimum requirements for foreign investors stipulated under Investment law of the country.

4/ A “substantial shareholder” in Sub-Article (3) of this Article means, in relation to a company, a person who has an interest in shares in the company:

a) The nominal value of which is equal to or more than five percent (5%), or such other percentage as the Authority may determine by a directive, of the issued share capital of the company; or

ለ) ለባለአክሲዮኑ የአምስት ከመቶ (5%) ወይም ባለስልጣኑ የሚወስነውን ሌላ የመቶኛ ባለድርሻ መብት የሚያሰጠው፣ ወይም የነዚህን ያህል ባለድርሻዎችን መብት የመቆጣጠር ስልጣን የሚያሰጠው፤

ነው፡፡

፶፯. የፈቃድ ማመልከቻ

፩/ ፈቃድ ለማግኘት ለባስልጣኑ የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በሚዘጋጀው ቅጽ ተሞልቶ፣ ከሚጠየቀው ክፍያ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

፪/ ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ከሆነ፣ አስቀድሞ የተሰጠው ፈቃድ ጊዜው ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት፡፡

፫/ አመልካቹ ባለስልጣኑ ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ እንዲቀርብ የሚፈልገውን ማናቸውንም ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

፶፰. የፈቃድ ወይም የፈቃድ ጥያቄን ስለመከልከል

፩/ ቁጥጥር የሚደረግበት የካፒታል ገበያ ተግባርን ለማከናወን የፈቃድ ወይም ፈቃድ የማሳደስ ጥያቄ የሚያቀርብ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ፈፅሞ ከተገኘ ባለስልጣኑ ፈቃዱን ወይም የፈቃድ ዕድሳት ጥያቄዉን ሊከለክል ይችላል፡-

ሀ) አሳሳች መረጃ ለባለስልጣኑ ካቀረበ፤

ለ) ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክት ለባለሥልጣኑ ሊቀርብ የሚገባ ወሳኝ የሆነን ጉዳይ ወይም መረጃ ሳይገልጽ ከቀረ፤

b) Which entitles the person to exercise or control the exercise of five percent (5%) or such other percentage as the Authority may determine.

57. Applications for License

1/ An application for a license shall be made to the Authority in the prescribed form and shall be accompanied by the prescribed fee.

2/ In the case of an application for renewal of a license, such application shall be made not later than one month before the expiry of the license.

3/ The applicant may be required to supply the Authority with such further information, in relation to the application, as the Authority considers necessary.

58. Refusal to Grant or Renew a License

1/ The Authority may refuse to grant or renew a license for a person to engage in regulated capital market activities, or any person related to it, if it were given evidence that the person has:

a) given misleading information;

b) omitted a material fact when applying for a license or failed to mention any other information that should be submitted to the Authority;

ሐ) የብቁነትና የተገቢነት መመዘኛን፣ አነስተኛውን የካፒታል መጠን፣ የውስጥ አደረጃጀትና የስጋት አመራርን እና በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ፈቃድ ለማግኘት የሚጠየቁ የቁጥጥር መስፈርቶችን ካላሟላ፤

መ) ከፈቃድ ጋር የተያያዘን ሥራ ለማከናወን የአዕምሮ ወይም የአካል ብቃት የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ፤ ወይም

ሠ) የዚህን አዋጅ ወይም አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌን ጥሶ መገኘቱ ከተረጋገጠ፡፡

፪/ ባለስልጣኑ ለአመልካቹ ወይም ለባለፈቃዱ የመሰማት ዕድል ሳይሰጥ ፈቃድ ሊከለክል ወይም አላድስም ሊል አይችልም፡፡

፶፱. ፈቃድን ስለማገድ

፩/ ቁጥጥር የሚደረግበት የካፒታል ገበያ ተግባርን ለማከናወን ፈቃድ ያለዉ ማንኛዉም ሰዉ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የተመለከቱትን የባለፈቃድ ግዴታዎችን ካልተወጣ፤

ለ) በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ካልሰጠ፤

ሐ) ፈቃዱ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሁኔታዎችን ወይም ገደቦችን ወይም የዚህን አዋጅና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌን ተላልፎ ወይም ጥሶ ከተገኘ፤

c) failed to meet the fit and proper criteria, minimum capital requirements, internal organization and risk management, and other regulatory and supervisory requirements for obtaining a license to be determined by directive of the Authority;

d) become incapable mentally or physically of performing the activities to which the licence relates; or

e) violated any provision of this Proclamation or Regulations or Directives issued thereunder.

2/ The Authority may not refuse to grant or renew a license without first giving the applicant or the holder of a license an opportunity of being heard.

59. Suspension of a License

1/ The Authority may suspend the license of any person engaged in regulated capital market activities on the grounds that the licensed person:

a) fails to discharge obligations of a licensed person as specified under this Proclamation or regulations or directives issued thereunder;

b) fails to provide timely and accurate information upon the request of the Authority;

c) violates or breaches any conditions or restrictions applicable in respect of the license or any other provision in this Proclamation or regulations or directives issued thereunder;

መ) ፈቃድ ከተሰጠው ወይም ፈቃዱ ከታደሰለት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ፲፪ (አሥራ ሁለት) ወራት ውስጥ ፈቃድ ያገኘበትን ሥራ ካላከናወነ፣ ወይም

ሠ) በሥራ የሚገናኛቸውን ወይም የበታች ሠራተኛውን የዚህን አዋጅና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎችን በሚጥስ መንገድ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ ካልቻለ፣

ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ የእገዳውን ምክንያት እና ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ለእገዳው ምክንያት የሆነውን ጉድለቶች ለማስተካከል መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች ለባለፈቃዱ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡

፫/ ባለስልጣኑ ለአመልካቹ ወይም ለባለፈቃዱ የመሰማት እና ፈቃዱ መታገድ እንደሌለበት ምክንያቱን በጽሁፍ እንዲገልጽ ዕድል ሳይሰጠው ፈቃዱን ሊያግድ አይችልም፡፡

፬/ ፈቃዱ በባለሥልጣኑ የታገደበት ማንኛውም ሰው የፈቃዱ እገዳው ከፀናበት ቀን ጀምሮ ቁጥጥር በሚደረግበት በማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ አይችልም፡፡

፷. ፈቃድን ስለመሰረዝ

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ ክፍል የተመለከተውን ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች መሰረዝ ይችላል፡-

ሀ) ፈቃዱ ሐሰተኛ ወይም የተሳሳተ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ፣

ለ) ባለፈቃዱ በራሱ ምርጫ ቁጥጥር የሚደረግበትን ሥራ ማከናወን ካቆመ፣

d) fails to carry out the activity for which the person was licensed for 12 (twelve) months following the granting or renewal of the license; or

e) fails to prevent one of his affiliates or subordinates from acting in a way that violates the provisions of this Proclamation or regulations or directives issued thereunder.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the Authority shall notify the licensed person in writing the cause of the suspension and measures need to be taken within reasonable period of time to rectify the shortcomings that led to the suspension.

3/ The Authority may not suspend a license without first giving the applicant or the holder of a license an opportunity of being heard.

4/ A person whose license has been suspended by the Authority shall be prohibited from engaging in any regulated activity starting from the effective date of suspension of its license.

60. Revocation of a License

1/ The Authority may revoke a license under this part on the following grounds:

a) it is confirmed that the license was obtained on the basis of false or wrong information;

b) the licensee ceases to carry out regulated activity by his own choice;

ሐ) ባለፈቃዱ ለፈቃዱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ፤

መ) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ላልተፈቀደ ተግባር ወይም ዓላማ ከተጠቀመበት፤

ሠ) ባለፈቃዱ ከዚህ በፊት የፈቃድ እግድ ያስከተለበትን ጥፋት ደግሞ ከሰራ፤ ወይም

ረ) ባለፈቃዱ ኪሣራ ከታወጀበት ወይም ክፍያ መክፈል ካቆመ፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃዱን ለመሰረዝ ከመወሰኑ በፊት ባለፈቃዱ ተቃውሞ ካለው ተቃውሞውን በደብዳቤ እንዲያቀርብ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፫/ ባለፈቃዱ ያቀረበው ተቃውሞ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ወይም የባለሥልጣኑ ማስታወቂያ ደብዳቤ በደረሰው በ፴ (ሰላሣ) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካላቀረበ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ የኩባንያውን ፈቃድ የሰረዘበትን ውሳኔ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እንዲታተም ያደርጋል፡፡

፭/ የፈቃዱ መሰረዝ ውሳኔው በጋዜጣ ከወጣበት ወይም ባለሥልጣኑ ከሚወስነው ሌላ ማናቸውም ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

፮/ ፈቃዱ ከተሰረዘ ወይም ባለፈቃዱ ግዴታውን መወጣት ካልቻለ፣ ባለሥልጣኑ በባለፈቃዱ ወይም በባለፈቃዱ ስም በሦስተኛ ሰው የተያዘን ሀብት በሌላ ሰው ይዞታ ሥር እንዲሆን ወይም ቁጥጥር እንዲደረግበት ባለፈቃዱን፤

c) the licensee fails to rectify the failings that led to the suspension of his within the specified time given by the Authority;

d) the licensee has utilized the license for unauthorised activity and purpose;

e) the licensee has committed a violation that has led to suspension of its license in the past; or

f) the licensee has been declared bankrupt or insolvent.

2/ The Authority, before deciding to revoke the license pursuant to Sub-Article (1) of this Article, shall notify the licensed person by a letter to submit his objection in writing, if any.

3/ If the objection of the licensed person is not found to be satisfactory or the licensed person fails to submit his objection within 30 (thirty) days of receipt of Authority's letter, his license shall be revoked.

4/ The decision to revoke the license of a licensed person shall be published by the Authority in a newspaper of wide circulation.

5/ The revocation of license shall become effective on the date of its publication or on any other date as the Authority may specify.

6/ In case of revocation a license or failure of a licensed person, the Authority may require the licensed person to:

ሀ) የደንበኛውን የባንክ ሂሣቦች ወደ ሌላ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አገልግሎት አቅራቢ እንዲያዛውር፤ እና/ወይም

ለ) ተቆጣጣሪ፣ ንብረት ጠባቂና አጣሪ ወይም ሌላ አስተዳዳሪ እንዲሾም፤

ሊያደርገዉ ይችላል፡፡

፷፩. የራሱን በራስ ተቆጣጣሪ ድርጅት አባል ስለመሆን

በዚህ ክፍል ለአመልካቾች የተሰጡት መብቶች ቢኖሩም፣ ባለስልጣኑ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፍቃድ ለማውጣት ወይም ለማሳደስ የራሱን በራስ ተቆጣጣሪ ድርጅት አባል እንዲሆኑ የሚያስገድድ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፷፪. የሒሳብ መዝገብ ቅኝት እና የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት

፩/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚመለከተው የመንግስት አካል በሚጠይቀው የሂሳብ አያያዝ ዘዴ መሠረት የሒሳብ መዝገብ ስርዓት መዘርጋት እና ከእርሱ ጋር የተያያዙ ግብይቶችን ወይም የባለቤትነት ዝውውሮችን በትክክልና በዝርዝር በሂሳብ መደቦች መመዝገብና መያዝ አለበት፡፡

፪/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው መዝገቦቹን፣ ሰነዶቹን እና የሒሳብ መግለጫዎችን ከተዘጋጁበት ቀን ጀምሮ ለ፲ (አስር) ዓመት ወይም ከደንበኛው ጋር ሙግት ውስጥ የገባበት ጉዳይ ካለ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የበለጠውን ያህል ጊዜ ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡ በዚህ ወቅትም ለምርመራ ከተፈለጉ መቅረብ አለባቸው፡፡

a) move clients' accounts to another capital market service provider; and/or

b) request the appointment of a monitor, receiver, curator or other administrator

to take possession or control of the assets held by a licensed person or a third party on behalf of the licensed person.

61. Membership to a Self-regulatory Organization

Notwithstanding the rights of applicants provided under this Part, the Authority may issue a directive requiring capital market service providers to be members of a self-regulatory organization as a requirement for the granting of license or for its renewal.

62. Review of Accounts and Internal Control procedures

1/ A licensed person shall establish and maintain books, records, and detailed and accurate accounts that reflect transactions or transfers of ownership of the assets related to such licensed person, in accordance with accounting standards set out by the pertinent government organ.

2/ A licensed person shall maintain the records, books and accounts for 10 (ten) years from the day of preparation thereof, or until any dispute between the licensed person and a client is resolved, whichever is higher, during which they should be available for review if requested.

፫/ የተጠቀሱት ሰነዶች በባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ ስራውን እንዲያከናውን በሚመድበው ማናቸውም ሰው በማናቸውም ጊዜ ፍተሻ ወይም ምርመራ ይካሄድባቸዋል፡፡

፬/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የደንበኞቹን ማንነት መዝግቦ የመያዝ፣ እንዲሁም ገንዘብና ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር በተያያዘ ከድለላ እና ከባንክ ሒሳቦች የገቡበትንና የወጡበትን ክትትል ለማድረግ በሚያስችል መልኩ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

፭/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሂሳብ መዝገብ ቅኝትን በተመለከተ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትና ለሚከተሉት ተገዢ መሆን አለበት፡-

ሀ) በበላይነት ለመከታተል ለስጋት አስተዳዳር እንዲሁም የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያስችሉ የዉስጥ መመሪያዎችንና አሠራሮችን ማዘጋጀት፤

ለ) ሥራዎችን ከሚመለከተው ክፍል በተገኘ አጠቃላይ ወይም ልዩ ፈቃድ መሠረት መፈጸም፤

ሐ) ከሚመለከተው ክፍል በተገኘ አጠቃላይ ወይም ልዩ ፈቃድ መሠረት ሀብት የማስወገድ ሂደት ነጻነትን ማረጋገጥ፤

መ) የተመዘገቡ ሀብቶችን፣ በአስፈላጊው ጊዜ በማስተያየት የጎላ ልዩነት ከታየ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፤ እና

ሠ) የሚመለከተው የመንግስት አካል ባስቀመጠው አሠራር መሠረት የፋይናንስ መግለጫ ማዘጋጀት በሚያስችል መልኩ ሂሳቦችን መመዝገብ፡፡

3/ These documents shall be subject to inspection and auditing at all times by the Authority or whoever is assigned by the Authority to do so.

4/ A licensed person shall maintain records concerning client identity and maintain records that permit tracing of funds and securities in and out of brokerage and bank accounts related to securities transactions.

5/ A licensed person shall establish an internal control system in relation to review of accounts, and abide by the following:

a) Develop guidelines and procedures for supervision, risk management and prevention of conflict of interests;

b) Execute the operations according to general or special authorization obtained from a relevant department;

c) Ensure independence of disposition of assets under general or special authorization from a relevant department;

d) Compare registered assets during appropriate periods of time and take the necessary actions towards any material changes; and

e) Record transactions to allow preparation of financial statements in accordance with the standards set out by a pertinent government organ.

፷፫. የዉጭ ኦዲተሮች ስያሜ

፩/ እያንዳንዱ ፈቃድ ያለው ሰው በባለስልጣኑ የፀደቀ የዉጭ ኦዲተር መሰየም አለበት፡፡

፪/ አንድ ሰው ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የውጭ ኦዲተር ሆኖ መሰየም የማይችልባቸው ሁኔታዎች፡-

ሀ) ለባለ ፈቃዱ ሰው የአክሲዮን ባለድርሻ፣ ዳይሬክተር ወይም ሰራተኛ ከሆነ፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ከተዘረዘሩት በአንዱ ምድብ ላለ ሰው የትዳር ጓደኛ ከሆነ ወይም በጋብቻም ሆነ በስጋ አንደኛ ደረጃ ዝምድና ካለው፤ ወይም

ሐ) የኦዲተሮቹ ድርጅት ባለድርሻ ወይም የኦዲት ቡድን አባል በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ሥር ከተጠቀሱት በአንዱ የሚወድቅ የሆነ እንደሆነ፡፡

፫/ ባለስልጣኑ ፈቃድ ለተሰጣቸው ግለሰቦች የውጭ ኦዲተር ሆነው ሊሰየሙ የሚችሉ ባለሙያዎች ሊኖራቸው ስለሚገባ ዝቅተኛ ሙያዊ ዕውቀትና ልምድ በየጊዜው መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

ክፍል ሰባት

የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት

፷፬. የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ስለማቋቋም

በባለስልጣኑ ውሳኔዎች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በይግባኝ መርምሮ የሚወስን የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት (ከዚህ በኃላ ‹‹አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት›› እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

63. Appointment of External Auditors

1/ Every licensed person shall appoint an External Auditor approved by the Authority.

2/ A person may not be qualified for appointment as an external auditor of a licensed person if:

a) he is a shareholder, director, or employee of the licensed person;

b) he is a spouse or relative by consanguinity or affinity to the first degree to a person falling within the categories provided under paragraph (a) of this Sub-Article; or

c) it is a firm of auditors of which any partner or auditing team falls within the categories provided under paragraph (a) or (b) of this Sub-Article.

3/ The Authority may issue directives from time to time on the minimum professional knowledge and experience required of external auditors appointed to perform audits of a licensed person.

PART SEVEN

CAPITAL MARKET TRIBUNAL

64. Establishment of the Capital Market Administrative Tribunal

The Capital Market Tribunal (hereunder the "Administrative Tribunal") is hereby established by this Proclamation to hear appeals against decisions of the Authority.

https://ethiodata.et/

፷፭. የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ስልጣን

አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ በባለስልጣኑ ወይም የባለስልጣኑን ተግባርና ስልጣን በሚያስፈጽም ሰው በተላለፈ ውሳኔ ላይ የቀረበን ይግባኝ የመስማትና የመወሰን ስልጣን አለው፡፡

፷፮. የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ አባላት ሹመት

፩/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አምስት አባላትን ለአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ይሾማሉ፡፡

፪/ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ አባላት ከሚከተሉት የተውጣጡ ይሆናሉ፡-

ሀ) የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ማገልገል የሚያስችል ብቃት ያላቸው ሆነው ከንግድ ሥራ ወይም ከፋይናንስ ወይም ከሒሳብ አያያዝ ጋር ተዛማጅነት ያለው የስራ ልምድ ያላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ፣ እና

ለ) የህግ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣ የንግድ ሥራ ወይም የፋይናንስ ወይም የሒሳብ አያያዝ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ሌሎች ሦስት አባላት::

፫/ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ አባል፡-

ሀ) የሙሉ ጊዜ ወይም የትርፍ ጊዜ አባል ተደርጎ ሊሾም ይችላል፤

ለ) የሹመቱ የመጀመሪያ የሥራ ዘመን ፭ (አምስት) ዓመት ሆኖ፣ ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን በድጋሚ ሊሾም ይችላል፤ እና

ሐ) በስራው በሚቆይበት ጊዜ ክፍያውና የሙያ አበሉ፣ መንግስት በሚወስነው መሰረት ይሆናል፡፡

65. The Jurisdiction of the Administrative Tribunal

The Administrative Tribunal shall have jurisdiction to hear and determine appeals of the decisions of the Authority or a person exercising the functions or powers of the Authority.

66. Appointment of Members of the Administrative Tribunal

1/ The Prime Minister shall appoint five members to the Administrative Tribunal.

2/ Members of the Administrative Tribunal shall constitute:

a) Chairperson and vice chairperson, who shall have similar qualifications to a person who is eligible to be a judge of the Federal High Court with relevant experience in securities, commerce, finance or accountancy; and

b) Three other members with knowledge and experience in law, securities, commerce, finance or accountancy.

3/ A member of the Administrative Tribunal:

a) may be appointed as either a full-time or part-time member;

b) shall be appointed for an initial term of five (5) years and shall be eligible for re-appointment for a further one term; and

c) shall hold office on such terms and conditions, including in relation to remuneration and attendance fees, as determined by the Government.

፷፯. ለአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ አባልነት ብቁ አለመሆን

አንድ ሰው፡-

፩/ መክሰሩ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠበት፣

፪/ የባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ ፈቃድ ለሰጠው ሰው ሰራተኛ ከሆነ፣ ወይም

፫/ በማንኛውም ህግ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ከ፮ (ስድስት) ወር የበለጠ እስራት ከተፈረደበት፣

የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ አባል መሆን አይችልም፡፡

፷፰. የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ አስተዳደር

፩/ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ የፍርድ ቤቱን አስተዳደራዊ ጉዳዮች ይመራል፡፡

፪/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር እና በሰብሳቢው የሚወሰን ሌሎች መሰል ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፷፱. የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ በጀት እና የሂሳብ መዝገብ

፩/ የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

፪/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የተሟላና ትክክለኛ የሒሳብ መዝገብ መያዝ አለበት፡፡

፫/ የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የሒሳብ መዝገቦችና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በፌደራል ዋና ኦዲተር በሚመደብ ኦዲተር ይመረመራል፡፡

67. Disqualification of Members of the Administrative Tribunal

A person shall not be appointed as a member of the Administrative Tribunal if he:

1/ is declared bankrupt;

2/ is an employee of the Authority or persons licensed by the Authority; or

3/ has been convicted of an offence under any law and sentenced to imprisonment for a period exceeding 6 (six) months.

68. Administration of the Administrative Tribunal

1/ The Chairperson of the Administrative Tribunal shall be responsible for managing the administrative affairs of the Tribunal.

2/ The Administrative Tribunal shall have a Registrar and such other staff as the Chairperson determines.

69. Budget and Accounts of the Administrative Tribunal

1/ The budget of the Administrative Tribunal shall be allocated by the Government.

2/ The Administrative Tribunal shall keep complete and accurate books of account.

3/ The books of account and other financial documents of the Administrative Tribunal shall be audited by the Federal Auditor-General or by an Auditor designated by the Federal Auditor-General.

https://ethiodata.et/

፸. የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ዓመታዊ ሪፖርት

፩/ የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤት ሰብሳቢው በየበጀት ዓመቱ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱን ጉዳዮች የሚመለከት ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ለየበጀት ዓመቱ የሚዘጋጀው ሪፖርት የበጀት ዓመቱ ባለቀ በ፫ (ሦስት) ወር ጊዜ ውስጥ ለጠቅላይ ሚንስትሩ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፸፩. ይግባኝ ስለመጠየቅ

፩/ ማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ ውሳኔ ላይ ለአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ መጠየቅ ከፈለገ፣ ውሳኔው ከተገለጸለት በኋላ ባሉ በ፳፰ (ሃያ ስምንት) ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማሳወቂያ ለሬጅስትራር ፋይል በማድረግ እና የተወሰነውን ክፍያ በመፈጸም ማመልከት ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም፣ ይግባኝ በወቅቱ ያልተጠየቀበት አሳማኝ ምክንያት ካለና ከዚያም በኋላ ያለምንም መዘግየት ይግባኙ እንደተጠየቀ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ካመነ የተጠቀሰው ጊዜ ካለፈም በኋላ ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፫/ የይግባኝ ማሳወቂያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ በሚጠይቀው አቀራረብ መሠረት ለይግባኝ ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች ለይቶ የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡

፬/ ባለስልጣኑ የይግባኝ ማስታወቂያው በደረሰው በ፯ (ሰባት) ቀናት ውስጥ ይግባኝ ከተጠየቀበት ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሰነዶችን ቅጂ ለአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ መላክ አለበት፡፡

70. Annual Report of the Administrative Tribunal

1/ The Chairperson of the Administrative Tribunal shall prepare a report of the affairs of the Tribunal for each fiscal year.

2/ A report under Sub-Article (1) of this Article for a fiscal year shall be submitted to the Prime Minister within 3 (three) months after the end of the fiscal year.

71. Filing of an Appeal

1/ A person may appeal to the Administrative Tribunal against the decision of the Authority by filing a notice of appeal to the Registrar, accompanied by the prescribed fee, within 28 (twenty eight) days of service of notice of the decision.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, an appeal may be instituted out of time if the Administrative Tribunal is satisfied that there was a reasonable cause for not appealing within the time prescribed and that the appeal was filed thereafter without unreasonable delay.

3/ A notice of appeal shall specify the grounds of appeal and be in such form and manner as may be prescribed by Administrative Tribunal.

4/ The Authority shall, within seven days, after receiving a notice of appeal, forward to the Administrative Tribunal copies of all documents related to the decision appealed from.

፸፪. የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ አሠራር

፩/ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሰብሳቢው ከአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ችሎቶች የአንዱ አባል ሆኖ ያገለግላል፡፡

፪/ በይግባኝ የተነሱትን ጭብጦች ከግምት ውስጥ በማስገባት የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ተገቢ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱን አባል ወይም አባላት ይግባኙን እንዲሰሙ ይመድባል፡፡

፫/ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን፣ ብይኑን፣ ትእዛዙን እና የችሎት አካሄዱን ለማስፈጸም በፍትሐ ብሔር ስነ-ስርዓት ህግ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ስልጣን ይኖረዋል፡፡

፸፫. የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ

፩/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ይግባኝ በመስማት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ በተጠየቀ በ፷ (ስልሳ) ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

፫/ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት እና ለፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለተከራካሪ ወገኖች የጽሑፍ ማሳወቂያ በመስጠት የይግባኝ መወሰኛ ጊዜውን ከ፴ (ሰላሳ) ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፡፡

፬/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተመለከቱትን አለማክበሩ በፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ተቀባይነት ሊያሳጣው አይችልም፡፡

72. Proceedings of the Administrative Tribunal

1/ The Chairperson of the Administrative Tribunal shall serve as a member of one of the panels of the Tribunal.

2/ The Chairperson of the Administrative Tribunal shall assign a member or members to the hearing of an appeal as the Chairperson considers appropriate having regard to the issues raised by the appeal.

3/ The Administrative Tribunal shall have the power, given to an ordinary court under civil procedure code, to execute its own decision, decree, order and the court procedure.

73. Decision of the Administrative Tribunal

1/ The Administrative Tribunal shall hear and determine an appeal and make a decision.

2/ The Administrative Tribunal shall decide an appeal within 60 (sixty) days after the notice of appeal was filed.

3/ The Chairperson of the Administrative Tribunal may, by notice in writing to the parties to an appeal, extend the period for deciding the appeal for a period not exceeding 30 (thirty) days having regard to the complexity of the issues in the case and the interests of justice.

4/ A failure by the Administrative Tribunal to comply with Sub-Article (2) and (3) of this Article shall not affect the validity of a decision made by the Tribunal on the appeal.

https://ethiodata.et/

፭/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ይግባኝ ከተመለከተ በኋላ፦

ሀ) የመጀመሪያውን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ እንዳለ ሊያፀናው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው፤

ለ) ትክክለኛ ነው ብሎ በወሰነው አቅጣጫ ጉዳዩን እንደገና እንዲያየው ወደ ባለስልጣኑ ሊመልሰው፤ ወይም

ሐ) ትክክለኛ ነው ብሎ የሚያምነውን ማናቸውም አይነት ሌላ ትእዛዝ ሊሰጥ፤

ይችላል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ ፭ (ሀ) መሰረት አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የመጀመሪያውን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ከሻረ፣ ትእዛዙን ወይም ውሳኔዉን ራሱ ትክክለኛ ነው ብሎ ባመነበት ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ሊተካዉ ይችላል፡፡

፯/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የይግባኙን ውሳኔ ቅጂ፣ ውሳኔውን በሰጠ በ፯ (ሰባት) ቀናት ውስጥ ለባለጉዳዮቹ እንዲደርሳቸው ማድረግ አለበት፡፡

፰/ የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ለውሳኔ ያበቁትን ምክንያቶች እንዲሁም ጥያቄ ባስነሱ ጭብጦች ላይ የተደረሰበትን ግኝት፣ የማስረጃውን ዋቢ ወይም ሌሎች ለግኝቱ መሠረት የሆኑ ፍሬነገሮችን ማካተት አለበት፡፡

፱/ በይግባኙ ላይ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ወይም አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ በውሳኔ ማሳወቂያው ላይ ከሚገልጸው ሌላ ማናቸውም ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5/ The Administrative Tribunal may dispose of an appeal by:

a) confirming, varying or setting aside an original order, or decision;

b) remitting the matter in question to the Authority with such directions as it considers appropriate; or

c) making any other order which the Administrative Tribunal considers appropriate.

6/ According to Sub-Article (5) (a) of this Article, where the original order or decision is set aside, the Administrative Tribunal may substitute the order or decision as it considers appropriate.

7/ The Administrative Tribunal shall serve a copy of the decision on an appeal on each party to the appeal within 7 (seven) days of the making of the decision.

8/ The Administrative Tribunal's decision shall include the reasons for the decision and the findings on material questions of fact, and reference to the evidence or other material on which those findings were based.

9/ The decision of the Administrative Tribunal on an appeal shall come into operation upon giving of the decision or on such other date as may be specified by the Administrative Tribunal in the notice of the decision.

https://ethiodata.et/

፸፬. ወደ ፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ስለመጠየቅ

በአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ አካል ውሳኔውን ባወቀ በ ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በህግ ጉዳይ ላይ ብቻ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

ክፍል ስምንት

ለህዝብ ሽያጭ ማቅረብና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት

፸፭. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባ

፩/ ለህዝብ የሚሸጥ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለሽያጭ ወይም ለገበያ ከመቅረቡ በፊት በባለስልጣኑ መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪ ወይም ተወካዩ ለዚሁ ተብሎ በባለስልጣኑ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ በመፈረም የተወሰነውን ክፍያ በመክፈል የምዝገባ መግለጫውን ለባለስልጣኑ ማስገባት አለበት፡፡

፫/ ባለስልጣኑ መግለጫን ለማስመዝገብ የሚጠየቀውን መረጃ በመመሪያ ይወስናል፡፡

፬/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አይነቶች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡-

ሀ) በኢትዮጵያ መንግስት ለሽያጭ በቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤

ለ) በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤

ሐ) መክሰራቸዉ የታወጀባቸዉ ኩባንያዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤

74. Appeal to the Federal High Court

A party to a proceeding before the Tribunal who is dissatisfied with the decision of the Tribunal may, within 30 (Thirty) days after being served with notice of the decision, file a notice of appeal, on question of law only, to the Federal High Court.

PART EIGHT

PUBLIC OFFERING AND TRADING OF SECURITIES

75. Registration of Securities

1/ A publicly traded security shall be registered, prior to the offer or placement, by the Authority.

2/ The issuer of a security or his representative must sign and file a statement of registration, with the Authority, in the prescribed form relating to the security together with the prescribed fee.

3/ The Authority shall determine, by directive, the information required for registration statements.

4/ The registration of securities shall not apply to any of the following class of securities:

a) Offering of securities issued by the Government of Ethiopia;

b) Sale of securities under court judgments or rulings;

c) Sale of securities of companies which are declared bankrupt;

https://ethiodata.et/

መ) በግል ለሽያጭ በሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ እና

ሠ) ባለስልጣኑ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ከምዝገባ ነጻ በተደረጉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፡፡

፭/ በግል ለሽያጭ የሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለህዝብ ለሽያጭ አይቀርቡም፡፡

፮/ ባለስልጣኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በግል ለሽያጭ የሚቀርቡበትን መሥፈርቶች በመመሪያ ይወስናል፡፡

፯/ ባለስልጣኑ የታዳጊ ኩባንያዎችን የምዝገባ መግለጫ መሥፈርቶችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

፰/ ባለስልጣኑ ባልተማከለ ጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የሚደረጉ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ለማካሄድ የሚጠየቁ የምዝገባ መግለጫ መሥፈርቶችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

፸፮. <u>በኩባንያዎች ለሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መግለጫ</u>

፩/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪ ማንኛውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለህዝብ ለሽያጭ ለማቅረብ ሰነዱን ከማውጣቱ ወይም ከማስተዋወቁ በፊት የደንበኛ ሳቢ መግለጫውን በባለልጣኑ ማስፀደቅ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው መግለጫ ትክክለኛ፣ የሚገባውን ያህል ግልጽ፣ የተሟላ፣ ምክንያታዊ በሆነ ደረጃ የሚፈለገውን ለይቶ የሚያቀርብ እና ወቅታዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው ቢኖርም፣ ባለስልጣኑ ለህዝብ የሚቀርቡ የሽያጭ ማስታወቂያዎችን ጨምሮ፣ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ የተለዩ መሥፈርቶችን በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

d) Securities offered in private placement; and

e) Any other class of securities that the Authority shall, from time to time, determine as exempted securities, by directive.

5/ Privately issued securities shall not be publicly traded.

6/ The Authority shall determine requirements for private placement of securities in a directive.

7/ The Authority shall determine registration statement requirements for an emerging growth company by directive.

8/ The Authority shall determine, by directive, registration statement requirements for securities traded in over-the-counter markets.

76. <u>Prospectus for Securities Issued by Companies</u>

1/ An issuer of securities shall obtain approval from the Authority for its prospectus prior to issuing or advertising any securities for a public offering.

2/ The prospectus under Sub-Article (1) of this Article shall be accurate, sufficiently clear, comprehensive and reasonably specific and timely.

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, the Authority may issue specific requirements of the prospectus, including advertisement of public offerings, in a directive.

፬/ ባለስልጣኑ አንድን የደንበኛ መሳቢያ መግለጫ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊከለክል ይችላል፡-

ሀ) መግለጫው የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች፣ ይህን አዋጅ ወይም ሌሎች በባለስልጣኑ መመሪያዎች እንዲሟሉ የሚጠየቁ መስፈርቶችን ያልተከተለ ከሆነ፤ ወይም

ለ) መግለጫው በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገዥው ውሳኔ ላይ ተጽእኖ ሊያስከትል የሚችል፤ የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ ሃሳብ ካለበት፡፡

፭/ መግለጫ አውጭው መግለጫውን በባለስልጣኑ መመሪያ በተካተቱት ቃላትና ሁኔታዎች መሠረት፣ ያለ ክፍያ ለህዝብ ማቅረብ አለበት፡፡

፸፯. <u>በቀጣይነት መረጃን ይፋ የማድረግ ግዴታዎች</u>

፩/ ለህዝብ የሚቀርቡ ወይም በህዝብ የተያዙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሽያጭ የሚያቀርብ አዉጪ ከራሱ እና፣ ተቀጥላ ካለ፣ ከተቀጥላ ድርጅቱ ጋር በተያያዘ፡-

ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አቅራቢውንና የተቀጥላ ድርጅቱን የፋይናንስ አቋም ለመገምገም አስፈላጊ የሆነ፤ እንዲሁም

ለ) በሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የሚገበያይ የሐሰት ገበያ እንዳይቋቋም የሚያደርግ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የገበያ ዋጋ ላይ በወሳኝነት ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል፤

መረጃ ለባለሥልጣኑ፣ ለአባላቱ እና የእርሱን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለያዙ በተቻለ መጠን በፍጥነት ማሳወቅ አለበት፡፡

4/ The Authority may refuse the prospectus for any of the following reasons:

a) the prospectus is not in accordance with the provisions of the Commercial Code, this Proclamation, or any other requirements to be issued in a directive by the Authority; or

b) the prospectus contains any inaccurate or incomplete statement that may influence the decision of the subscriber.

5/ The issuer shall make the prospectus available to the public free of charge, in the terms and conditions as determined in a directive by the Authority.

77. <u>Ongoing Information Disclosure Obligations</u>

1/ An issuer of securities that are the subject of a public offer, or which are publicly held, shall inform the Authority, members of the issuer and other holders of its securities as soon as reasonably practicable of any information relating to the issuer and its subsidiaries, if any, that:

a) is necessary to enable them and the public to appraise the financial position of the issuer and of its subsidiaries; and

b) is necessary to avoid the establishment of a false market in its securities, or might reasonably be expected to materially affect market price of its securities.

፪/ ማናቸውም ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አቅራቢዎች በባለስልጣኑ መመሪያዎች፣ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ባወጣቸውና ባለስልጣኑ ባጸደቃቸው ዉስጠ-ደንቦች መሠረት የተመረመረ የሂሳብ መግለጫቸውን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

፫/ ባለስልጣኑ የተመዘገቡ ኩባንያዎች በውስጣቸው የሚከሰቱ ማናቸውንም አይነት ጉልህ ለውጦችን በፍጥነት በይፋ እንዲያሳውቁ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፬/ ማንኛዉም ሰዉ ይፋ የተደረጉ ወይም የተገለፁ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የተቀመጡ ወቅታዊ ህትመቶችን፣ ሪፖርቶችን፣ መረጃዎችን እና የመግለጫዎችን ቅጂዎች ባለሰልጣኑ የሚወስነውን ክፍያ እየከፈለ ማየት ወይም ቅጅ መውሰድ ይችላል፡፡

፭/ የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አንድ ጊዜ ከወጡ በኋላ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ዋጋ ሊለውጡ የሚችሉ ማናቸውም መረጃዎች መኖራቸው በአቅራቢው ድርጅት ዳይሬክተሮች እንደታወቁ፣ አውጪው ወዲያውኑ ለህዝብ በሚሰራጭ ጋዜጣ በሚወጣ ማስታወቂያ እና ለባለስልጣኑ እና ለተመዘገቡባቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ሪፖርት በማድረግ ህዝቡ እንዲያውቅ ማድረግ አለበት፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አነቀጽ (፭) የተደነገገው ቢኖርም፣ ባለስልጣኑ ወሳኝነት ያላቸውን መረጃዎች ይፋ ስለማድረግ ተጨማሪ ግዴታዎችን በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ All issuers of public offerings shall disclose their audited financial statements in accordance with directives issued by the Authority or rules issued by the securities exchange and approved by the Authority.

3/ The Authority may require the securities exchange to take all necessary actions to urge listed companies to expedite the disclosure of any material changes that may occur in any of these companies.

4/ Any person may, for a fee specified by the Authority, have access to or obtain copies of periodic publications, reports, information and statements kept at a securities exchange, which was announced or disclosed.

5/ Once registered securities are issued, the issuer must keep the public informed of all matters which affect the value of the securities, immediately upon their becoming known to the directors of the issuer, by placing an advertisement in a newspaper of general circulation and by reports to the Authority and to any securities exchange on which they are listed.

6/ Notwithstanding Sub-Article (5) of this Article, the Authority may issue additional requirements regarding disclosure of material information in a directive.

፸፰. በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አሻሻጥ

፩/ በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሽያጭ የሚቀርቡት በባለ ልዩ ተልእኮ ተቋም የሚወጡ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

፪/ ባለስልጣኑ፡-

ሀ) ወደ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከሚቀየሩና በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር የተያያዙ በገበያው የሚወጡ ሰነዶችና ተግባራትን፣ እና

ለ) በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አቅራቢዎችን በሚመለከት፣ ለእያንዳንዱ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምድብ፣ ሰነዱ የተደገፈውን ሀብት የሚመለከት መረጃን፣

በተመለከተ ስለሚወጡት ውስጠ-ደንቦችና ውስጣዊ መመሪያዎች መመሪያ ማውጣት አለበት፡፡

፫/ ባለስልጣኑ ሰነዱ የወጣበትንና ለሽያጩ የቀረበበትን ምድብ እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዩን የደገፈውን ሀብት አይነት ወይም ባለስልጣኑ ተገቢ ናቸው ብሎ የሚላቸውን ሌሎችን ጉዳዮች ከግንዛቤ በማስገባት፣ የደንበኛ ሳቢ መግለጫውን ወይም የኩባንያውን አላማዎች፣ ስጋት እና የሙዓለ ንዋዮች የውለታ ቃሎች የመሳሰሉት የሚገለፁበትን ሰነድ ይዘት በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

፬/ ማናቸውም ሰው በዚህ ክፍል ወይም በባለስልጣኑ ካልፀደቀ በስተቀር በሃብት የተደገፈ ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ወይም ለተወሰኑ ኢንቨስተሮች ለገበያ ሊያቀርብ ወይም እንዲፈርሙ ወይም እንዲገዙ ሊጋብዝ አይችልም፡፡

78. Offer of Asset-Backed Securities

1/ An offer of asset-backed securities shall be made only if they are issued by a special purpose institution.

2/ The Authority shall issue a directive regarding rules and regulations:

a) on products and activities related to securitization and asset backed securities; and

b) with respect to issuer of an asset backed security to disclose, for each class of security, information regarding to the asset backing that security.

3/ The Authority may prescribe, by directive, the contents of a prospectus or offering memorandum taking into consideration on the classification of the issue or offer and the nature of the assets backing the securities or such other factors that the Authority may consider appropriate.

4/ A person shall not issue, offer for subscription purchase, or invite the subscription or purchase of asset-backed securities to the public or to restricted investors, except in accordance with this Part or approval by the Authority.

https://ethiodata.et/

ክፍል ዘጠኝ
ጥቅምን ይፋ ስለማድረግ

፸፱. ትርጓሜ

ለዚህ ክፍል ዓላማ ‹‹ጥቅም ያለው ሰው›› ማለት ማንኛውም በግብይት የተመዘገበ ኩባንያን ካፒታል አምስት (፭) በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን በቀጥታ፣ በተዘዋዋሪ ወይም ከሌሎች ጋር በመጣመር ድርሻ ያለው ሰው ነው፡፡

፹. የቀረበ መረጃ

፩/ ጥቅም ያለው ሰው ድርሻ ከገዛበት ቀን ጀምሮ በ፭ (አምስት) ቀናት ውስጥ የተረጋገጠና የተፈረመ መግለጫ ለባለስልጣኑ፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ግብይት ለሚፈፀምበት ገበያ እና ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ አቅራቢ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰዉን መግለጫ ይዘት ባለስልጣኑ በመመሪያ ይወስናል፡፡

፫/ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የተመዘገበ ማንኛውም አክሲዮን ኩባንያ፣ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች ስምና በአክሲዮን ድርሻቸው ላይ የሚደረገውን ማናቸውንም ለውጥ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገዉን መረጃ ይፋ የሚደረግበትን አሠራርና ጊዜ በተመለከተ ባለስልጣኑ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

፭/ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የተመዘገበበት ገበያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፫) ይፋ የተደረጉ ጥቅሞችን በተመለከተ የደረሰውን መረጃ መረጃው እንደደረሰው ወዲያውኑ በባለስልጣኑ መመሪያ በተደነገገዉ መሠረት ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

PART NINE
DISCLOSURE OF INTERESTS

79. Definition

For the purpose of this Part, an **"Interested Person"** means any person who has an interest that represents five (5) percent or more in the capital of a company listed on an Exchange, whether directly, indirectly, or in alliance with others.

80. Submitted Information

1/ An interested person shall, within a period of 5 (five) days from acquiring the interest, send an authenticated and signed statement to the Authority, the exchange where the securities are traded, and to the issuer of those securities.

2/ The Authority shall determine, in a directive, the information content of the statement in Sub-Article (1) of this Article.

3/ Any share company listed on an exchange shall disclose the names of interested persons and any change in their shareholding.

4/ The Authority may specify, in a directive, procedures and timing for the disclosures under Sub-Article (3) of this Article.

5/ The exchange in which a security is listed shall announce the information received concerning the disclosures of interests under Sub-Articles (1) and (3) of this Article immediately upon receipt thereof as specified by directive of the Authority.

https://ethiodata.et/

፯/ መረጃውን ይፋ የማድረግ ግዴታ የተጣለበት ሰው፣ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ጥቅሞችን ባለማሳወቁ ምክንያት በባለስልጣኑ፣ በገበያው ወይም በሌላ ሦስተኛ ወገን ላይ ለሚደርሰው ማናቸውም ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፹፩. ለውጦችን ስለማሳወቅ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹ ይፋ ስለማድረግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጥቅም ያለው ሰውና በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የተመዘገበ አክሲዮን ኩባንያ ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው ካፒታል 0.5 (ዜሮ ነጥብ አምስት) በመቶ የሚበልጡ በጥቅም ላይ የተደረጉ ማናቸውንም ለውጦች፣ ለውጡ በተደረገ በ፲ (አስር) ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ለተመዘገበበት ገበያ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሪፖርት የማድረጉ ግዴታ፣ የጥቅም ለውጡ እየቀነሰ ሄዶ ጥቅሙ ከካፒታሉ ከ፭ በመቶ በታች እስከሚሆን ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡

፹፪. ይፋ የማድረጊያ መዝገብ

፩/ ማንኛውም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የተመዘገበ አክሲዮን ኩባንያ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተሮችን እና ሥራ አስኪያጆችን የሚመለከት መረጃ ለጠቅላላ ጉባኤው በቀረበው ሪፖርት ውስጥ በተካተተበት አኳኋን ክፍያን፣ ደመወዝን፣ ማትጊያን እና ሌሎችን ጥቅማ ጥቅሞችን ጨምሮ በባለስልጣኑ በሚወሰነው መሠረት መግለጫዎችንና መረጃዎችን ይፋ የሚያደርግበት ልዩ መዝገብ ሊኖረው ይገባል፡፡

6/ A person under the obligation of disclosure shall be held liable for any damages incurred by the Authority, the exchange or a third party as a result of a failure to disclose the interest according to the provisions of this Proclamation and Directives issued by the Authority.

81. Notification of Changes

1/ An interested person and a share company listed on an exchange shall report to the Authority and the exchange on which securities are traded of any changes in any interest, subject to disclosure under Article 80 of this Proclamation, that exceeds more than 0.5 (zero point five) percent of the issuer's capital within a period of 10 (ten) days as of the date of the change.

2/ The reporting under Sub-Article (1) of this Article remains mandatory until the change results in a decline of the interest to below 5 percent of the capital.

82. Register of Disclosure

1/ Any share company listed on an exchange shall maintain a special register for the disclosure of the members of the board of directors, executive directors, and managers, which involve all statements and information determined by the Authority, and shall include all data related to remunerations, salaries, incentives, and other financial benefits as included in the report of the General Assembly.

፪/ ማንኛውም ባለድርሻ አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰዉን መዝገብ በመደበኛ የሥራ ሠዓት የማየት መብት አለው፡፡

ክፍል አስር
ለቁጥጥር የሚያበቃ የአክስዮን ግዥ እና ስለ አነስተኛ ባለድርሻዎች መብት ጥበቃ

፹፫. ትርጓሜ

ለዚህ ክፍል አላማ ‹‹**ለቁጥጥር የሚያበቃ የግዢ ጥያቄ**›› ማለት አንድን የተመዘገበ ኩባንያ የዳይሬክተሮች ቦርድ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለመቆጣጠር የሚያስችል የግዥ ጥያቄ ማቅረብ፣ ለመግዛት ግፊት ማድረግ ወይም ከመቶኛ አብዛኛውን ባለቤት ለመሆን ጥያቄ ማቅረብ ነው፡፡

፹፬. የግዢ ጥያቄ

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው፣ በባለስልጣኑ በወጣው መመሪያ ወይም በሌላ ህግ መሠረት ካልሆነ በስተቀር የማናቸውንም ኩባንያ አክሲዮን ለቁጥጥር በሚያበቃ መልኩ መግዛትን በተመለከተ የመግዛት ጥያቄ ማቅረብም ሆነ ክትትል ማድረግ አይችልም፡፡

፪/ ለቁጥጥር የሚያበቃ የአክሲዮን ግዥ የሚፈልግ ሰው፣ የግዢ ጥያቄ ማቅረቢያ ሰነዶችን ቅጂ ከሌሎች አግባብነት ካላቸው መረጃዎች ጋር ለባለስልጣኑ፣ ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው እና ለቁጥጥር የሚያበቃ ግዥ ለተጠየቀበት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ ለቁጥጥር የሚያበቃ የአክሲዮን ግዥ የሚያደርግ ሰው ከባለስልጣኑ ይሁንታ ከማግኘቱ በፊት በግዢው ሂደት ወደ ቀጣዩ ደረጃ መሸጋገር የለበትም፡፡

2/ Any stakeholder shall have the right to access the register under Sub-Article (1) of this Article during regular working hours

PART TEN
ACQUISITION AND PROTECTION OF MINORITY INTERESTS

83. Definition

For the purpose of this part, “**acquisition offer**” means the offer, or solicitation to offer, or request to own the majority percentage of a listed company that enables the offeror, directly or indirectly, to control the board of directors of the company.

84. Acquisition Offer

1/ A person shall not make or pursue an offer in respect of an acquisition of the securities of any company except in accordance with the conditions prescribed by this Proclamation or the directives issued by Authority or any other law.

2/ The person, wishing to submit an acquisition offer, shall submit copies of the offer documents, along with the relevant information to the Authority, securities exchange, and the issuer of the securities subject to the acquisition offer.

3/ The offeror shall not take any further steps in the acquisition process before obtaining the Authority’s approval.

፬/ ባለስልጣኑም ማመልከቻውን እና የግዢ ሰነዶችን በማረጋገጥ ቢዘገይ በ፲ (አስር) ቀናት ውስጥ ዉሳኔ መስጠት አለበት፤

፭/ ባለስልጣኑ፡-

ሀ) የግዥ ጥያቄው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችንና ተያያዥ የሆኑ ባለስልጣኑ ያወጣቸውን መመሪያዎች የሚጥስ ሆኖ ከተገኘ፤

ለ) ከግዥ ጥያቄው ጋር የማመልከቻ ክፍያዎች ተያይዘው ካልቀረቡ፤

ሐ) የግዥ ጥያቄ አቅራቢው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ባለስልጣኑ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት የሚያስፈልጉ ሰነዶችን አያይዞ ማቅረብ ካልቻለ፤ ወይም

መ) የግዥ ጥያቄው የአክሲዮን ኩባንያው ባለ አክሲዮኖች ውሳኔ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል ትክክል ያልሆነ ወይም ያልተሟላ ነገር ከተገኘበት

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ለቀረበለት ማመልከቻ ይሁንታ ሊከለክል ይችላል፡፡

፮/ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ከአንድ የተመዘገበ ኩባንያ ግብይት እንዲደረግባቸው ከገቡ አክሲዮኖች ከሚያስፈልገው አብላጫ የመቶኛ ድርሻ በላይ የገዛ ሰው ከገዛበት ቀን ጀምሮ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በገበያው ግብይት የሚደረግባቸውን ቀሪ አክሲዮኖች ለመግዛት የግገዢ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፯/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፮) ድንጋጌ የሚውል የመቶኛ አብላጫ ድርሻ መጠንን ባለስልጣኑ በመመሪያ ይወስናል፡፡

4/ The Authority shall, within a maximum period of 10 (ten) days, review the application and offer documents and issue its decision.

5/ The Authority may refrain from issuing its approval pursuant to Sub-Article (4) of this Article if:

a) the offer does not comply with the provisions of this Proclamation and related directives issued by the Authority;

b) the application fees are not included in the offer;

c) the offeror fails to submit the necessary documents in accordance with the provisions of this Proclamation and related directives issued by the Authority; or

d) the offer includes incorrect or incomplete statement, which shall have an influence on the decision of the shareholders of the company.

6/ A person who acquires, directly or indirectly, more than the required majority percentage of the shares admitted to trading of a listed company shall within 30 (thirty) days from the date of acquisition submit an offer to purchase all the remaining shares traded in the exchange.

7/ The Authority shall issue a directive determining the required majority percentage to apply to Sub-Article (6) of the Article.

https://ethiodata.et/

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት ጎጂ ተጽዕኖ የደረሰበት ማንኛውም ባለአክሲዮን የተመዘገበው ኩባንያ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች አነስተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸውን ባለአክሲዮኖች ጥቅም የሚጎዳ የሆነ እንደሆነ በንግድ ህጉ በተቀመጡ ተገቢነት ባላቸዉ ድንጋጌዎች መሠረት ውሳኔውን መቃወም ይችላል፡፡

፱/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮)፣(፯) እና (፰) በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡-

ሀ) ለህዝብ ጥቅም እና ለተቀሩት ባለአክሲዮኖች ሲባል በሚደረጉ ግዢዎች፤

ለ) ኩባንያው ካፒታሉን በሚያሳድግበት ጊዜ በሚገኝ ተጨማሪ የአክሲዮን ድልድል የተወሰኑ ባለአክሲዮኖች ከመግዛት በመቆጠባቸው ምክንያት መቶኛ ገደብ ሲታለፍ፤

ሐ) ዕዳ እንደገና በመዋቀሩ ወደ አክሲዮን በመቀየሩ ምክንያት የተጠቀሰው የመቶኛ ገደብ ሲታለፍ፤

መ) በውርስ፣ በኑዛዜ ወይም በፍርድ ውሳኔ የተጠቀሰው መቶኛ ሲወሰድ፤ የተጣለው የመቶኛ ገደብ ሲታለፍ፤ እና

ሠ)ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ውስጠ-ደንቦች እና በተካተቱ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች፡፡

፲/ ማናቸውም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፱(ሀ) መሰረት በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የተፈጻሚነት ወሰንን የሚገድብ ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ ምክንያቱ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

፲፩/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ፱(መ) አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ግለሰቡ ጭማሪ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ከ፪ (ሁለት) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የድርሻውን ሁኔታ ማስተካከል አለበት፡፡

8/ Any shareholders adversely impacted under Sub-Article (6) of this Article may challenge the resolutions of the General Assembly of the listed company, as per relevant provisions of the Commercial Code, if such decisions harm the interests of the minority.

9/ Sub-Article (6), (7), and (8) of this Article shall not be applicable on the following cases:

a) Acquisition in consideration of the public interest and in the interest of the remaining shareholders;

b) Gaining the stated percentage when the company increases its capital and some shareholders refrain from subscription;

c) Gaining the stated percentage because of debt restructure;

d) Gaining the stated percentage because of an inheritance, a will or a judicial ruling; and

e) Such other cases as provided in a directive issued by the Authority.

10/ Any exemption decision issued by the Authority under Sub-Article (9) (a) of this Article shall be written and reasoned.

11/ In the case of Sub-Article (9) (d) of this Article, the person shall complete the formalities within not more than 2 (two) years as from the increase.

https://ethiodata.et/

፲፪/ ለቁጥጥር በሚያበቃ መልኩ ግዢ የሚፈጸምባቸው ወይም እንዳለ ተጠቃለው የሚወሰዱበት አክሲዮኖቹን ለሽያጭ ያቀረበ አክሲዮን አውጪ አስተያየቱን እና ለባለአክሲዮኖች የውሳኔ ሃሣቦችን ያካተተ ምላሽ የሽያጭ ማቅረቢያው ማስታወቂያ በደረሰው በ፯ (ሰባት) ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፲፫/ ነባር ባለአክሲዮኖች የኩባንያቸዉን አክሲዮን የመጠቅለል ወይም ለቁጥጥር የሚያበቃ ግዢ ጥያቄ ሲቀርብላቸው፡-

ሀ) ሐሳቡን በሚገባ እንዲያስቡበት በቂ ጊዜ፤

ለ) የቀረበው ሐሣብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ለመገምገም እንዲችሉ በቂ መረጃ፤

ሐ) ተግባራዊ ማድረግ እስከተቻለ ድረስ፣ በውሳኔ ሐሣቡ መሠረት ባለአክሲዮኖች ከሚያገኙት ማናቸውም ጥቅም ተጠቃሚ ለመሆን ምክንያታዊና ፍትሀዊ ዕድሎች፤ እና

መ) ከቀረበው ሃሳብ ጋር በተያያዘ ተመጣጣኝና ፍትሃዊ መስተንግዶ፣ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ክፍል አስራ አንድ
የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ

፹፭. የህግ ቅርጽ

የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ከሚከተሉት በአንዱ መልክ ሊቋቋም ይችላል፡-

፩/ እንደ ጋርዮሽ ገንዘብ ያሉ የኢንቨስትመንት ኩባንያዎች፤

፪/ የተወሰነ ኃላፊነት ያላቸው የሽርክና ማህበሮች፤ ወይም

፫/ ባለስልጣኑ በጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥር መካተት አለባቸው ብሎ የሚወስናቸው ሌሎች በንግድ ህጉ የተደነገጉ አደረጃጀቶችና አወቃቀሮች፡፡

12/ An issuer whose shares are the subject of an acquisition or takeover shall, within 7 (seven) days from receipt of the offer, submit a response to the Authority stating its opinion and recommendations to the shareholders.

13/ Existing shareholders of the company being offered for takeover or acquisition shall be፡

a) given a reasonable time to consider the proposal;

b) supplied with adequate information to enable them to assess the merits of the proposal;

c) as far as practicable, given a reasonable and equitable opportunities to participate in any benefit accruing to the shareholders under the proposal; and

d) given fair and equitable treatment in relation to the proposal.

PART ELEVEN
COLLECTIVE INVESTMENT SCHEMES

85. Legal Form

A Collective Investment Scheme may exist in any of the following forms:

1/ Investment companies such as mutual funds;

2/ Limited partnerships; or

3/ Any other such forms or mechanisms under the commercial code, which the Authority decides to include as a collective investment scheme.

፹፮. የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አመዘጋገብ

፩/ ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ጋር የተያያዙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም ክፍልፋዮች በባለስልጣኑ ካልተመዘገቡ እና ምዝገባውም በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ ለህዝብ ካልተገለፀ በስተቀር ሊሰራባቸው ወይም ሊሸጡ አይችሉም፡፡

፪/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ምዝገባ ማመልከቻ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ ለባለስልጣኑ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) የማመልከቻ ቅጽ፣

ለ) ለባለስልጣኑ የሚከፈል የማመልከቻ ክፍያ፣

ሐ) የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመጨረሻ የቅርብ ጊዜ የፋይናንስ ሪፖርት፣ እና

መ) ሌሎች በደንብ ወይም በመመሪያ የተደነገጉ ወይም በባለስልጣኑ እንደሁኔታው የሚጠየቁ ሰነዶችና መረጃዎች፡፡

፫/ ባለስልጣኑ ማመልከቻውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በቀረበው መሠረት መርምሮ ብቁ ሆኖ ካገኘው ፈንዱን ይመዘግባል፤ ይህንንም ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

፬/ ባለስልጣኑ ስለ ጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች አይነት፣ በጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች ሥራ ላይ ሊውሉ ስለሚችሉ የኢንቨስትመንት ክፍልፋዮች፣ ስለሀብት አገማመት፣ ስለዋጋ ቁጥጥር፣ እና መረጃን ይፋ የማድረጊያ መስፈርቶችን የሚመለከት መመሪያ ያወጣል፡፡

86. Registration of Collective Investment Schemes

1/ Securities or units pertaining to a collective investment scheme shall not be managed or sold unless the Scheme has been registered by the Authority and the registration has been announced to the public in a widely circulated newspaper.

2/ An application for the registration of a collective investment scheme shall be made to the Authority in the prescribed form and manner and shall be accompanied by:

a) application form;

b) application fee payable to the Authority;

c) memorandum of association and most recent financial report; and

d) such other documents and information as may be prescribed or as the Authority may reasonably require.

3/ If, the Authority is satisfied,after considering an application in terms of Sub-Article (2) of this Article, the Authority shall register the scheme and shall notify the applicant in writing accordingly.

4/ The Authority shall issue a directive on types of the schemes, on issuance and redemption of investment units, asset valuations, pricing controls, and disclosure requirements of collective investment schemes.

፹፯. የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኝ

፩/ ለጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኝ ሆኖ የሚያገለግል ማንኛውም ሰው ፈቃድ ለማግኘት፡-

ሀ) የስጋት አስተዳደር ዘዴዎች፣

ለ) የውስጥ ቁጥጥር፣

ሐ) የሒሳብ አሠራር ሥርዓት፣

መ) የድርጅት አስተዳደር፣

ሠ) ተገቢና ብቁ የሰውና የቴክኒክ ሀብት፣

ረ) ዝቅተኛ ተፈላጊ ካፒታል፣ እና

ሰ) ሌሎች በባለስልጣኑ መመሪያ የሚወሰኑ መስፈርቶች፤

በተመለከተ ዝቅተኛ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

፪/ ባለስልጣኑ፡-

ሀ) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስትመንቶችን ለመምረጥ የሚካሄዱ የተገቢነት ጥናቶችን፤

ለ) የጋራ ኢነቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስተሮችን ጥቅም ማስጠበቅና በፍትሐዊነት የማስተናገድ መርሆዎችን መከተልን፤

ሐ) የጥቅም ግጭትን መለየትና የማስተዳደር፣ በተለይም ከተዛመደ አካል ጋር የሚደረግ ግብይይትን፤ እና

መ) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራዎችን በሥርዓት መምራትና ማጠናቀቅን

በተመለከተ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድን ሥራ አከናዋኞች በየጊዜው ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን ከአነስተኛ ደረጃዎች ጋር በመመሪያ ያወጣል፡፡

87. Collective Investment Scheme Operator

1/ Any person acting as a collective investment scheme operator shall meet minimum requirements for licencing with regard to:

a) Risk management mechanisms;

b) Internal controls;

c) Accounting procedures;

d) Corporate governance;

e) Appropriate and sufficient human and technical resources;

f) Minimum capital requirements, and

g) Any other requirements to be determined by directive of the Authority.

2/ The Authority may issue directive regarding ongoing requirements for collective investment scheme operators with minimum standards regarding:

a) Due diligence in the selection of collective investment scheme investments;

b) Acting in the best interest of collective investment scheme investors and in accordance with the principles of fair treatments;

c) Identification and managements of conflicts of interests, especially with regards to related party transactions; and

d) Procedures for orderly winding up of collective investment schemes businesses.

፫/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኞች የፈንዱን ሀብቶች እና ከፈንዱ አክሲዮኖችና ክፍልፋዮች ጋር የተገናኙ የገንዘብ ዝውውሮችን (ግዥና ሽያጭን) የሚመለከት መዝገቦችን መመዝገብና መያዝ አለባቸው፡፡

፬/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኞች ማናቸውም አይነት በፈንዱ አስተዳደር ወይም መዋቅር ወይም በኢንቨስተሮች መብቶች ወይም በፈንዱ አሠራር ላይ የሚከሰቱ ጉልህ ለውጦችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፭/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኝ የራሱን ሀብት ከጋራ ኢንቨስትመንቱ ሀብት መለየት ይኖርበታል፡፡

፮/ የደንበኛ ሀብት ከጋራ ኢንቨስትመንት ሥራ አከናዋኙ ጉዳትና ኪሳራ መጠበቅ አለበት፡፡

፯/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስራ አከናዋኙ፤

ሀ) ክፍልፋዮችን ሽጦ የመዉጣት ጥያቄን ማሳካት የማይችል ከሆነ፤

ለ) ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዱ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ወይም ውሎች ወይም ከደንበኛ ሳቢ መግለጫው ጋር በሚቃረን መንገድ ክፍልፋዮችን ሽጦ መዉጣት ላይ እገዳ ከጣለ፤ ወይም

ሐ) ይህን አዋጅ ይጥሳል ተብሎ ከታመነ፤

ባለስልጣኑ ጣልቃ በመግባት የመፍትሔ እርምጃ ይወስዳል፡፡

3/ Collective investment scheme operators shall keep books and records in relation to transactions involving collective investment scheme assets, and all transactions in collective investment scheme shares or units.

4/ A collective investment scheme operator shall report to the Authority any information relating to material changes in its management or organisation or investor rights or in the operations of the collective investment scheme.

5/ A collective investment scheme operator shall separate its own assets from collective investment scheme assets.

6/ Collective investment scheme investor's assets should be protected from losses or insolvency of collective investment scheme operator.

7/ In instances where the collective investment scheme operator is:

a) Failing to honour redemptions;

b) Imposing a suspension of redemptions in a manner that is not consistent with collective investment scheme Memorandum or Articles of Association or contracts or prospectus; or

c) Deemed to be in violation of this Proclamation,

the Authority shall intervene and address the situation.

፹፰. <u>የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስተሮች መብት</u>

፩/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አከናዋኝ፣ ሥራ ላይ ለማዋል በኢንቨስተሮች አስቀድመው መጽደቅ የማያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሆነው በኢንቨስተሮች መብት ላይ ጉልህ ለውጦች የሚያስከትሉትን ስራ ላይ ከማዋሉ በፊት ለኢንቨስተሮች ማስታወቅ አለበት፡፡

፪/ በኢንቨስተሮች መብት ላይ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል ጉልህ ለውጥ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ኢንቨስተሮች፣ ከፈለጉ፣ ክፍልፋዮቻቸዉን ያለ ክፍያ እንዲሸጡ እድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

፫/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስተሮች ክፍልፋያቸውን በመተዳደሪያ ደንብ፣ ወይም በመመስረቻ ፅሁፍ፣ ወይም በኮንትራት ወይም በደንበኛ ሳቢ መግለጫው መሠረት ያለምንም ቅድመ ማስታወቂያ ሽጠዉ መዉጣት ይችላሉ፡፡

፹፱. <u>የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስትመንት አማካሪ</u>

ማናቸውም የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አማካሪ ሆኖ የሚያገለግል ሰው የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

፩/ በኢንቨስትመንት አማካሪነት ለመስራት ከባለሰልጣኑ ፈቃድ ማግኘት፤

፪/ የክፍልፋይ ባለድርሻዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዱ የሚመራባቸውን መመሪያዎችና አሠራሮች አክብሮ መንቀሳቀስ፤

፫/ የኢንቨስትመንት ምክር በሚሰጥበት ጊዜ የግል ንብረቱን ለመጠበቅ ለሚተጋ ሰው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ፤

88. <u>Rights of Collective Investment Scheme Investors</u>

1/ A collective investment scheme operator shall give notice to investors of material changes to investor rights notice before they take effects, in cases where such changes do not require prior approval from investors.

2/ Before material changes to investor rights take effects, the investors should be given the possibility to redeem their shares with no redemption fee, if they choose to.

3/ Investors of a collective investment scheme are entitled to redeem their units from a collective investment scheme in accordance with the Memorandum or Articles of Association or Contract or prospectus, without giving prior notice.

89. <u>Investment Advisor of a Collective Investment Scheme</u>

Any person acting as an advisor for a Collective Investment Scheme shall comply with the following:

1/ Be licensed by the Authority to act as an Investment Advisor;

2/ Act in the conformity with the regulations and procedures governing the Collective Investment Scheme, which aims to achieve the unit holders' interests;

3/ Exert reasonable care of the person that is protecting his own property when offering investment advices;

https://ethiodata.et/

፬/ ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዱ ጋር የተያያዙ መደበኛ ሪኮርዶችን በፈንዱ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መዝግቦ መያዝ፤ እና

፭/ በተጠየቀ ጊዜ እና በባለስልጣኑ መመሪያ መሠረት በየጊዜው ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ፡፡

፺. የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ጠባቂ

፩/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሀብት የጥበቃ ሥራ በሚያከናውን ሀብቱን በደንበኛ ሀብትነት ለይቶ በሚይዝ ራሱን በቻለ ሌላ ጠባቂ አካል ጥበቃ ሥር መሆን ይኖርበታል፡፡

፪/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ጠባቂ በአሰራሩ ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኝ ገለልተኛ ሆኖ ሁልጊዜም ለኢንቨስተሮች ጥቅም የቆመ መሆን አለበት፡፡

፫/ ባለስልጣኑ የጠባቂዉን፡-

ሀ) የፋይናንስ እና የማስተዳደር ብቃት፤ እና

ለ) የኢንቨስትመንት ፈንድ ሀብቶችን ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስራ አከናዋኙ፣ ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አማካሪዉ እንዲሁም ከራሱ ሀብቶች ለይቶ የመጠበቅ ብቃቱን፤

በተመለከተ መመዘኛዎችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

4/ Maintain regular records according to the accounting systems related to the collective investment schemes; and

5/ Submit periodic reports to the Authority, as requested and in accordance with its directives.

90. Custodian of Collective Investment Scheme

1/ Collective investment scheme assets should be under the custody of an independent party, a custodian, to whom such assets shall be identified as clients' assets.

2/ The custodian of a collective investment scheme shall be functionally independent of the collective investment scheme operator and shall always act in the best interests of investors.

3/ The Authority shall specify, in a directive, qualifying requirements for a custodian in relation to:

a) its financial and managerial capacity; and

b) its ability to protect the assets of the collective investment scheme by separating these assets from the assets of the collective investment scheme operator, of the investment advisor of the collective investment scheme, and of the custodian itself.

፺፩. በጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ላይ የተጣሉ ገደቦች

፩/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ የሚከተሉትን ተግባራት ከማከናወን የተከለከለ ነው፡-

ሀ) ብድር መስጠት፣

ለ) በባለስልጣኑ መመሪያ በወጡ መስፈርቶች እስከተፈቀደው መጠን ድረስ ካልሆነ በስተቀር፤ ፈንዱን ከሚያስተዳድረው ኩባንያ ወይም ከተቀጥላ ኩባንያዎቹ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መግዛት፤ እና

ሐ) በባለስልጣኑ በወጣ መመሪያ ከተቀመጠው አግባብ ውጪ፣ የፈንዱ አማካሪ ለሕዝብ የማቅረብ ስራን ከሚመራበት ወይም የሽያጭ ወኪል ሆኖ ከሚያገለግልበት ማናቸውም ተቋም፣ ምንም አይነት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መግዛት፡፡

፪/ ማንኛዉም የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ያለ ባለስልጣኑ ይሁንታ የኢንቨስትመንት ፈንድ አማካሪ ወይም ጠባቂ ሊሾም ወይም በሌላ ሊተካ አይችልም፡፡

፫/ ባለስልጣኑ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስትመንት ፈንድ አማካሪ ወይም ጠባቂ የመሾም ወይም የመተካት ማመልከቻ በደረሰዉ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ዉስጥ ውሳኔውን እና የውሳኔውን ምክንያት ያሳዉቃል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አማካሪ ወይም ጠባቂ የመሾም ወይም የመተካት ማመልከቻ ቀርቦለት ባለስልጣኑ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ተቃዉሞ ካልገለፀ ማመልከቻዉ የባለስልጣኑን ይሁንታ እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

91. Restrictions on Collective Investment Schemes

1/ The collective investment scheme is prohibited from carrying out the following:

a) Grant credit;

b) Purchase any securities issued by the company managing the scheme or any of its subsidiaries, except to the extent of the requirements established by directive of the Authority in this regard; and

c) Purchase any securities of the entity, where the scheme's advisor is acting as the subscription manager or sales agent, except to the extent of the requirements established by the Authority in this regard.

2/ A collective investment scheme may not appoint or replace an investment advisor or custodian without consent from the Authority.

3/ After receiving request for appointment or replacement of a manager or custodian from a collective investment scheme, the Authority shall notify the applicant its reasoned decision within 30 (thirty) days from the date of receipt of the request.

4/ Under Sub-Article (3) of this Article, if the Authority does not express objection within 30 days, the appointment or replacement shall be considered as having received the consent of the Authority.

https://ethiodata.et/

ክፍል አስራ ሁለት
የተከለከሉ የግብይት ተግባራት

፺፪. ለህዝብ የተሰራጨ መረጃ

፩/ ለዚህ አዋጅ አላማዎች፣ አንድ መረጃ ለህዝብ ተሰራጭቷል የሚባለው፡-

ሀ) በባለስልጣኑ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ገበያ መመሪያዎች መሠረት ለኢንቨስተሮች እና ለአማካሪ ባለሙያዎች መረጃ ለመስጠት ተብሎ ከታተመ፤

ለ) ተመዝግቦ ተይዞ በወጣ ህግ መሰረት ለህዝብ ዕይታ ክፍት ከሆነ፤

ሐ) መረጃው፡-

(፩) ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ፤ ወይም

(፪) ከሰነደ ሙዓለ ንዋዩ አቅራቢ፤ጋር የተገናኘ ሆኖ ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር በተገናኘ ስራ ሊሰሩ በሚችሉ አካላት በቀላሉ ሊገኝ ከቻለ፤ ወይም

መ) ለህዝብ እንዲያውቀው ከተደረገ መረጃ የተገኘ ከሆነ

ነው፡፡

፪/ መረጃው፡-

ሀ) በጥንቃቄ በሚሰሩና የሙያው ብቃት ባላቸው ሰዎች ብቻ የሚደረስ፤

ለ) በፍትሐዊና ተመጣጣኝ ክፍያ በቋሚ ደንበኝነት ወይም በክፍያ ለህዝብ የሚደርስ፤

ሐ) በምልከታ ብቻ የሚገኝ፤ ወይም

መ) ከኢትዮጵያ ውጭ ብቻ የሚታተም

ቢሆንም ለህዝብ እንደተሰራጨ ሊቆጠር ይችላል፡፡

PART TWELVE
PROHIBITED TRADING PRACTICES

92. Information Made Public

1/ For the purposes of this Proclamation, information is made public if it:

a) is published in accordance with the directives of the Authority or a securities exchange for the purpose of informing investors and their professional advisers;

b) is contained in records which by virtue of any enactment are open to inspection by the public;

c) can be readily acquired by those likely to deal in any securities:

(1) to which the information relates; or

(2) of an issuer to which the information relates; or

d) is derived from information which has been made public.

2/ Information may be treated as made public even though it:

a) can be acquired only by persons exercising diligence or expertise;

b) is communicated to the public on subscription or payment of a fair and reasonable fee;

c) can be acquired only by observation; or

d) is published only outside Ethiopia.

፺፫. የውስጥ አዋቂ መረጃ

፩/ ለዚህ ክፍል አላማ ‹‹ውስጥ አዋቂ መረጃ›› ማለት ቀጥተኛ እና ግልጽ፣ ለህዝብ ያልተሰራጨ እና ለህዝብ ቢሰራጭ ኖሮ በማናቸውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዋጋ ላይ ጉልህ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል ነው፡፡

፪/ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከውስጠ አዋቂ መረጃዎች ጋር በተያያዘ ‹‹ዋጋቸው ተለዋዋጭ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች›› ናቸው የሚባሉት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እሴትን ጨምሮ መረጃው ለህዝብ ቢገለፅ በዋጋው ላይ ጉልህ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል ከሆነ ነው፡፡

፺፬. ውስጥ አዋቂዎች

፩/ ለዚህ ክፍል አላማ ‹‹ውስጥ አዋቂ›› ማለት የውስጥ መረጃ ያለው ሰው ነው፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አላማ አንድ ሰው፡-

ሀ) ዳይሬክተር፣ ሰራተኛ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አቅራቢ ባለአክሲዮን በመሆኑ፤

ለ) በሙያው፣ በስራ ቅጥሩ፣ በቢሮው ምክንያት መረጃውን የማግኘት ዕድል ያለው በመሆኑ፤ ወይም

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) እና/ወይም (ለ) ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር ባለዉ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ ግንኙነት፤

መረጃውን ያገኘ እንደሆነ ከውስጥ ምንጭ እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

93. Inside Information

1/ For the purpose of this Part **"inside information"** means information which is specific or precise, has not been made public, and, if it were made public, would likely have a material effect on the price of any securities.

2/ Securities are **"price-sensitive securities"** in relation to inside information, if the information would, if made public, be likely to have a material effect on the price including the value of the securities.

94. Insiders

1/ For the purpose of this Part, an "**insider**" means a person in possession of inside information.

2/ For the purpose of Sub-Article (1) of this Article, a person has information from an inside source if that person has it through:

a) being a director, employee or shareholder of an issuer of securities;

b) having access to the information by virtue of his or her employment, office or profession; or

c) direct or indirect relationship with a person under paragraph (a) and/or (b) of this Sub-Article.

https://ethiodata.et/

፺፭. የውስጥ አዋቂ ግብይት

፩/ የውስጥ አዋቂ መረጃ ያለው ሰው፡-

ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ከውስጥ አዋቂ መረጃ ጋር በተያያዘ ዋጋቸው ተለዋዋጭ ከሆኑ፣

ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ግብይት ሊካሄድ እንደሚችል በማወቁ ወይም በቂ ምክንያት መኖሩን በማመኑ ሌላን ሰው ቢያውቅም ባያውቅም በውስጥ አዋቂው ይዞታ ሥር ካለ መረጃ ጋር በተያያዘ ዋጋቸው ተለዋዋጭ በሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም ከእነርሱ በሚመነጩ ሰነዶች እንዲገበያይ ካበረታታ፣ ወይም

ሐ) ከተቀጠረበት ስራ፣ ከቢሮው ወይም ከሙያው ጋር ባልተያያዘ መንገድ መረጃውን ከገለፀ

በሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ መገበያየት አይፈቀድለትም፡፡

፪/ አንድ ውል በዚህ አንቀጽ በተጠቀሱት ጥፋቶች ብቻ ፈራሽ ወይም የማይፈፀም ሊሆን አይችልም፡፡

፫/ ባለስልጣኑ የውስጥ አዋቂ ንግድ ግብይትን ለመቆጣጠርና በበላይነት ለመከታተል ተጨማሪ ድንጋጌዎችን በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፺፮. የገበያ ሸፍጥ

አንድ ሰው ግብይቶችን በራሳቸው ወይም ከሌላ ማናቸውም ግብይት ጋር በማጣመር፡-

95. Insider Trading

1/ A person who has inside information is prohibited from trading in securities if:

a) the securities are price-sensitive in relation to the inside information;

b) that person encourages another person, whether or not that other person knows it, to deal in securities or their derivatives which are price-sensitive in relation to the information in the possession of the insider, knowing or having reasonable cause to believe that the dealing would take place; or

c) that person discloses the information, otherwise than in the proper performance of the functions of his employment, office or profession, to another person.

2/ A contract shall not be void or unenforceable by reason only of the commission of an offence under this Article.

3/ The Authority may issue additional provisions in a directive to regulate and supervise insider trading activities.

96. Market Manipulation

A person shall not enter into or carry out, directly or indirectly, two or more transactions in the securities of a company, or in other publicly traded securities, which by themselves or in conjunction with any other transaction:

https://ethiodata.et/

፩/ ሌላ ሰው የተመሳሳይ ኩባንያን፣ ወይም የሌላ ተዛማጅ ኩባንያን፣ ወይም የተመዘገቡ ሌሎች መሰል ኩባንያዎችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እንዲገዛ፣ ለመግዛት ቃል እንዲገባ፣ ወይም ከመሸጥ እንዲታቀብ ለመገፋፋት፣ በማሰብ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋን በሚጨምሩ፣ ወይም ሊጨምሩ፤

፪/ ሌላ ሰው የተመሳሳይ ኩባንያን፣ ወይም የሌላ ተዛማጅ ኩባንያን፣ ወይም የተመዘገቡ ሌሎች መሰል ኩባንያዎችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እንዲሸጥ፣ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከመግዛት እንዲታቀብ ለመገፋፋት፣ በማሰብ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋን በሚቀንሱ፣ ወይም ሊቀንሱ፤ ወይም

፫/ የተመሳሳይ ኩባንያን፣ ወይም የሌላ ተዛማጅ ኩባንያን፣ ወይም የተመዘገቡ ሌሎች መሰል ኩባንያዎችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሌላ ሰው እንዲገዛ፣ እንዲሸጥ፣ ወይም ለመግዛት ቃል እንዲገባ፣ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከመሸጥ፣ ከመግዛት እንዲታቀብ ለመገፋፋት፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ዋጋ በሚያረጋጉ ወይም ሊያረጋጉ፤

በሚችሉ በአንድ ኩባንያ ሰነደ መዓለ ንዋዮች ወይም በሌላ በይፋ በሚካሄድ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የሰነደ መዓለ ንዋዮች ግብይቶችን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ መፈጸም አይችልም፡፡

1/ increase, or are likely to increase the price of securities with the intention of inducing another person to purchase, or subscribe for, or to refrain from selling securities issued by the same company or a related company, or such other listed securities;

2/ decrease, or are likely to decrease, the price of securities with the intention of inducing another person to sell , or to refrain from purchasing, securities issued by the same company or a related company, or such other listed securities; or

3/ stabilize, or are likely to stabilize, the price of securities with the intention of inducing another person to sell, purchase, or subscribe for, or to refrain from selling, purchasing or subscribing for, securities issued by the same company or by a related company, or such other listed securities.

፺፯. <u>የሀሰት ግብይት</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በመካሄድ ላይ ባለ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት በመጠንም ሆነ በዋጋ ላይ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ዕይታ እንዲኖር የሚፈጥር ወይም እንዲፈጠር የሚያደርግ ወይም ሌላ የተዛባ ሁኔታ ማድረግ የለበትም፡፡

97. <u>False Trading</u>

1/ A person shall not create or cause to be created, or do anything with the intention of creating a false or misleading appearance of active trading in volume and prices of securities.

፪/ በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ ሰው፡-

ሀ) በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጥቅም የባለቤትነት ለውጥን በማያስገኝ ሁኔታ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ የመግዛት ወይም የመሸጥ ግብይት ከፈጸመ ወይም እንዲፈጸም ካቀረበ፤ ወይም

ለ) በግልጽ በሚታይ ሁኔታ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለራሱ እንዲሸጥለት ባዘጋጀው ወይም ባቀረበው ዋጋ ለመሸጥ ካቀረበ፣ ወይም ከሱ ጋር የሚገበያየው ሰው በግልጽ በሚታይ ሁኔታ እንዲሸጥለት ያዘጋጀው ወይም ያቀረበው እኩል ብዛት ያላቸው ወይም እኩል ብዛት እንዳላቸው በግልጽ ሊታወቁ የሚችሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ካቀረበ

ለዚህ ክፍል ዓላማ በመካሄድ ላይ ባለ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት እና ዋጋ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ዕይታ እንዲኖረው የማድረጉ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

፺፰. <u>የተጭበረበረ ግብይት</u>

ማንኛውም ሰው፡-

፩/ ሀሰተኛ፣ አሳሳችና፣ አታላይ መግለጫ ቃል በመስጠት፣ ትንበያ በመስጠት ወይም በማሳተም፤

፪/ ወሳኝ መረጃ በመደበቅ፤ ወይም

2/ Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, a false or misleading impression of active trading and prices of securities is created for the purpose of this section if a person:

a) enters into or carries out, directly or indirectly, any transaction for the sale or purchase of securities which does not involve a change in the beneficial ownership of the securities, or offers to do so; or

b) offers to sell securities at a price which is conspicuously the same as the price at which he has made or proposes to make, or knows that his counterpart has made or proposes to make, an offer to buy the same or conspicuously the same, number of securities.

98. <u>Fraudulent Transactions</u>

A person shall not induce or attempt to induce another person to subscribe for, sell or purchase securities by:

1/ making or publishing any statement, promise or forecast that is false, misleading or deceptive;

2/ concealing any material facts; or

፫/ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች የሆነ መረጃ በመካኒካል ወይም በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ መሣሪያ በመቅዳት ወይም በማከማቸት

ሌላ ሰው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመሸጥ እንዲያመለክት፣ እንዲገዛ ወይም እንዲሸጥ መገፋፋት ወይም ለመገፋፋት መሞከር የለበትም፡፡

፺፱. የሸፍጥ ዘዴዎችን መጠቀም

ማንኛውም ሰው፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ፣ ከሌላ ሰው ጋር ከሚያደርገው ፈርሞ ከመግዛት፣ ከግዥ እና ከሽያጭ ግብይይት ጋር በተያያዘ፡-

፩/ ሌላውን ሰው በማታለል ወይም ማንኛውንም አይነት መሣሪያ፣ ዘዴ፣ ወይም ረቂቅ መንገድን በመጠቀም፤ ወይም

፪/ ሌላን ሰው በሚያጭበረብር ወይም በሚያታልል፣ ወይም ሊያታልሉ ወይም ሊያጭበረብሩ በሚችሉ ድርጊቶችና ተግባራት ወይም አሠራር በመሠማራት፤

ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ሊገዛ ወይም ሊሸጥ አይችልም፡፡

፻. ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫዎች

፩/ ማንኛውም ሰው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ፣ ሌላ ሰው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወይም ሌሎች የተመዘገቡ ማናቸውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት ቃል እንዲገባ፣ እንዲገዛ፣ ወይም እንዲሸጥ ለመገፋፋት አላማ፤ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋ ባለበት እንዲቀጥል፣ እንዲጨምር፣ እንዲቀንስ ወይም እንዲረጋጋ ለማድረግ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ መስጠት የለበትም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣

አንድ ሰው፡-

3/ recording or storing in, or by means of, any mechanical, electrical or other device, information that is false or misleading

99. Use of Manipulative Means

A person shall not, directly or indirectly, in connection with any transaction with any other person involving the subscription, purchase or sale of securities:

1/ using any device, scheme or artifice to defraud the other person; or

2/ engaging in any act, practice or course of business which is fraudulent, deceptive, or likely to defraud or deceive that other person.

100. False or Misleading Statements

1/ A person shall not make false or misleading statement, directly or indirectly, for the purpose of inducing the subscription for or sale or purchase of securities by another person or maintaining, increasing, reducing or stabilizing the price of such securities.

2/ Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, a person shall not make any statement which:

ሀ) በተገለጸበት ጊዜና አኳኋን ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሀሰተኛና አሳሳች የሆነ እና ሰውየውም ሀሰተኛና የተዛባ መሆኑን የሚያውቀው ወይም አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ሊያውቀው የሚችል፤ ወይም

ለ) አንድ ወሳኝ ጉዳይ ቀሪ በመሆኑ ምክንያት ሀሰተኛና የተዛባ የሆነ፣ እና ሰውየውም ቀሪ በሆነው ወሳኝ ጉዳይ ምክንያት ሀሰተኛና የተዛባ መሆኑን የሚያውቀው ወይም አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ሀሰተኛና የተዛባ መሆኑን ሊያውቀው የሚችል፤

መግልጫ መስጠት የለበትም፡፡

a) at the time and in light of the circumstances in which it was made, is false or misleading with respect to any material fact and which that person knows or reasonably ought to know is false or misleading; or

b) by reason of the omission of a material fact, it is rendered false or misleading and which that person knows or ought to know is rendered false or misleading by reason of omission of that fact.

፩፻፩. <u>የጅሮ ጠብ እና ሌሎች የግብይት አይነቶች</u>

፩/ የዋጋ ልዩነት ያለበት የደንበኛ ትዕዛዞችን በተመለከተ የውስጥ አዋቂ መረጃ ያለውና ትዕዛዞቹ መኖራቸውን ያወቀ እና በሚመለከተው ሰነደ መዓለ ንዋዮች ወይም በማናቸውም ኢንቬስትመንቶች በቀጥታ በሌላ ሰው አማካኝነት ለራሱ ግብይት የሚፈጽም ማንኛውም ህጋዊ ፈቃድ ያለው ሰው የደንበኛው ትዕዛዝ ከመፈጸሙ በፊት በዋጋ ልዩነቱ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

፪/ ፈቃድ ያለው ሰው ከደንበኞቹ ቀድሞ መገበያየት ወይም በደንበኞቹ ፋንታ የዕለት ገበያ በተጋነነ መልክ ከፍ አድርጎ መዝጋት አይችልም፡፡

101. <u>Front–Running and Other Trading Practices</u>

1/ Any licensed person who has insider information on client orders with a price differential or is aware of such orders and effects an own account transaction in the securities concerned or in any related investments directly through any other person, shall not take advantage of the price differential before the client order is executed.

2/ A licensed person shall not deal ahead of his clients or mark the close or excessively deal on behalf of clients.

፩፻፪. <u>በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ስለሚጣሉ ገደቦች</u>

ማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ በሚወጣ መመሪያ ገደብ በተጣለባቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ማካሄድ አይችልም፡፡

102. <u>Restrictions on Trading of Securities</u>

A person shall not engage in trading of securities that are restricted by directive of the Authority.

ክፍል አስራ ሶስት
የካሣ ፈንድ

፩፻፫. የካሳ ፈንድ ስለ ማቋቋም

፩/ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የውል ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት የገንዘብ ኪሣራ ለሚደርስባቸው ኢንቬስተሮች ካሣ የመስጠትን እና የመብት ጥያቄ ያልቀረበባቸውን የተሰበሰቡ የትርፍ ድርሻዎችን ሁኔታው ሲፈጠር ለተጠቃሚዎች የመክፈልን ዓላማዎች ያነገበ የካሳ ፈንድ (ከዚህ በኃላ ‹‹ፈንድ›› እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ውጭ ለኢንቨስተሮች የተሟላ ጥበቃ የሚያደርጉ ሌሎች ዝግጅቶች መኖራቸውን ካመነ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሱት ግዴታዎች ነፃ ሊያደርገው ይችላል፡፡

፫/ የካሣ ፈንዱ የገንዘብ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) ፈቃድ ባላቸው ሰዎች ለካሳ ፈንድ እንዲከፈል የሚጠየቅ ገንዘብ፤

ለ) የካሳ ፈንዱ ገንዘብን ኢንቨስት በማድረግ የሚገኝ ወለድና ትርፍ፤

ሐ) ግዴታቸውን መወጣት ባለመቻላቸው ኢንቨስተሮችን ለካሳ ክፍያ ከዳረጉ አካላት በባለስልጣኑ ወይም በባለስልጣኑ በተወከለ አካል የሚሰበሰብ ገንዘብ፤ ወይም

PART THIRTEEN
COMPENSATION FUND

103. Establishment of a Compensation Fund

1/ The Compensation Fund (here under called the “Fund”) is hereby established for the purposes of granting compensation to investors who suffer pecuniary loss resulting from the failure of a capital market service provider or securities exchange to meet his contractual obligations and paying beneficiaries from collected unclaimed dividends when they resurface.

2/ Where the Authority is satisfied that adequate arrangements, other than those required under Sub-Article (1) of this Article for the protection of investors exist, the Authority may exempt a securities exchange from the requirements of Sub-Article (1) of this Article.

3/ The Compensation Fund shall consist of:

a) such moneys as are required to be paid into the Compensation Fund by licensed persons;

b) such sums of money as accrued from interest and profits from investing Compensation Fund moneys;

c) such sums of money recovered by or on behalf of the Authority from entities whose failure to meet their obligations to investors result in payments from the Compensation Fund; or

መ) በመንግሥት በፀደቀው መሠረት ለካሣ ፈንድ ዓላማዎች ከሌላ ማናቸውም ምንጭ ከተገኘ ገንዘብ፡፡

፬/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ሐ) የተጠቀሱትን ገንዘቦች ለማስከፈል የሚያስችል አዲስና ወቅታዊ መረጃ የሚያቀርብን ማንኛውንም ሰው ሊሸልም ይችላል፡፡ ሆኖም:-

ሀ) ይህ ድንጋጌ በማንኛውም የባለስልጣኑ ሠራተኛ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤

ለ) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈለው ሽልማት ከተገኘው ገንዘብ ከሦስት በመቶ ሊበልጥ አይችልም፤ እና

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) የተጠቀሰው ሽልማት፣ የተገኘው ገንዘብ ወደ ፈንዱ ገቢ ከመደረጉ በፊት መከፈል አለበት፡፡

፭/ በካሳ ፈንድ ውስጥ የተጠራቀመው ገንዘብ በባለስልጣኑ ኢንቨስት ሊደረግ ይችላል፡፡

፮/ ከፈንዱ ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ጉዳዮች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናሉ፡-

ሀ) የፈንዱ አስተዳደር፤

ለ) የፈንዱ ገንዘብ ኢንቨስት የሚደረግበት ፖሊሲ፤

ሐ) በፈንዱ ውስጥ ሊኖር የሚችለው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን፣ እና ከዝቅተኛው መጠን ቢቀንስ መደረግ ያለበት ሁኔታ፤

መ) የፈንዱን ግዴታዎች ለማሟላት ሊጣሉ ስለሚችሉ ክፍያዎች፤

ሠ) በፈንዱ ላይ የይገባኛል ክስ የሚቀርብበት ሁኔታ፤ እና

d) such sums of money as are received for purposes of the Compensation Fund from any other source approved by the Government.

4/ The Authority may reward any person who provides new and timely information leading to the recovery of sums of money referred to in Sub-Article (3)(c) of this Article. However:

a) this provision shall not apply to any officer of the Authority;

b) the reward payable under this Article shall not exceed three per cent of the amount recovered; and

c) the reward referred to in paragraph (b) shall be paid before the recovered sums of money are transferred to the Fund.

5/ Monies which have accumulated in the Compensation Fund may be invested by the Authority.

6/ The following issues related to the Compensation Fund shall be determined by Regulation of the Council of Ministers:

a) Administration of the Fund;

b) Investment policy of monies of the Fund;

c) Minimum amount to be kept in the Fund, and provisions if the Fund is reduced below the minimum amount;

d) Levies that may be imposed to meet liabilities of the Fund;

e) Manner of lodging claims against the Fund; and

https://ethiodata.et/

ረ) ፈንዱን ለማቋቋምና ለማስቀጠል የሚያስፈልጉ ማናቸውም ጉዳዮች፡፡

፻፬. <u>ከፈንዱ ስለሚፈጸሙ ክፍያዎች</u>

፩/ ለፈንዱ የሚደረጉ መዋጮዎች እና ከፈንዱ የሚከፈሉ ክፍያዎች ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈጸማል፡፡

፪/ በማንኛውም ፈቃድ ባለው ሰው ጥፋት ምክንያት ከካሳ ፈንዱ የሚደረግ ማናቸውም ክፍያ ለፈንዱ የሚመለስ እዳ ሆኖ፣ ባለስልጣኑም በማንኛውም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ የሚያስመልሰው ይሆናል፡፡

፻፭. <u>የፈንዱ ሀብትና ዕዳ</u>

የፈንዱ ሀብቶች በዚህ ክፍል ለተመለከተው ዓላማ ሲባል ከሌሎች የባለስልጣኑ ንብረቶች ተለይተውና ተጠብቀው ይያዛሉ፡፡

<u>ክፍል አስራ አራት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፻፮. <u>የወንጀል ተጠያቂነት</u>

፩/ ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ዕውቅና ሳይሰጠው እንደ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የሰራ ወይም እንደሚሠራ አድርጎ የተንቀሳቀሰ እንደሆነ፣ ከብር ፻ሺ በማያንስና ከብር ፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፭ ዓመት በማያንስና ከ፲፪ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ወይም ፈቃዱ በባለስልጣኑ ሳይፀድቅለት በንግድ ሥራነት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ተዛማጅ ውሎች ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ

f) Any other matter incidental to the establishment and maintenance of the Fund.

104. <u>Disbursements from the Fund</u>

1/ The contributions to and payments out of the Fund shall be made in accordance with directives to be issued by the Authority.

2/ Any disbursement from the compensation fund that is accountable to the default of any licensed person is a debt due to the fund and is recoverable at the suit of the Authority in any court of competent jurisdiction.

105. <u>Assets and Liability of the Fund</u>

The assets of the Fund shall be kept separate from all other properties and shall be kept in trust for the purposes set out in this Part.

<u>PART FOURTEEN</u>

<u>MISCLLANEOUS PROVISIONS</u>

106. <u>Criminal Liability</u>

1/ Whoever operates or purports to operate as a self-regulatory organization without being recognized as such by the Authority shall be punishable with a fine of no less than Birr 100,000 and no more than Birr 150,000, and a rigorous imprisonment of no less than 5 years and no more than 12 years.

2/ A person who establishes or launches a business as a securities exchange or a derivative exchange or over-the-counter market without obtaining license from the Authority under this Proclamation

ዙሪያ ገበያ ያቋቋመ ወይም የከፈተ እንደሆነ፣ ከብር ፩፻ሺ በማያንስና ከብር ፩፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፭ ዓመት በማያንስና ከ፲፪ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፫/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ፈቃድ በሌለዉ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ተዛማጅ ውሎች ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ የሌለዉ መሆኑን እያወቀ የተገበያየ እንደሆነ፣ ከብር ፩፻ሺ በማያንስና ከብር ፩፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፭ ዓመት በማያንስና ከ፲፪ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፬/ ፈቃድ ከተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ውጭ ያለ ሌላ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ‹‹የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ›› ወይም ‹‹የአክሲዮን ገበያ›› ወይም ‹‹የተዛማጅ ውሎች ገበያ›› የሚል ስም፤ ወይም

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ከተጠቀሱት ስያሜዎች ከአንዱ ጋር በጣም ተቀራራቢ ስያሜ በመሆኑ ሊያታልል የሚችል ማናቸውም ስም

የወሰደ ወይም የተጠቀመ ወይም በየትኛውም ቦታ የለጠፈ ወይም ያሳየ እንደሆነ፣ ከብር ፩፻ሺ በማያንስና ከብር ፩፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና እስከ ፯ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፭/ ማንኛውም ሰው ያልተመዘገበ፣ በመንግስት ዋስትና ያልተሰጠው ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት በወጣ መመሪያ ከምዝገባ መስፈርቶች ግዴታ ነፃ ያልሆነ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ያወጣ እንደሆነ፣ ከብር ፩፻፶ሺ በማያንስና ከብር ፫፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፯ ዓመት በማያንስና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

shall be punishable with a fine of no less than Birr 100,000 and no more than Birr 150,000, and a rigorous imprisonment of no less than 5 years and no more than 12 years.

3/ A person who knowingly deals in securities at or through unlicensed securities exchange or a derivative exchange or over-the-counter market under Sub-Article (2) of this Article shall be punishable with a fine of no less than Birr 100,000 and no more than Birr 150,000, and a rigorous imprisonment of no less than 5 years and no more than 12 years.

4/ A person, other than a licensed securities exchange, who takes or uses, or has attached to, or exhibited at, any place:

a) the title “securities exchange” or “stock exchange” or “derivatives exchange”; or

b) any title which so closely resembles either of the titles specified in paragraph (a) of this Sub-Article as to be likely to deceive,

shall be punishable with a fine of no less than Birr 100,000 and no more than Birr 150,000, and a rigorous imprisonment of no more than 7 years .

5/ Any person who issues a security that has not been registered or is not guaranteed by the Government or exempted by directives made under this Proclamation from the requirements of registration of securities shall be punishable with a fine of no less than Birr 150,000 and no more than Birr 300,000, and a rigorous imprisonment of no less than 7 years and no more than 15 years.

፮/ ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳይገኝ ቁጥጥር በሚደረግበት የካፒታል ገበያ ተግባራት ተሰማርቶ የተገኘ እንደሆነ፣ ከብር ፻፶ሺ በማያንስና ከብር ፫፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፯ ዓመት በማያንስና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፯/ ማንኛውም ሰው የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ፈቃድ ከተሰጣቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ካልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ውጭ ሲገበያይ የተገኘ እንደሆነ፣ ከብር ፻ሺ በማያንስና ከብር ፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፭ ዓመት በማያንስና ከ፲፪ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፰/ ማንኛውም ሰው ማናቸውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ፈቃድ ከተሰጠው የገበያ አከናዋኝ ውጭ ሲገበያይ የተገኘ እንደሆነ፣ ከብር ፶ሺ በማያንስና ከብር ፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና እስከ ፯ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፱/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፭ የተደነገገውን በመተላለፍ በውስጥ አዋቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተገበያየ እንደሆነ፣ ከብር ፪፻ሺ በማያንስና ከብር ፫፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፯ ዓመት በማያንስና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፲/ ማንኛውም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ የተሿሚ እንደራሴነት ፈቃድ የሌለውን ሰው ዉክልና በመስጠት ቁጥጥር የሚደረግበትን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ወይም ተግባራትን ያሰራ እንደሆነ፣ ከብር ፻ሺ በማያንስና ከብር ፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፭ ዓመት በማያንስና ከ፲፪ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

6/ A person who performs a regulated capital market activity without license from the Authority shall be punishable with a fine of no less than Birr 150,000 and no more than Birr 300,000, and a rigorous imprisonment of no less than 7 years and no more than 15 years.

7/ A person who deals in registered securities otherwise than through a licensed securities exchange or over-the-counter market shall be punishable with a fine of no less than Birr 100,000 and no more than Birr 150,000, and a rigorous imprisonment of no less than 5 years and no more than 12 years.

8/ A person who deals in any securities otherwise than through a licensed dealer shall be guilty of an offence and shall be punishable with a fine of no less than Birr 50,000 and no more than Birr 100,000, and a rigorous imprisonment of up to 7 years.

9/ A person who trades with inside information by contravening Article 95 of this Proclamation shall be punishable with a fine of no less than Birr 200,000 and no more than Birr 350,000, and a rigorous imprisonment of no less than 7 years and no more than 15 years.

10/ A person who performs regulated capital market services or activities by nominating a representative who does not hold an appointed representative's license shall be punishable with a fine of no less than Birr 100,000 and no more than Birr 150,000, and a rigorous imprisonment of no less than 5 years and no more than 12 years.

፲፩/ ማንኛውም ሰው የተሿሚ እንደራሴነት ፈቃድ ሳይኖረው እንደ ተወካይ ሆኖ ቁጥጥር የሚደረግበትን የካፒታል ገበያ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ፣ ከብር ፩፻ሺ በማያንስና ከብር ፩፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፭ ዓመት በማያንስና ከ፲፪ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፲፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት፣ ፈቃድ ለማግኘት ወይም ለማሳደስ ብሎ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በጽሑፍ፣ በቃል ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ሃሰተኛና የተዛባ መረጃ ያቀረበ ወይም ሐሰተኛ መረጃ በማቅረብ ፈቃድ ያወጣ ወይም ያሳደሰ እንደሆነ፣ ከብር ፩፻፶ሺ በማያንስና ከብር ፫፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፯ ዓመት በማያንስና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፲፫/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ባልተመዘገበ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያለን ጥቅም የሚወክሉ አክሲዮኖችን፣ ክፍልፋዮችን ወይም ሌሎችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለመግዛት፣ ለማስተላፍ ወይም ለማስወገድ ወይም ግዴታ ለማስገባት በመፈለግ ውል የተዋዋለ ወይም የፈጸመ ወይም እንዲፈጽሙ የጠየቀ፤ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ያልተመዘገበ የጋራ ኢንቨስትመን ፈንድ ያቋቋመ እና ያካሄደ እንደሆነ፣ ከብር ፫፻ሺ በማያንስና ከብር ፭፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፲ ዓመት በማያንስና ከ፳ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

11/ A person who performs regulated capital market services or activities as a representative without holding an appointed representative's license shall be punishable with a fine of no less than Birr 100,000 and no more than Birr 150,000, and a rigorous imprisonment of no less than 5 years and no more than 12 years.

12/ A person who, for the purpose of obtaining or renewing a license in accordance with this Proclamation, whether directly or indirectly, makes any representation, in writing, orally or otherwise, which is false or misleading; or obtained or renewed a license on the bases of false or misleading information shall be punishable with a fine of no less than Birr 150,000 and no more than Birr 300,000, and a rigorous imprisonment of no less than 7 years and no more than 15 years.

13/ A person who enters or offers to enter into any agreement for, or with a view to, acquiring, disposing of, or subscribing for, shares, units or other securities representing an interest in a collective investment scheme that is not registered in accordance with the provisions of this Proclamation, or establishes and operates a collective investment scheme that is not registered in accordance with the provisions of this Proclamation, shall be punishable with a fine of no less than Birr 300,000 and no more than Birr 500,000, and a rigorous imprisonment of no less than 10 years and no more than 20 years.

https://ethiodata.et/

፲፬/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት አንድን ጉዳይ ለመከታተልና ለመመርመር የሚጠቅም ሰነድ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ያጠፋ፣ አስመስሎ ያቀረበ ፣ የደበቀ ወይም ያስወገደ፣ ወይም እንዲጠፋ፣ ተመሳስሎ እንዲሰራ፣ እንዲደበቅ ወይም እንዲወገድ ያስደረገ ወይም የፈቀደ እንደሆነ፣ እስከ ፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፲፭/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በገበያ ሸፍጥ፣ ወይም በሃሰተኛ ግብይት ወይም በማጭበርበር ግብይት ወይም በጆሮ ጠብ ንግድ የተሠማራ፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻ በተገለጸው መሠረት ማታለያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሌሎችን ሰዎች ያጭበረበረ ወይም ያታለለ፤

ሐ) ከደንበኞቹ ቀድሞ የተገበያየ፣ ወይም የዕለቱን ገበያ ዋጋ በተጋነነ ሁኔታ ከፍ አድርጎ የዘጋ ወይም በደንበኞቹ ስም ከሚገባው በላይ የተገበያየ፤ ወይም

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፩ በተደነገገው መሠረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ አንድ ሰው በሌላ ኩባንያ ውስጥ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም ሌሎች ማናቸውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለመግዛት እንዲፈርም፣ እንዲገዛ፣ ወይም እንዲሸጥ ለመገፋፋት በማሰብ፤ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋ ባለበት እንዲቀጥል፣ እንዲጨምር፣ እንዲቀንስ ወይም እንዲረጋጋ ለማድረግ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ያወጣ እንደሆነ፤

ሠ) በዚህ አዋጅ መረጃን ስለመስጠት የተደነገገዉን በመተላለፍ መረጃን ለሌላ ሰው አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤

ከብር ፪፻ሺ በማያንስና ከብር ፫፻፶ሺ

14/ A person who destroys, falsifies, conceals or disposes of, or causes or permits the destruction, falsification, concealment or disposal of, any document, which the person knows or ought to know is relevant to an inspection or investigation under this Proclamation shall be punishable with a rigorous imprisonment of up to 5 years.

15/ A person who:

a) engages in market manipulation or false trading or fraudulent transactions or front running;

b) uses manipulative means to defraud or deceive that other person under Article 100 of this Proclamation;

c) deals ahead of his clients or mark the close or excessively deal on behalf of his clients; or

d) makes false or misleading statements, directly or indirectly, for the purpose of inducing the subscription for, sale or purchase of securities by another person of any company, or of any other listed securities, or to maintain, increase, reduce or stabilize the price of such securities under Article 101 of this Proclamation,

e) discloses information in violation of the information disclosure provisions of this proclamation

shall be punishable with a fine of no less

https://ethiodata.et/

በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፯ ዓመት በማያንስና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፲፮/ ማንም ሰው በውጤቱ እርግጠኛ ቢሆንም ባይሆንም ሌሎች ሰዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋይ እንዲገዙ ለመገፋፋት ወይም ባለአክሲዮኖችን ወይም ባለገንዘቦችን ለማታለል ወይም ለማጭበርበር በማሰብ ሀሰተኛ መሆኑን የሚያውቀውን የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ያዘጋጀ፣ ያሰራጨ ወይም ያሳተመ እንደሆነ፣ ከብር ፪፻ሺ በማያንስና ከብር ፫፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ፯ ዓመት በማያንስና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፲፯/ ማንኛውም ሰው፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፫(፬) በተደነገገው መሠረት፡-

ሀ) ሽልማት ለማግኘት ብሎ ከባለስልጣኑ ሠራተኛ ጋር የተመሳጠረ፤

ለ) በባለስልጣኑ ዉስጥ እየሰራ ሳለ ሌሎች ሰዎች መረጃ እንዲያገኙ ያገዘ እና መረጃ የሰጠ፤ ወይም

ሐ) የተሳሳተ መረጃ የሰጠ፤

እንደሆነ፣ እስከ ፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፲፰/ በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱት ወንጀሎች የተፈጸሙት ህጋዊ ሰውነት ባለው ድርጅት የሆነ እንደሆነ፣ ድርጅቱ፡-

ሀ) እስከ ፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል፣ እስከ ፭፻ሺ ብር፤

than birr 200,000 and no more than birr 350,000, and a rigorous imprisonment of no less than 7 years and no more than 15 years.

16/ Whoever, directly or indirectly, makes, circulates or publishes a prospectus that he knows is false, with intent to induce other persons, whether ascertained or not, to purchase a security, or deceive or defraud the shareholders or creditors shall be punishable with a fine of no less than Birr 200,000 and no more than Birr 350,000, and a rigorous imprisonment of no less than 7 years and no more than 15 years.

17/ A person who under Sub-Article (4) of Article 103 of this Proclamation:

a) colludes with an officer of the Authority for the purpose of collecting the reward;

b) while working at the Authority aids another person to get and provide information; or

c) provides false information,

shall be punishable with a rigorous imprisonment of up to 5 years.

18/ Where the offences under this Article are committed by a body corporate, the body corporate shall be punishable as follows:

a) Up to Birr 500,000 for offences punishable with a rigorous imprisonment of up to 5 years;

ለ) እስከ ፯ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል፣ ከብር ፭፻ሺ በማያንስና ከብር ፩ ሚሊዮን በማይበልጥ፤

ሐ) ከ፭ እስከ ፲፪ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል፣ ከብር ፭፻ሺ በማያንስና ከብር 1.5 ሚሊዮን በማይበልጥ፤

መ) ከ፯ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል፣ ከብር ፩ ሚሊዮን በማያንስና ከብር ፪ ሚሊዮን በማይበልጥ፤ እና

ሠ) ከ፲ እስከ ፳ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል፣ ከብር 1.5 ሚሊዮን በማያንስና ከብር 2.5 ሚሊዮን በማይበልጥ፤

የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፲፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፰) ከተደነገገዉ ቅጣት በተጨማሪ፣ ፍርድ ቤቱ በዐቃቤ ህግ ጠያቂነት ወይም በራሱ ተነሳሽነት ድርጅቱ እንዲፈርስ ወይም ንብረቱ እንዲወረስ ሊወስን ይችላል፡፡

፳/ በዚህ አንቀጽ ከተደነገጉት ቅጣቶች በተጨማሪ፣ እንደ-አስፈላጊነቱ ያለ አግባብ የተገኘ ጥቅም እንዲወረስ ወይም እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

፳፩/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከሚጣል መቀጮ የሚገኝ ገንዘብ እና የሚወረስ ወይም የሚመለስ ንብረት ለካሳ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል፡፡

b) No less than Birr 500,000 and no more than Birr 1,000,000 for offences punishable with a rigorous imprisonment of up to 7 years;

c) No less than Birr 500,000 and no more than Birr 1,500,000 for offences punishable with a rigorous imprisonment of no less than 5 years and no more than 12 years;

d) No less than Birr 1,000,000 and no more than Birr 2,000,000 for offences punishable with a rigorous imprisonment of no less than 7 years and no more than 15 years; and

e) No less than Birr 1,500,000 and no more than Birr 2,500,000 for offences punishable with a rigorous imprisonment of no less than 10 years and no more than 20 years.

19/ In addition to the penalties provided under Sub-Article (18) of this Article, the Court may, upon the application of the public prosecutor or on its own motion, decide to dissolve the body corporate or confiscate its property.

20/ In addition to the imprisonments and fines imposed under this Article, the proceeds of the crime shall be confiscated or recovered where relevant.

21/ Any sum of money collected through fines and confiscation or recovery of the proceeds of crimes under this Article shall be transferred to the Compensation Fund.

፩፻፯. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፮ መሠረት በወንጀል መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለስልጣኑ ራሱ በሚያደርገው የበላይ ክትትልና ምርመራ ላይ ተመሥርቶ ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በተላለፈ ሰው ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ፣ ፈቃድ ሊሰርዝ ወይም ሊያግድ እና/ወይም የባለፈቃዱን ከፍተኛ ኃላፊዎችን ወይም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ወይም እንዲታገዱ ትእዛዝ ሊሰጥ ወይም የገንዘብ ቅጣት ሊጥል ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ባለስልጣኑ በመመሪያ ይወስናል፡፡

፩፻፰. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ባለስልጣኑ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫/ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የዚህን አዋጅ አንቀፅ ፶፫ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ከመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር በተያያዘ ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤትን እና ክፍያ ማጣራትና መፈፀምን የሚመለከቱ ደንቦችን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

107. Administrative Measures

1/ Notwithstanding criminal conviction of a person under Article 106 of this Proclamation, the Authority may impose administrative measure based on its supervision or investigation report to revoke or suspend a license or order the dismissal or suspension of senior personnel or board of directors of the licensed person and/or impose fine on a person who contravenes the provisions of this Proclamation, or Regulations or Directives issued under this Proclamation.

2/ The Authority shall specify the administrative measures under Sub-Article (1) of this Article by directive.

108. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Authority may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

3/ The National Bank of Ethiopia may issue directives necessary for the implementation of Article 53 of this Proclamation and Regulations issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article in matters related to central securities depository and clearing for Government securities.

https://ethiodata.et/

፩፻፱. የፈቃድ ዕድሳት

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም ፈቃድ፣ በባለስልጣኑ የሚጠየቀውን ክፍያ በመክፈል በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

፩፻፲. የሠራተኞች አስተዳደር

የባለስልጣኑ የሥራ መሪዎች እና ሠራተኞች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት የሚተዳደሩ ይሆናል፡፡

፩፻፲፩. አለመግባባቶችን ስለመፍታት

፩/ የዚህ አዋጅ ክፍል ሰባት (፯) እንደተጠበቀ ሆኖ በካፒታል ገበያ ውስጥ በሚሳተፉ ወገኖች መካከል ይህን አዋጅ አስመልክቶ የሚነሳ ማንኛውንም የፍትሐብሔር ጉዳይ አለመግባባቶች በሽምግልና ይፈታሉ፡፡

፪/ አለመግባባቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሽምግልና የማይቋጭ የሆነ እንደሆነ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲያልቅ ይደረጋል፡፡

፫/ ከይግባኝ ጋር በተያያዘ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተሰጠው ውሳኔ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የመጨረሻ እና አስገዳጅ ይሆናል፡፡

፬/ የግልግል ዳኞች ስለሚሾሙበት ሁኔታ እና ስለ ዳኞች ብቃት መስፈርት፣ ስለ ግልግል ዳኝነት አሠራር እና ከግልግል ዳኝነት ጋር የተያያዙ ወጭዎችን በተመለከተ ባለሥልጣኑ በሚያውጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

109. License Renewal

Any license granted under this Proclamation shall be renewed annually by paying required fees to be prescribed by the Authority.

110. Administration of Employees

The employees and management of the Authority shall be governed by regulation to be issued by the Council of Ministers.

111. Settlement of Disputes

1/ Without prejudice to Part Seven (7) of this Proclamation, disputes among parties involved in the capital market concerning any civil matter arising under this Proclamation shall be resolved by mediation.

2/ Where the disputes cannot be resolved through mediation as per Sub-Article (1) of this Article, the matter shall be settled by arbitration.

3/ Without prejudice to provisions of the Civil Procedure Code relating to appeals, the arbitral award under Sub Article (2) of this Article shall be final and binding on the parties.

4/ The qualification and manner of appointment of arbitrators, the procedure of the arbitration proceedings, and the payment of arbitration related costs shall be determined by directive of the Authority.

https://ethiodata.et/

፩፻፲፪. ስለተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

፩/ የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፰/፪ሺ፫ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ ፬ እና የአንቀፅ ፬ ንዑስ አንቀፅ ፩ (ለ) በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ህግ ወይም ልማድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

፩፻፲፫. አዋጁ የሚጸናበት ቀን

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሀምሌ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ/ም

ሣህለወርቅ ዘውዴ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

112. Inapplicable Laws

1/ Article 2 Sub-Article (4) and Article 4 Sub-Article (1) paragraph (b) of the National Payment System Proclamation No. 718/2011 are hereby repealed.

2/ No, law or customary practice, inconsistent with this Proclamation, shall have effect with respect to matters governed by this Proclamation.

113. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, On this 23rd Day of July, 2021

SAHLEWORK ZEWUDIE
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

https://ethiodata.et/